## <u>የመጽሐፉ የፊት ሽፋን</u>

የመጽሐፉ የፊት ሽፋን በሰነድ፥ በትውፊት፥ በአርኪኦሎጂ፥ በሊንጉዊስቲክስና በፖሌኦንቶሎጂ መረጃዎች ላይ በዘመናዊ የጥናት ሜቶዶሎጂ በአገርኛ ቋንቋ ያዘጋጀሁትና ባለፉት አምስትና ስድስት ሺህ ዓመታት በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የተካሄደውን የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገር፥ ኅብረተሰብና መንግሥት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት በሥፍራና በጊዜ ሚዛን የሚያሳይ የአገሪቱ የመጀመሪያ የታሪክ ኅብረ ቀለም ካርታ ነው። መጽሐፉ በካርታው ላይ በመስመርና በቀለም ምልክቶች በአጭርና በጥቅል የቀረበ የኢትዮጵያ ረጅምና ውስብስብ ታሪክ ዝርዝር መግለጫና ማብራሪያ ነው።

ይህ ካርታ በኢትዮጵያ ረጅምና በሀውርታዊ የጥንት፥ የመካከለኛና የዘመናዊ ታሪክ ላይ አዘጋጅቼ ካቀረብኩት ሰፊ ጥናት ጋር፥ በኢትዮጵያ የካርታ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በ1988 በተዘጋጀው ብሔራዊ አትላስ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕትመት ወጥቷል። ባለሥልጣኑ የካርታውን ቅጅ ስለሰጠኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

# የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መገለጫዎች

## የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ግንዛቤ

### አራተኛ መጽሐፍ

أهدي كتاب عن تاريخ اثيوبيا [illegible]

[illegible]

12-14-99


ከዶ/ር ላጵሶ ጌ. ድሌቦ
ረዳት የታሪክ ፕሮፌሰርና ደራሲ.


1999

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

በ1999 ታተመ።

Typesetting by M. A. Allam



# መታሰቢያ

ይህ <u>የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች</u> የኢትዮጵያን ጥንታዊ የእስላም ሥልጣኔና የአገሪቱን ሕዝቦች የመስተጋብር እና የመወራረስ ታሪክ ከጊዜና ከዘመን ጨለማ ወደ ብርሃን አውጥተው ለትውልድና ለዓለም ላሳወቁ የሕዝብና የአገር ባለውለታዎች፣ ማለትም፦

1. በሐረር ከተማ ኤሚሬት ሰነድ የኢትዮጵያን የሸዋ ሱልጣኔት (896-1285) ታሪክ ላቆየው የሐረሩ ጸሐፊ።
2. የሐርላና የሀዲያ እስላም ሕዝቦችንና መንግሥታትን ታሪክ በአጼ አምደ ጽዮን (1314-1344) ዜና መዋዕል ለጻፈውና ስሙ ለማይታወቅ ኢትዮጵያዊ ጸሐፊ።
3. በ1330ዎቹ የይፋት፣ የሀዲያ፣ የደዋሮ፣ የአርባቢኒ፣ የሸርካ፣ የባሌና የደራ ሱልጣኔቶችን ታሪክ ለግብፁ ጸሐፊ አልዑመሪ ላስተማረው ኢትዮጵያዊ የሕግ ምሁርና ዲፕሎማት ሼክ ጀማሉዲን አብደላህ።
4. የይፋት፣ የሀዲያ፣ የደዋሮ፣ የአርባቢኒ፣ የሸርካ፣ የባሌና የደራ ሱልጣኔቶችን ታሪክ ከሼክ ጀማሉዲን አብደላህ ተምሮ በመጽሐፍ ለትውልድና ለዓለም ላቆየውና በ1348 ለሞተው ግብፃዊ ጸሐፊ ለፈድለአላህ አልዑመሪ።
5. የኢትዮጵያ የሰለሞናዊ ክርስቲያን ዓጼዎችንና የሃሸማይት ዋላስማ እስላም ሱልጣኖችን የጦርነት ታሪክ ከሰባቱ የይፋት፣ የሀዲያ፣ የደዋሮ፣ የአርባቢኒ፣ የሸርካ፣ የባሌና የደራ ሱልጣኔቶች ታሪክ ጋር መዝግቦ ላቆየው ግብፃዊ ጸሐፊ አህመድ ማክሪዚ (1364-1442)።
6. የኢማም አሕመድን የአመጽ ጦርነት (1524-1543) ታሪክ <u>ፉቱሕ አልሐበሻ</u> በተሰኘ መጽሐፍ ጽፎ ለትውልድና ለዓለም ላቆየው ለኢትዮጵያዊ የሕግ ምሁር ሽሃቢዲን ቢን አብዱልቃድር (1506-1543)።
7. የኢትዮጵያን የ1520-1620 ታላቁን የሕዝቦች እንቅስቃሴ ታሪክ በቅደም ተከተል በዜና ዘጋላ፣ በሠረጸ ድንግል ዜና መዋዕል፣ በሱሰንዮስ ዜና መዋዕልና በጋላ ታሪክ ጽፈው ላቆዩት ለኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች ባሕሪይ፣ ወልደሃይማኖት፣ ተክለሥላሴና አጽመ ጊዮርጊስ፣
8. ዘረኛ የውጭ አስተማሪዎች የኢትዮጵያን ጥንታዊ የደአማት-አክሱም ሥልጣኔ ፈጣሪዎች ከእስያ መጤ ሴማውያን ናቸው ብለው ለረጅም ዘመን ለዓለም ያስተማሩትን ተረት ውድቅ በማድረግ የሥልጣኔው ፈጣሪ ባለቤት ነባርና ሉአላዊ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መሆናቸውን በአርኪኦሎጂ መረጃና ትምህርት በቅደም ተከተል <u>Inscriptions de l'Ethiopie Antique</u> እና "Les Debuts de l'Histoire Ethiopienne" በተሰኙ ተከታታይ ጥናቶች ለዓለምና ለትውልድ ላረጋገጡ የኢፒግራፊ ምሁራን፣ የደቹ ፕሮፌሰር አብራሃም ጆሃን ድሬዊስና የሉክሰምበርጉ ፕሮፌሰር ሮገር ሽናይደር መታሰቢያ ነው።

# የደራሲው የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናትና ግንዛቤ

ለዚህ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች ትምህርትና ምርት ባለፉት አምስት የትምህርትና የሥራ አሥርታት በአገር ውስጥና በውጭ አገር የዓላማ፣ የመነሻ፣ የይዘት፣ የዕውቀት፣ የሙያ፣ የቴክኒክ፣ የሥልት፣ የተግባር፣ የማቴሪያልና የሞራል፣ የሀሳብና የእምነት ድጋፍ እርዳታና ግፊት የሰጡኝ ባለውለታ አስተማሪዎች፣ የትምህርትና የባህል ተቋማት፣ መጻሕፍት፣ የሃይማኖት፣ የታሪክና የፍልስፍና ምሁራንና ፈላስፋዎች፣ ድርጅቶችና ማኅበራት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ግለሰቦችና ወዳጆች እጅግ በጣም ብዙ ናቸው። በዚህ ወቅትና ኢጋጣሚ ጥቂቶችን ብቻ ከሕይወት፣ ከትምህርትና ከሥራ ገጠመኝ አኳያ እንደሚከተለው አስታውሳለሁ።

በሕፃንነቴ ዘመን ወላጆቼ በ1951* በአንድ ሳምንት ውስጥ በሞት ከተለዩኝ በኋላ በድምሩ ከ1953 እስከ 1964 ድረስ በትውልድ አገሬ በቦቢቾ የሱዳን ኢንተርዮር ሚሲዮን ትምህርት ቤት ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል፣ በሆሳዕና የራስ አባተ ቧያለው 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ7 እስከ 8ኛ ክፍል፣ በናዝሬት የአጼ ገላውድዎስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል፣ በናዝሬት ባይብል አካዳሚ ከ10ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ብዙ ሚሲዮናውያንና የኢትዮጵያ አስተማሪዎች በነፃ ያስተማሩኝ የ1ኛ እና የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ጠንካራ የሕይወት፣ የእምነትና የእውቀት መነሻ፣ መሠረትና መሣሪያ ሆኖኛል።

ከ1960 እስከ 1966 ድረስ በትምህርትና በሥራ ምክንያቶች በናዝሬት ከተማና በአካባቢው በነበርኩበት ዘመን ለወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ሠራተኞች አንድ ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያንና የግል ትምህ ርት ቤት አቋቁሜ በአስተዳዳሪነትና በአስተማሪነት ለስድስት ዓመ ታት ኅብረተሰቡን አገልግየዋለሁ።

ከ1953 እስከ 1966 ድረስ በትምህርትና በሥራ ምክንያቶች በቦቢቾ፣ በሆሣዕናና በወንጂ ሸዋ በነበርኩበት ዘመን በኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገርና ኅብረተሰብ የነበረውን የመሬት፣ የብሔረሰብ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የባህል፣ የፍትህ፣ የሥርዓት፣ የትምህርት፣ የመደብ፣ የአስተዳደር፣ የፖለቲካ፣ የአርሶአደርና የሠራተኛ ችግር፣ ብዝበዛና ጭቆና በሕይወትና ልምድ ከመስኩና ከመድረኩ ለማየትና ለማወቅ ችያለሁ። ይህም ገጠመኝ የኢትዮጵያን ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ

* እንደ አውሮፓ አቆጣጠር

ሕዝቦች ኅብረተሰብና መንግሥት ታሪክ ከሥር መሠረቱ እንዳጠና ወሳኝ መነሻና መሣሪያ ሆኖኛል።

ከ1966 እስከ 1974 ድረስ በአሜሪካ አገር በቨርጂኒያ እስቴት በኢስተርን ሜኖናይት ኮሌጅና በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ በሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ በሃይማኖት፣ በፍልስፍናና በታሪክ መስኮችና ጥናቶች የባችለርስ፣ የማስትሬትና የፒኤችዲ ዲግሪዎችን አገኘሁ። በሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ በከፍተኛ የትምህርት ውጤትና የውድድር ሚዛን የፎርድ ፋውንዴሽን ፌሎውሽፕ ሽልማት በማሸነፍ በፒኤችዲ ዲግሪ ጥናት ፕሮግራምና ሥራ ግራጁዌት ፌሎው ተማሪ ነበርኩ።

በፒኤችዲ ዲግሪ ጥናትና ዲሰርቴሽን የኢትዮጵያ የዘመኑ ሁለት ብሔራዊ የሕዝብ፣ የአገርና የሥርዓት ችግሮች በደቡብ ተዛማጅ የመሬት፣ የብሔረሰብ፣ የጎሳ፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ የሃይማኖትና የሥልጣን ችግር በሰሜን ደግሞ የኤርትራ የፖለቲካ ችግር እንደሆኑ በዩኒቨርሲቲ ጥናትና በሕትመት ሥራ በግልጽና በይፋ አረጋግጫለሁ።

በአሜሪካ በትምህርትና በሥራ ምክንያቶች ከ1966 እስከ 1976 ድረስ በቆየሁበት ዘመን የአገሪቱን ወቅታዊ የሥርዓትና የፖለቲካ ጉዳዮችን በሚመለከት በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር አባል ነበርኩ። ከትምህርት አኳያ በፍልስፍና መሠረታዊ የሰው፣ የኅብረተሰብ፣ የተፈጥሮ፣ የሕይወት፣ የእውቀት፣ የንብረት፣ የሕግ፣ የሃይማኖት፣ የኤቲክስ፣ የርዕዮተ ዓለም፣ የፖለቲካ፣ የሥርዓትና የመንግሥት ጉዳዮችን በሚመለከት ከምዕራብ ታላላቅ ፈላስፋ ዎችና ምሁራን በተለይም ከፍራንሲስ ቤከን፣ ከሬኔ ደካርት፣ ከጆርጅ በርክሌ፣ ከባሩክ እስፕኖዛ፣ ከቶማስ ሆብስ፣ ከጆን ላክ፣ ከዴቪድ ሁም፣ ከኤማኑኤል ካንት፣ ከጆርጅ ሄግል፣ ከሰረን ክርከጋርድና ከካርል ማርክስ እንዲሁም የታሪክ ትርጉምና ትምህርት በሚመለከት ከሄግልና ከማርክስ ታላቅ ትምህርታዊ ግንዛቤ አግኝቻለሁ። በተጨማሪም በሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ ታዋቂ አፍሮ አሜሪካዊ የታሪክ ምሁርና ጸሐፊ ፕሮፌሰር ቻንስለር ዊሊያምስ በአፍሪካ ታሪክ የጂኦ-ፖለቲካና የውጭ ኃይሎች የተጽዕኖ ሚና በሚመለከት መሠረታዊ ትምህርት አስተምረውኛል።

ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብና መንግሥት ታሪክ ባለፉት 700 ዓመታት የግብፅ፣ የአውሮፓና የኢትዮጵያ ክርስቲያን የሃይማኖት፣ የቋንቋ፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የነገሥታት ዜና መዋዕልና የቅዱሳን ገድል አስተማሪዎች ተርጓሚዎችና ጸሐፊዎች ካሳደሩበት ተጽዕኖ ነፃ ተደርጎ





ከሥልተ ምርትና ከሥርዓተ ማህበር አኳያ ከኢትዮጵያ ሕዝቦች አገራዊ አንድነትና ዲሞክራሲያዊ እኩልነት አኳያ እንደገና በአዲስ የጥናት ዘዴ መጠናትና መጻፍ እንዳለበት ከራሴ ጥናት ተረዳሁ። በዚሁ መሠረት በሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ ለፒኤችዲ ዲግሪ ባቀረብኩት ዲሰርቴሽን የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ የጥናት ሥልትና ሚዛን ማጥናትና መጻፍ ጀመርኩ።

ከ1974 እስከ 1976 በአሜሪካ በቨርጂኒያ እስቴት በሪችሞንድ ከተማ በቨርጂኒያ ዩኒየን ዩኒቨርሲቲ በረዳት ፕሮፌሰር ማዕረግ የአፍሪካ ጥናት ፕሮግራም ኃላፊና የታሪክ አስተማሪ ሆኜ ሠርቻለሁ። በግንቦት 1976 በእናት አገር ጥሪ የቨርጂኒያ ዩኒየን ዩኒቨርሲቲ ሥራዬን በፈቃዴ ለቅቄ ከውጭ ወደ አገሬ ተመለስኩ።

ከውጭ አገር ወደ አገሬ ከተመለስኩ በኋላ ከ1976 እስከ 1997 በኢትዮጵያ ማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ባህል ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ (ኢፌድሪ) ሕገ መንግሥት ኮሚሽንና በኢፌድሪ ፓርላመንት ዋና የታሪክ ኤክስፐርት በመሆን በድምሩ ለሀያ አንድ ዓመታት በዚህ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች ጥናት በስፋትና በዝርዝር የቀረበውን የራሴን የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብና መንግሥት ታሪክ ግንዛቤ ትምህርትና ትርጉም በሚመለከት የስድስት ጥናታዊ መጻሕፍት ሕትመትና ስርጭት ጨምሮ በልዩ ልዩ የትምህርት የባህልና የመገናኛ መንገዶች መድረኮችና መሣሪያዎች ማለትም በሕትመት ሥራ፣ በስብሰባ፣ በመጽሔቶችና በጋዜጦች፣ በሕዝባዊና በመንግሥታዊ ጉባኤዎች በብሔራዊ አትላስ፣ በሬዲዮና በቴሌቭዥን ሚዲያ በድምሩ በመቶ አምሳ የሚቆጠሩ ጥናታዊ ጽሑፎችንና ንግግሮችን በማቅረብ የራሴን አዲስ የኢትዮጵያ ታሪክ ትምህርትና ትርጉም ለኅብረተሰቡ በሕዝባዊ የአገር ቋንቋና ባህል አቅርቤአለሁ።

በዚህ ረገድና ተግባር በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ብሔራዊ አትላስ (*National Atlas of Ethiopia*) በኢትዮጵያ የካርታ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ በሳይንሳዊ ቴክኒክና አሠራር የተዘጋጀው በ1988 ነው። የካርታ ባለሥልጣን ለአትላሱ የታሪክ ምዕራፍ የሚያስፈልገውን በኢትዮጵያ የጥንት፣ የመካከለኛውና የዘመናዊ ታሪክ ላይ ከተስማሚ ካርታዎች ጋር የተዘጋጁ ጥናታዊ የሽልማት

ጽሑፎችን ለምርጫ የሚያቀርቡ የታሪክ ምሁራንን አወዳድሮ ለመምረጥ በጋዜጣ ዓለማቀፋዊ ማስታወቂያ አወጣ።

ከተወዳዳሪ የውጭና የአገር ውስጥ ምሁራን ለምርጫ ከቀረቡ የታሪክ ጽሁፎችና ካርታዎች በካርታ ባለሥልጣን ተመርጠ በስሜ ለአትላሱ አገልግሎት የዋለው በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት በአገሪቱ የጥንት፣ የመካከለኛውና የዘመናዊ ታሪክ ላይ ከዘጠኝ ካርታዎች ጋር አዘጋጅቼ ያቀርብኩት የኢትዮጵያ ረጅም፣ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች የአምስት ሺህ ዓመታት ታሪክ ጥናትና ትምህርት ነው።

በተጨማሪም የአትላሱ የታሪክ ጥናት ከዘጠኙ ካርታዎች ጋር በ1988፣ Ethiopia: A Cradle of History በሚል ርዕስ በልዩ እትም በኢትዮጵያ የማስታወቂያ ሚኒስቴር በብዙ ሺህ ኮፒዎች በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰራጨ። እንዲሁም በ1989፣ ኢትዮጵያ፣ የታሪክ መነሻ በሚል ርዕስና የአማርኛ ትርጉም በኢትዮጵያ የትምህርት ሚኒስቴር በ40,000 ኮፒዎች ታትሞ በአገሪቱ የትምህርት ቤቶች የትምህርት ማስተማሪያ መጽሐፍ እንዲሆን ተሰራጭቷል።

በዚህ መጽሐፍ ተደጋግሞ የሚጠቀሰው የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት (ኢብጥኢ) ከ1983 እስከ 1993 ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን ብሔራዊ የመሬት ክልልና የሕዝብ ቁጥር በሚመለከት በአገሪቱ ረጅም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ የጥናት ዘዴና ሚዛን የተሳካ ጥናት ያካሄደው ልዩ የትምህርት ተቋም ነው።

በዚህ ልዩ የጥናትና ምርምር ተቋም በተጠቀሰው ዘመን (1983-1993) ከላይ ከተመለከተው ጥናት ሌላ (1) *የምርትና የባህል ዕድገት በከምባታ-ሀዲያ* (1983)፣ (2) *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ* (1990)፣ (3) *የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም* (1991) እና (4) *የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ* (1993) በተሰኙ ርዕሰ ጉዳዮች በኢትዮጵያ ረጅም፣ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብና መንግሥት ታሪክ ላይ እነዚህን ጥናታዊ መጻሕፍት በሕዝባዊ የአገር ቋንቋና ባህል ጽፌና አሳትሜ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ በብዛትና በስፋት አሰራጭቻለሁ። በተጨማሪም በ1993-1994 የኢፌድሪ ሕገ መንግሥት ኮሚሽን የታሪክ ጥናት ቡድን ሰብሳቢ ኤክስፐርት በመሆን በሕገ መንግሥቱ ለአገሪቱ ታሪክ የተሰጠውን ከፍተኛ ግምትና ሥፍራ በእርካታ አረጋግጫለሁ። የራሴንም አስተዋጽኦ አድርጌዋለሁ።





ከእነዚህ መጻሕፍት፣ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ* በመጀመሪያ 18 ወራት ሶስት ጊዜ ታትሞ ተሰራጭቷል። የኢትዮጵያ የትምህርት ሚኒስቴር ከሁለቱ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ* እና *የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም* ብዙ ሺህ ኮፒዎችን የትምህርት መረጃ ምንጮች እንዲሆኑ ለ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤተ መጻህፍት አከፋፍሏል።

በአጭርና በጥቅል አነጋገር በ1983-1993 አሥርት ከላይ የተጠቀሱ ጥናታዊ መጻሕፍት ሕትመትና ሰፊ ስርጭት የኢትዮጵያን ረጅም፣ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብና መንግሥት ታሪካዊ መነሻ፣ ዕድገት፣ ይዘትና ተግባር በሚመለከት ለኢትዮጵያ ሕዝብና ኅብረተሰብ አዲስ ትምህርታዊ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ችያለሁ የሚል እምነት አለኝ። ይህም ትምህርታዊ ግምትና ግንዛቤ ይህን ቀጣይ *የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች* ማለትም የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ማብራሪያ ጥናት እንዳካሄድ የመንፈስ ግፊት፣ ብርታትና ትጋት ሰጥቶኛል።

በእነዚህ ጥናቶች ብሎም በመጽሐፉ ይዘትና ግኝት በስፋት እና በዝርዝር እንደተገለጸው፣ የግብጽና የአውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖትና የቋንቋ አስተማሪዎች ከተከታዮቻቸው ጋር በኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች ሕብረተሰብና ታሪክ ላይ እስከ የኢትዮጵያ የ1974 ሕዝባዊ አብዮት ድረስ ለረጅም ዘመን በፈጠሩ የይዘት፣ የቅርጽ፣ የስልትና የትርጉም ግድፈቶች የአገሪቱ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በትክክል ከሥልተ ምርትና ከሥርዓተ ማህበር አኳያ ሳይጠና፣ ሳይገለጽና ሳይታወቅ ዝክረ ተረት ሆኖ ኖሯል።

ይህ ሁሉ ከሆነና ከታወቀ በኋላ በአንድ በኩል ለተጠቀሰው የፖለቲካ ተረትና ትውፊት መሠረትና መሣሪያ ሆኖ የኖረው የኢትዮጵያ ጥንታዊ የዘውድ ሥርዓት ከገዥው መደብ ጋር በአብዮቱ ፍንዳታና ሂደት ተወግዷል። በሌላ በኩል ደግሞ በቅርቡ የተገኙ ሳይንሳዊ የጂኦፖለቲካ፣ የሰነድ፣ የሊንጉዊስቲክስ፣ የአርኪኦሎጂ፣ የፓለንቶሎጂና የኢቮሉሽን መረጃዎች በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ በውጭ አስተማሪዎች የተፈጠረውን የፖለቲካና የዘረኝነት ተረት ውግዘና ውድው አድርገውታል።

በመሆኑም ዛሬ በድህረ አብዮት በኢትዮጵያ በአንድ በኩል በአገሪቱ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች ሕብረተሰብና ታሪክ ላይ በውጭ አገር አስተማሪዎች ትምህርት የተፈጠ

ረውን ግድፈት በባህላዊ ትምህርትና አብዮት ለማስወገድ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያን ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በሳይንሳዊ ሥልተ ጥናትና ትርጉም እንደገና ለማጥናትና ለመጻፍ በሙያውና በመስኩ በተሰማሩ የአገሪቱ ምሁራን ፊት የማይታጠፍና የማይታለፍ ትውልዳዊ ግዴታና ኃላፊነት ተደቅኗል።

ባጭሩ ከዚህ በላይና በታች ከደራሲው የቀረበው ጅምር የኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ጥናት የተካሄደው ይህንን ሰብአዊና ትውልዳዊ ግዴታና ኃላፊነት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው። በመጨረሻም በምንም ሥፍራና ጊዜ ማንም ግለሰብ በደራሲው ጅምር የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ላይ ሊኖር የሚችለውን የመረጃ፥ የሥልት፥ የግንዛቤና የትርጉም ግድፈት በተሻለ የትምህርት መሣሪያ፥ መንገድና አሰራር ቢያርምና ቢያስተካክል ለደራሲውም ለሕብረተሰቡም የትምህርትና የእውቀት ግንዛቤ ስለሚሰጥ ከወዲሁ ይመሰገናል።



## ማውጫ


ገጽ

መቅድምና መግቢያ ... XVII

የኢትዮጵያ የብዙ ሕዝቦች ኅብረተሰብና መንግሥት
አከታተልና ዕድገት ... XVII

የሰሜን/ፊላሻና የሙስሊም ሕዝቦች ታሪክ ጥናትና ግንዛቤ ... XXIV

## ክፍል አንድ

የኢትዮጵያ ታሪክ ግምገማና ትንተና ... 1

1. ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ... 1
2. የኢትዮጵያ በሀውርታዊ ታሪክ መነሻና ዕድገት ... 5
   - የኢትዮጵያ ታሪክ መነሻና የባለቤት ጥያቄ ... 5
   - የኢትዮጵያ ሕዝቦች መጤዎች አይደሉም ... 6
   - የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሀገር በቀል ናቸው ... 8
   - የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ጥንታዊ ነው ... 9
   - አውሮፓውያን የማንነት ችግር አለባቸው ... 10
   - የሰው ዘር መገኛ የአፍሪካ አህጉር ነው ... 12
   - የአፍሮ-እስያ ቋንቋዎች መነሻና ትምህርት ... 13
   - የኢትዮጵያ ወንዞች የአፍሪካ ሥልጣኔ ምንጮች ናቸው ... 16
   - የተማከለ ቋንቋ ወጣት ነው ... 16
   - የጉራጌ አመጣጥ ታሪክ ... 18
   - ነጮች የአፍሪካን ሥልጣኔ ከደዋል ... 20
   - ለኢትዮጵያ ታሪክ በቂ ስፍራ አልተሰጠም ... 21
3. የኢትዮጵያ የጂኦ-ፖለቲካ ታሪክ ግንዛቤ ... 22
   - የኢትዮጵያና የአረቦች ግንኙነት ታሪክ ... 22
   - የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ ዕድገትና ዓለማቀፋዊ ይዘት ... 22
   - የኢትዮጵያ የ550-1300 የታሪክ መረጃ ያልተገኘበት 'ጨለማ ዘመን' ... 23
   - የኢትዮጵያና የአረቦች የጂኦፖለቲካ ታሪክ ... 25
   - በዘመነ እስልምና ዋዜማ በአካባቢው የዓለም ኃያላን መንግሥታት አሰላለፍ ... 27
   - የኢትዮጵያ የአረቢያ ግዛት ታሪካዊ መነሻ ... 28
   - የኢትዮጵያ ነገሥታትና ወታደሮች በአረቢያ ... 30

የአይሁዶች ጦርነትና የኢትዮጵያ ግዛት በየመን አረቢያ ... 33
የኢትዮጵያውያኑ የ577-610 የሂጃዝ አረቢያ ሰፈራና
የእስልምና ክስተት በመካ ... 35
የ615-631 የኢትዮ-አረብ ሙስሊም ስደተኞች በኢትዮጵያ ... 36
ኢትዮጵያና እስልምና ... 37
4. የጦርነት ተፅዕኖ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ... 39
የኃይለኛ መንግሥትና የደካማ ኅብረተሰብ ግንኙነት ... 39
የመንግሥትና የሃይማኖት ግኑኙነት ... 44
የሕዝቦች እንቅስቃሴና ባህላዊ መወራረስ በኢትዮጵያ ... 50
5. የሰብአዊ መብትና ነፃነት ጥያቄ-በኢትዮጵያ ታሪክ ... 58
የጦርነትና የሰብአዊ መብት ቅራኔ ... 58
የሰብአዊ መብትና ነፃነት ትምህርት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት 61
የሰብአዊ መብትና የነፃነት ሞዴሎች ... 61
1. የተፈጥሮ ሕግ ሞዴል ... 61
2. የማህበራዊ ሥርዓት ሞዴል ... 62
3. የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሞዴል ... 63
የ1948 የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶችና
ነፃነቶች ቻርተር ምሥረታ ... 64
የተመድ የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ታሪክ ... 66
6. የኢትዮጵያ ታሪክ ድልና ትንሣኤ ... 68
የሕዝብ የመብት ትግልና ድል ... 68
የታሪክ ትንሣኤና ትምህርት በአዲሲቱ ኢትዮጵያ ... 70
የእስልምና መነሻና ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ ... 73

## ክፍል ሁለት

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ግንዛቤ ... 79
1. የታሪክ መረጃ ትርጉምና ትምህርት ... 79
የቅድመ-ታሪክና የዘመነ-ታሪክ ልዩነትና ግንኙነት ... 79
የታሪክ መረጃ ዓይነቶች ... 80
የኢትዮጵያ የፖሌኦንቶሎጂ መረጃ ... 80
የኢትዮጵያ ታሪክ የሰነድ መረጃ ... 81
የፑንት-ኢትዮጵያ ታሪካዊ ክስተትና ዕድገት ... 81
የኢትዮጵያ ረጅም የሰነድ መረጃ ታሪክ ... 83





የአርኪኦሎጂ ሳይንስና የኢትዮጵያ ታሪክ ግኝት ... 85
2. የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ግንዛቤ ... 87
3. የኅብረተሰብና የሃይማኖት ግንኙነት ... 90
የሃይማኖት ማኅበራዊ ትምህርትና ተግባር ... 90
የሃይማኖት ድርጅትና ተግባር በጥንቱ አዋማዊ ግብዕ ... 91
የሃይማኖት ምሥጢራዊ ባሕሪውና ግልጽ ማኅበራዊ ፋይዳ . 92

## ክፍል ሦስት

የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች ዓይነትና ብዛት ... 93
1. የአዋማዊ ሃይማኖት ቀዳሚ መነሻና ሚና ... 93
አሰቢኑስ የትሮጅሎዳውያን የፀሐይ አምላክ ... 93
የደአማታውያኑ አዋማዊ አማልክትና ሃይማኖት ... 95
የአክሱማውያኑ አዋማዊ አማልክትና ሃይማኖት ... 95
የደቡብ ኢትዮጵያ አዋማዊ ሃይማኖቶችና የታሪክ መረጃዎች 96
2. የክርስትና ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት ... 100
የክብረ ነገሥቱ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ትምህርት ... 100
በኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት የአሪት መገኘት ጥያቄ ... 102
በአለቃ ታዬ የኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የቀረበ ሂስ ... 103
የክርስትና ታሪካዊ መነሻና ትምህርት ... 106
በኢትዮጵያ የክርስትና አባት አስተማሪዎች ... 110
የኢትዮጵያ የ550-1300 ‘ጨለማ‘ ዘመን ... 111
የክርስትና የዕድገትና የመስፋፋት ዘመን 1270-1524 ... 112
3. የሰሜን/ፈላሻ የኦሪት ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻ፥ ዕድገትና
ውድቀት ... 115
የሰሜን/ፈላሻ የጂኦፖለቲካ ታሪካዊ ፋይዳ ... 115
ኦሪታዊ የሰሜን/ፈላሻና የክርስቲያን ነገሥታት
የጂኦ-ፖለቲካ ጦርነት ... 119
የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀትና የመንግሥቱ የመስፋፋት
ታሪክ ... 119
የክብረ ነገሥትና የፍትሐ ነገሥት ትምህርት መነሻና ሚና
በኢትዮጵያ ታሪክ ... 121
በአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት የሰሜን/ፈላሻ ሚና ጥያቄ ... 123
የጉዲት ተረትና የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ ቅጣት ... 125

የትግሬ፥ የሰሜን/ፈላሻ፥ የአገውና የአማራ ሕዝቦች
የጋራ መነሻና ዕድገት ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 126
የሥርዓተ አሪት ታሪካዊ መነሻ በኢትዮጵያ ... ... ... ... ... ... 129
የኢትዮጵያ መምህራን ተግባር በሰሜን/ፈላሻ አገር ... ... ... ... 129
የእምስጣጤዎሳውያኑ የ1337-1450 የአሪት አመፅና ድል ... .. 131
የ1332-1632 የሰሜን/ፈላሻና የክርስቲያን ነገሥታት ጦርነቶች 135
የደቡብ ኢትዮጵያውያን ኋመፅ ተፅዕኖ በሰሜን/ፈላሻ
ታሪክ ላይ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 135
በሰሜን/ፈላሻ አገር የጎንደር መንግሥት ታሪካዊ
መነሻና ውጤት ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 139
የሠርፀድንግልና የሰሜን/ፈላሻ ጦርነቶች (1580-1595) ... ... ... 143
የቱርክ ነፍጠኞችና መድፎች በሰሜን/ፈላሻ ተራሮች ... ... ... 143
የ1580 የካሌፍ አምባ የመድፍና የመርግ ጦርነት ... ... ... ... 144
የ1580 የረድኤት አምባ የመድፍና የመርግ ጦርነት ... ... ... 146
የ1587 የጉሸን ወርቅ አምባ የመድፍና የመርግ ጦርነት ... ... 147
የሰሜን/ፈላሻ መንግሥት ውድቀት ... ... ... ... ... ... ... ... 148
የ1603-1632 የሃይማኖት ጦርነት ... ... ... ... ... ... ... ... ... 148
የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ትምህርትና ተግባር በኢትዮጵያ ... . 148
የ1609-1624 የዳግማዊ ጌዴኦን አመፅና የሰሜን/ፈላሻ
መንግሥት ፍፃሜ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 151
የጦርነቱ ታሪካዊ መነሻና ውጤት ... ... ... ... ... ... ... ... 152
የ1629-1632 የአገው አመፅና የኢትዮጵያ የካቶሊክ
መንግሥት ውድቀት ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 156
የቤተ እሥራኤል/ፈላሻ ሥቃይና የስደት ፍጻሜ ... ... ... ... ... 157
4. የእስልምና ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት... ... ... ... 161
ከእስልምና በፊት የኢትዮጵያና የአረቦች ታሪካዊ ግንኙነት 161
የኢትዮጵያና የሮማውያን የፖሊሲ ስምምነት በአረቢያ ... ... . 161
ኢትዮጵያ በአረቢያ ላይ የነበራት ፖሊሲ ታሪካዊ
መነሻና ዕድገት ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 162
የ517-525 የይሁዳውያኑ አመፅ በአረቢያ ... ... ... ... ... ... ... 168
በአረቢያ የአሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች ጦርነትና ውድቀት 168
የ517-525 የአረብ ስደተኞች በኢትዮጵያ ... ... ... ... ... ... ... 170
የይሁዳውያኑ የአረቢያ አመፅና ውድቀት ... ... ... ... ... ... ... 171





የኢትዮጵያ የ525-577 የደቡብ አረቢያ መንግሥት
ዕድገትና ውድቀት ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 172
የኢትዮጵያና የቁረይሽ አረብ ግንኙነት መነሻና
ዕድገት (577-610) ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 177
የኢትዮጵያውያኑ የሂጃዝ አረቢያ ስደትና ሰፈራ ... ... ... ... ... 177
በእስልምና ክስተት ዋዜማ በሂጃዝ፥ የኢትዮጵያና
የቁረይሽ አረቦች ግንኙነት ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 179
በእስልምና ምሥረታና ግምባታ የኢትዮጵያውያን ... ... ... ...
ተሳትፎና የድል አስተዋጽኦ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 184
የታሪክ መረጃ ምንጮች ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 184
የእስልምና ዓለም አቀፋዊ ክስተትና ዕድገት (610-661) ... ... 185
የኢትዮጵያውያን ተሳትፎና የድል አስተዋጽኦ
በእስልምና ምሥረታ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 188
በቁረይሽ አረቦች ጦርነት የኢትዮጵያ ሀበሾች ማንነትና ሚና 196
የሀበሻ መንግሥት መነሻና ውድቀት
በየመን አረቢያ (1021-1159) ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 202
በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የሙስሊሙ ዓለም ሚና ... .. 205

## ክፍል አራት

የእስልምና ሃይማኖትና መንግሥት መነሻና ዕድገት
በኢትዮጵያ 615-1300 ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 209
በዘመነ እስልምና የኢትዮጵያ የቀይ ባሕር በሮችና መንገዶች 209
የኢትዮጵያ እስላማዊ ሥልጣኔ ክስተትና ዕድገት (896-1300) 211
የታሪክ መረጃ ምንጮች ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 211
የኢትዮጵያ የማኽዙማይትና የሃሽማይት-ዋላስማ ሥርወ
መንግሥታት ታሪካዊ መነሻ ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 215
የኢትዮጵያ የሸዋ ቀዳሚ ሱልጣኔት ረጅም የጂኦ-ፖለቲካ
ታሪክ (896-1991) ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... 218

## ክፍል አምስት

የኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ረጅም የስያሜ ታሪክ ... 221
የሀበሻና የኢጋዓዚያን ነገዶች ጥያቄ በኢትዮጵያ ታሪክ ... .. 221
የሀበሻ ታሪካዊ መነሻና ትርጉም በአረቡ ዓለም ... ... ... ... 221
በኢትዮጵያ ታሪክ የሀበሻና የኢጋዓዚያን ጥያቄ ማብራሪያ .. 223

የአረቦቹ የአፍሪካውያን ግንዛቤና ስያሜ ........ 226
የኢትዮጵያ የአገርና የመንግሥት ስያሜ ረጅም ታሪክ ........ 227

## መደምደሚያ

የውጭ አገር አስተማሪዎች ትምህርት ተጽዕኖ
በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ........ 235
የመረጃ ምንጮች ........ 247

፣

## የመረጃና የማስረጃ ምንጮች

### ካርታና ቻርት

1) የዓለም ቋንቋዎች የመነሻና የሥርጭት ካርታና ቻርት ........ 3
2) የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የ5000 ዓመታት ታሪክ ካርታ 38
3) በ1855 ዘውዳዊ ምዕክልና በተጀመረ ጊዜ የኢትዮጵያ የነጻ
ሕዝቦችና መንግሥታት ካርታ ........ 54
4) የኢትዮጵያ የ1524 – 1543 የኢማም አህመድ ጦርነት ካርታ .... 99
5) የኢትዮጵያ የ1520 – 1660 ታላቁ የሕዝቦች እንቅስቃሴ ካርታ 208
6) የኢትዮጵያ የ1855 – 1900 ታላቁ ምዕክልና ታሪክ ካርታ ...... 220
7) የውጭ ኃይሎች ግፊት ፡ የኢትዮጵያ የትግልና የድል ካርታ ... 252

### ሠንጠረዥ

1) የኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች ዝርዝር ........ 55
2) በ1984 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከ20,000 በላይ የሰው ቁጥር
ያላቸው የኢትዮጵያ የ56 ብሔረሰቦች ዝርዝር ........ 56
3) በ1994–97 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች
ዓይነትና ብዛት ........ 57
4) የኢትዮጵያ የፖሌኦንቶሎጂና የአርኪኦሎጂ መረጃዎች ግኝት ... 81
5) በ522–1981 የኢትዮጵያን የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ያገኙ ምሁራን 85
6) በ1893–1981 የኢትዮጵያ የድንጋይ ላይ ጽሑፎችን
የተረጎሙ ምሁራን ........ 86
7) በ14ኛው ምዕተ ዓመት በጀማለዲን–ዑማሪ ግምት የኢትዮጵያ
የሰባት ሡልጣኔቶች የመሬት ስፋትና የሠራዊት ብዛት ........ 214

### የዘር ሐረግ

የኢትዮጵያ የማኽዙሚይትና የሃሽማይት ዋላስማ ሥርወ
መንግሥታት የነገድ ቁረይሽ ሐረግ ........ 217





# መቅድምና መግቢያ

## የኢትዮጵያ የብዙ ሕዝቦች ኅብረተሰብና መንግሥት ክስተትና ዕድገት

*የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች* የተሰኘው ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ጥናት ነው። መጽሐፉ በአዲስ ሳይንሳዊና ዘመናዊ የጥናት መረጃ፥ ሥልትና ሚዛን በሕዝባዊ የአገር ቋንቋና ባህል እስከ ዛሬ ድረስ በተገኙና በታወቁ የጂኦ-ፖለቲካ፥ የትውፊት፥ የሰነድ፥ የሊንጉዊስቲክስ (የቋንቋ ሳይንስ)፥ የአርኪኦሎጂ (ከከርሰ ምድር የሚገኙ ጥንታዊ ጽሑፎች)፥ የፓሌኦንቶሎጂ (ከከርሰ ምድር የሚገኙ የቅድመ ታሪክ የአጥንትና የድንጋይ መሣሪያዎች) እና የኢቮሉሽን (ሂደታዊ የተፈጥሮ የሕይወትና የሰው ክስተትና ዕድገት ትምህርት) መረጃዎች፥ ማስረጃዎች፥ ግኝቶችና ማብራሪያዎች ላይ የተመሠረተ የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብ፥ መንግሥትና ታሪክ አዲስ ትምህርትና ትርጉም ነው።

ይህ *የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች* ከይዘትና ከትምህርት ከሥልትና ከቴክኒክ ከድርጅትና ከዝግጅት አኳያ በአምስት ርዕስ ክፍሎችና በብዙ ምዕራፎች የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው። በመጽሐፉ የመጀመርያ ክፍል «የኢትዮጵያ ታሪክ ግምገማና ትንተና» በሚል ርዕስ ሥር በአንድ በኩል በግምትና በድምር ከ1270 እስከ 1974* ድረስ በ700 ዓመታት የግብፅ፥ የአውሮፓና የኢትዮጵያ የሃይማኖት፥ የቋንቋ፥ የሥነ ጽሑፍ፥ የነገሥታት ዜና መዋዕልና የቅዱሳን ገድል ጸሐፊዎች፥ ተርጓሚዎች እና አስተማሪዎች ተዛማጅ የመረጃ፥ የሥልትና የትርጉም ትምህርት በሥልተ ሂስ ተገምግሟል። በሌላ በኩል ግን በግምት በዓመተ ዓለም ከ500 እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በአሥር ምዕተ ዓመታት በአራቱ ጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግሪክና የግዕዝ ቋንቋዎችና ፊደሎች በድንጋይ ላይ ተጽፈው በዘመናችን የተገኙ የአዋማዊ ደአማት-አክሱም ጽሑፎችና ጥንታዊ የአጎራባች አረብ ሰነዶች ከዘመናዊ የሊንጉዊስቲክስና የፓሌኦንቶሎጂ

---

* ሌላ ማብራሪያ ካልተሰጠ በስተቀር በዚህ ጥናት የጊዜ ቀመር እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ነው።

መረጃዎች ጋር የተጠቀሱ የግብፅ፥ የአውሮፓና የኢትዮጵያ ክርስቲያን ጸሐፊዎችንና አስተማሪዎችን ወገናዊ ትምህርት ሰማረም ብሎም የኢትዮጵያን ጥንታዊና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች ታሪክ በአዲስ መንገድና መሣሪያ ለማጥናት፥ ለማወቅና ለማስተማር የሚያስችሉ ቁልፍ የትምህርትና የባህል መሣሪያዎች ሆነው ተገኝተዋል።

በተጠቀሱ ጥንታዊ የደአማት-አክሱም ጽሑፎች፥ የአረብ ሰነዶችና በዘመናዊ የሊንጉዊስቲክስና የፓሌኦንቶሎጂ መረጃዎች መሠረት፥ (1) የኢትዮጵያ ምድር ከሁሉ በፊት የሰው ዘር፥ ቋንቋና ሥልጣኔ ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተበት የሰውና የሥልጣኔ ምንጭና መነሻ ነው። (2) የኢትዮጵያ ሁሉም ኩሻዊ፥ ሴማዊ፥ ናይሎቲካዊና ኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች የአገሪቱ ጥንታዊ፥ ነባርና ተዛማጅ ሕዝቦችና ቋንቋዎች ናቸው። (3) የግዕዝ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት ጨምሮ የኢትዮጵያ ጥንታዊና አኩማዊ የደአማት-አክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በግብፅ፥ በአውሮፓና በኢትዮጵያ ክርስቲያን ጸሐፊዎችና አስተማሪዎች እንደ ተገመተው ከኢየሩሳሌምና ከአረቢያ የገቡ ሴማዊ የአይሁድና የአረብ ነገዶች ፈጠራ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ ጥንታዊና ነባር ሕዝቦች ምርት እንደሆኑ በታሪክ መረጃና ትምህርት በትክክል ተረጋግጧል።

(4) እንዲሁም በ330 የክርስትና ሃይማኖትን ቀጥሎም በ5ኛው ምዕተ ዓመት መጽሐፍ ቅዱስን ግሪኮ-ሮማውያን ክርስቲያኖች ወደ አክሱም ከማስገባታቸው በፊት በኢትዮጵያ ጥንታዊና አኩማዊ ምድርና ታሪክ የአይሁዳውያኑ መለኮታዊ የኦሪት ሃይማኖትና ሕግ በፍጹም አልተገኙም። (5) በመጨረሻ በ20ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በረጅም የፖለቲካ ትግልና ድል የአገሪቱን ታሪክና ባህል ከተጠቀሱ የውጭ አገርና የአገር ውስጥ ጸሐፊዎችና አስተማሪዎች ተጽዕኖ ነፃ አድርገዋል።

በመጽሐፉ ሁለተኛ ክፍል «የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ግንዛቤ» በሚል ርዕስ ከፍልስፍና አኳያ ከሁሉ በፊት የተፈጥሮ፥ የሰው፥ የአእምሮ፥ የተግባር፥ የእውቀት፥ የምርት፥ የሥርዓት፥ የባህልና የታሪክ መነሻ፥ መስተጋብርና መወራረስ ጥያቄ በሚመለከት የግንዛቤ ሀሳብና ትምህርት በከፊል እንደሚከተለው ቀርቧል። በዚህ የግንዛቤ ሀሳብና ትምህርት መሠረት የሰው ልጅ ራሱንና አካባቢውን በራሱ ማኅበራዊ የአእምሮ መሣሪያ በተወሰነ የሥፍራና የጊዜ ቀመር የሚያውቅና የሚለውጥ በማኅበራዊ ሥፍራው ራሱንና ባህሉን የሚፈጥር አንድ ልዩ አካል ነው።





የአእምሮና የዕውቀት ባለቤትና ጌታ የሆነው የሰው ልጅ ራሱንና አካባቢውን በሥፍራና በጊዜ ወሰን የሚያውቀውና የሚለውጠው ግን በታሪክ መሣሪያና እውቀት ነው። በዚህ ረገድና ተግባር የሰው ልጅ ህልውናና ሕይወት መኖርና መሆን በተግባራዊ ልምድ የሚከሰተው፥ የሚገለጸውና የሚታወቀው በተወሰነ የሥፍራና የጊዜ ገደብና ወሰን በራሱ የሥራ እንቅስቃሴና የቋንቋ መሣሪያ ነው። በዚህ አጭርና አጠቃላይ የተፈጥሮ፥ የሰው፥ የአእምሮ፥ የዕውቀት፥ የሀሳብ፥ የተግባር፥ የቋንቋ፥ የድርጅት፥ የባህል፥ የሥርዓትና የታሪክ ግንዛቤ፥ ትምህርትና ትርጉም መሠረት የኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረ ተሰብና መንግሥት ምንጭና መነሻ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ነው። በዚህ በተወሰነ የመሬት ክልል ላይ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ህልውናዊ መሠረቶች፥ መለያዎች፥ መግለጫዎችና መሣሪያዎች ናቸው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች በሙሉ በመካከላቸው የዓይነትና የደረጃ የእምነትና የባህል ልዩነትና ምርጫ ሳይደረግ የዚህ ሁለአቀፍ ሕዝባዊና አገራዊ ጥናትና ትምህርት ማዕከላዊ ርዕስ ጉዳዮች ሆነው ቀርበዋል።

በመጽሐፉ ሶስተኛ ክፍል «የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች ዓይነትና ብዛት» በሚል ርዕስ ሥር በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ ከጥንት እስከ ዛሬ ድረስ የተነሱ የአዋማ፥ የክርስትና፥ የሰሜን/ፈላሻ ኦሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች በተከታታይ ምዕራፎች በቅደም ተከተል ተገልጿል።

በዚህ ረገድና ተግባር ከ330 እስከ 615 ድረስ በ285 ዓመታት ሶስቱ መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስትና፥ የኦሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ከሶስቱ ሰማያዊ የጽላተ ሙሴ፥ የወንጌልና የቁርአን ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር በቅደም ተከተል ከመካከለኛው ምስራቅና ከምድረ አረቢያ በግሪኮ-ሮማውያንና በአረብ ስደተኞች፥ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች አማካይነት በሰላማዊ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደገቡ በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ሁሉ በተጨባጭ የታሪክ መረጃና ትምህርት በዝርዝር ተገልጿል።

የሃይማኖቶቹን ዕድገትና መስፋፋት በሚመለከት በግምት በሁለተኛው ሚሊኒየም መጀመሪያ ስድስት ምዕተ ዓመታት (1000-1600) ሶስቱ መለኮታዊና አሀዳዊ ሃይማኖቶች ማለትም ክርስትና በመሀል ሰሜኑ ደጋአምባ፥ በአክሱም-ትግሬ፥ በአገውና በአማራ አጎራባች ምድር፤ ኦሪት በሰሜን ምዕራብ በሰሜን/ፈላሻ ምድር፤ እስላምና በመሀል ደቡብ ምስራቅ በሐርላና በሀዲያ አጎራባች ምድር

በአንድ ዘመን በየአካባቢያቸው የአገሪቱ ሶስት ተቋማዊ የሕዝብና የመንግሥት ሃይማኖቶች ሆነው ተከሰቱ። አደጉ። ተስፋፉ። ተጋጩ። ተዋጉ። በመጨረሻ ደግሞ ታጠፉ።

በዚህ አኳያ በግምት ከ1270 እስከ 1600 ድረስ ለሶስት ምዕተ ዓመታት የመሬት የሥልጣንና የግዛት ባላንጣ ኃይሎች የነበሩ የኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ፥ አረታዊና እስላማዊ መንግሥታትና ባለሥልጣኖች በጂኦ-ፖለቲካ፥ በመሬትና በንግድ ጉዳዮችና ምክንያቶች ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉርን የዘውትር ጦርነት አውድማ አደረጉ። በመንግሥታቱ የመሬት፥ የግዛትና የንግድ ጦርነት ሃይማኖቶቹ በየአካባቢያቸው የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም መሣሪያዎችና አገልጋዮች ተደረጉ።

በመጨረሻ በ16ኛው ምዕተ ዓመት ከውጭ በፖርቱጋልና በቱርክ ተፃራሪ ኃይሎች ግፊት በአገር ውስጥ ደግሞ በተዛማጅ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚ የአመጽ ጦርነትና የ1520-1620 ታላቁ የሕዝቦች የፍልሰትና የሰፈራ እንቅስቃሴ ግፊት የኢትዮጵያ ሶስቱ የክርስቲያን፥ የአረትና የእስላም መንግሥታት በአንድ ዘመን በየፊናቸው ፈረሱ። በመንግሥታቱ ውድቀት ደግሞ ሃይማኖቶቹ በየአካባቢያቸው ከፖለቲካ ተጽዕኖ ነፃ ሆኑ። ከመንግሥታዊ ሞግዚትነትና ተጽዕኖ ነፃ ሆነው የሕዝብ ሃይማኖቶች መሆን ጀመሩ።

በዚህ ሁኔታና ወቅት በግምት ከ1559 እስከ 1855 ድረስ ለ3 ምዕተ ዓመታት በክፍለ አህጉሩ ነባር ኩሻዊ፥ ሴማዊ፥ ኦሞአዊና ናይሎቲካዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች መካከል በሥፍራ፥ በቋንቋ፥ በሃይማኖትና በባህል ታላቅ የመስተጋብርና የመወራረስ ሁኔታ፥ ሂደት እና ሥርዓት ተፈጠረ። በሌላ ቃል፥ በክፍለ አህጉሩ መንግሥታት ሲዳከሙና ሲወድቁ በሕዝቦች መካከል ነፃና ዘላቂ የሆነ የመስተ ጋብርና የመወራረስ እንቅስቃሴ የበለጠ ጠነከረ። አደገ። ተስፋፋ።

ከታሪክ አኳያ የዚህ የ1559-1855 የክፍለ አህጉሩ ነባርና አጎራባች ሕዝቦች የመስተጋብርና የመወራረስ ሁኔታ፥ ሂደትና ውጤት ለኢትዮጵያ በሀውርታዊ ኅብረተሰብና ታሪክ ዕድገት አንድ ታላቅ መነሻና መሠረት እንደሆነ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል። የዚህ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪካዊ ግንኙነት ሁኔታና ሂደት አንዱና ዋናው ምሳሌና መገለጫ የአዋማዊ ኦሮሞ ማኅበረሰብ ታሪካዊ ክስተት፥ ዕድገትና መስፋፋት ነው።

በዚህ አኳያ በ16ኛ ምዕተ ዓመት በ1520ዎቹ ጎዳማ ዛሬ





የኢትዮጵያ በቁጥርና በሥፍራ ትልቁ የሆነ ኩሻዊ የኦሮሞ ሕዝብ በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ በግምት በዓባያ ሐይቅና በገናሌ ወንዝ መካከል በሚገኘው ክልል "ገዳ" ተብሎ በሚታወቅ በራሱ ልዩ ሕዝባዊና ማኅበራዊ ሥርዓት እየተመራ በእንስሳት እርባታ ተሰማርቶ በዘላንነት የሚኖር አንድ አናሳ ማኅበረሰብ እንደነበር የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል። በዘመኑ የኦሮሞ ዘላን ማኅበረሰብ "ባዕዳን" የአካባቢ ሕዝቦችን በመብትና ግዴታ የራሱ ወገን ማለትም አንድና እኩል አድርጎ የሚቀልባቸው "ጉዲፈቻ" እና "ሞጋሳ" የተሰኙ የራሱ ማኅበራዊ ሕጎችና ሥርዓቶች ነበሩት።

ይህ በሕዝባዊ የገዳ፥ የጉዲፈቻና የሞጋሳ ድርጅቶች፥ ተቋማትና ሥርዓቶች የሚመራ የኦሮሞ አዋማዊ ሕዝብ በግምት ከ1520ዎቹ እስከ 1620ዎቹ ድረስ በአንድ ምዕተ ዓመት ዘመን ውስጥ በርቱማና ቦረና በተባሉ ሁለት ጎሳዎችና ከረዩ፥ ወሎ፥ ቱላማና ሚጫ በተባሉ አራት ቅርንጫፍ ማኅበረሰቦች ተከፍሎ በፍልሰት እንቅስቃሴ በደቡብ ምስራቅ ከገናሌ ወንዝ አካባቢ በመነሣትና በአብዛኛው የዛሬ ደቡብ፥ ምስራቅ፥ መሀልና ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ላይ በመስፋፋት ብሎም በተጠቀሱ አካባቢዎች ከጥንቱ ነባር ኩሻዊ፥ ሴማዊና ኦሞአዊ የባሌ፥ የደዋሮ፥ የአዳል፥ የሀዲያ፥ የፈጠጋር፥ የወርጂ፥ የሀርላ፥ የሶማሌ፥ የአፋር፥ የአርጎባ፥ የይፋት፥ የአማራ፥ የአገው፥ የትግሬ፥ የጋፋት፥ የአይመላል፥ የጉራጌ፥ የዳሞት፥ የቦሻ፥ የእናሪያ፥ የቢዛሞ ... ሕዝቦች አገሮችና መንግሥታት ጋር በሥፍራና በጊዜ፥ በጦርነት፥ በጋብቻ፥ በቋንቋ፥ በጎሳ፥ በባህል፥ በሃይማኖትና በሥርዓት በመወራረስ በአጭር የታሪክ ዘመን ውስጥ ከሥፍራና ከቁጥር አኳያ የኢትዮጵያ ትልቁ ማኅበረሰብ ለመሆን በቃ። በአገሪቱ የተለያዩ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች መካከል ባህላዊ መስተጋብርና መወራረስ ፈጠረ።

በዚህ መሠረታዊና ዘላቂ በሆነ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች የመስተጋብርና የመወራረስ ሁኔታና ሂደት ማለትም የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ብዙትና አንድነት ጉዳይ በሚመለከት በአገሪቱ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በአንድ ምዕተ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ (1520-1620) የአዋማዊ ኦሮሞ የገዳ ሕዝባዊ ሥርዓትና እንቅስቃሴ ያደረገውን ታላቅ አስተዋጽኦ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በ1000 ዓመታት፥ የክርስትና ሃይማኖት በ1670 ዓመታት፥ የእስልምና ሃይማኖት በ1300 ዓመታት እንዲሁም ሰለሞናዊ የአማራ ሥርወ መንግሥት በ700 (1270-1974) ዓመታት ዘመን አላደረገም። ምክንያቱም ለምሳሌ በኢትዮጵያ የ1994 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገሪቱ

ሕዝብ አንድ ሶስተኛ የኦሮሞ ቋንቋ ማኅበረሰብ አባል ነው። ከዚህም ሕዝብ በሃይማኖት ግማሹ ክርስቲያን ግማሹ ደግሞ እስላም እንደሆነ የቆጠራው ውጤት ጨምሮል ያሳያል።

በኢትዮጵያ በሀውርታዊ ኅብረተሰብና መንግሥት በቀድሞ ዘውዳዊ ሥርዓት (1855-1974) ማዕከላዊ ርዕሰ ጉዳይ ሁለአቀፍ የመሬት፣ የብሔረሰብ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የባህል፣ የትምህርትና የመንግሥት ሥልጣን ችግር ነው። የችግሩ ታሪካዊ መነሻና ዕድገት በ16ኛው ምዕተ ዓመት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ከሁለቱ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ተዛማጅና ተከታታይ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ የአመጽ ጦርነትና የ1520-1620 ታላቁ የሕዝቦች የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴ ጥምር ታሪክ ጋር በቅርብና በጥብቅ የተያያዘ የጭቆና ሥርዓት ነው።

በዚህ አኳያ በግምት ከ1270 እስከ 1543 ድረስ ከመሀል ሰሜኑ ደጋአምባ ክርስትቲያን ነገሥታትና የሃይማኖት መምህራን ከግብፅ አቡኖች ጋር የመላ ደቡብ ኢትዮጵያ አዋማዊና እስላማዊ ነባርና ጥንታዊ ሕዝቦችንና መንግሥታትን በሰፋሪ ወታደሮችና ቄሶች አማካይነት በክርስትና ሃይማኖት ለመግዛት ለሶስት ምዕተ ዓመታት ያካሄዱት ወታደራዊና ወንጌላዊ ዘመቻዎች ሁሉ በመጨረሻ በሁለቱ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ የአመጽ ጦርነትና የ1520-1620 የሕዝቦች የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴ ግፊት በሽንፈትና በውድቀት ተደመደሙ።

በሌላ በኩል ግን በሁለቱ የክርስቲያንና የእስላም ተፃራሪ መንግሥታት የጋራ ሽንፈትና ውድቀት በግምት ከ1559 እስከ 1855 ድረስ ከደቡብ ምስራቅ ቆላማ አካባቢ በተሳካ የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴ የተነሱ የኦሮሞ አራቱ የከረዩ፣ የወሎ፣ የቱለማና የሜጫ ማኅበረሰቦች በየፊናቸው በአብዛኛ የምስራቅ፣ የደቡብ፣ የመሀል፣ የምዕራብና የሰሜን ኢትዮጵያ ለሰውና ለእንስሳት ኑሮ ምቹ በሆኑ ሰፊ፣ ለም፣ ደጋማና ጤናማ አካባቢዎች በነዋሪነት ሰፈሩ።

በአንጻሩ በ16ኛው ምዕተ ዓመት ሁለቱ የክርስቲያንና የእስላም መንግሥታትና ሥርዓቶች በውስጥና በውጭ ተፃራሪ ሁኔታዎችና ኃይሎች ግፊት ከፈረሱ በኋላ በግምት ከ1600 እስከ 1855 ድረስ በሰሜኑ ደጋአምባዎች ሶስቱ ክርስቲያናዊ የጎንደር፣ የትግራይና የሸዋ የፖለቲካ ኃይሎች፣ ማዕከላትና አካባቢዎች በአዋማዊ፣ በኦሪታዊና በእስላማዊ ሕዝቦች ዙሪያና መካከል ተከሰቱ።

የሶስቱ የጎንደር፣ የትግራይና የሸዋ ክርስቲያናዊ የመሳፍንት፣ የካህናት፣ የባላባትና የጦር ኃይሎች የጋራ ዓላማ፣ ፖሊሲ፣





ፖለቲካና ተግባር በአንድ በኩል በየአካባቢያቸው አዋማዊ፣ ኦሪታዊና እስላማዊ ነባር ሕዝቦችን በጦርና በገባር ሥርዓት ማስገበርና መግዛት በሌላ በኩል ደግሞ በ16ኛው ምዕተ ዓመት በእስላሙ "ግራኝ ወረራ" እና በአዋማዊ "የጋላ ወረራ" ፈረሰ፣ ጠፋ፣ የሚሉትን ዘውዳዊ የአፄ መንግሥት «መልሶ» በተጠቀሱ «ጠላት» ሕዝቦች ላይ መገንባት ነበር።

ይህ የጎንደር፣ የትግራይና የሸዋ ክርስቲያናዊ ኃይሎች ዘውዳዊ የክርስቲያን ኅብረተሰብ፣ መንግሥትና ሥርዓት የመገንባት ቶች ፖሊሲና ፕሮግራም በ19ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ (1855-1900) ከሶስቱ አካባቢዎች በተከታታይ በተነሱ አፄ ነገሥታት ቴዎድሮስ፣ ዮሐንስና ምኒልክ አመራርና በውጭ ኃይሎች የመሣሪያ እና የፖለቲካ ድጋፍ እንደሚከተለው ተግባራዊ ሆነ። መጀመሪያ በመሀል ሰሜኑ ደጋአምባ ከጎንደርና ከትግራይ በተከታታይ የተነሱ አፄ ነገሥታት ቴዎድሮስና ዮሐንስ በአካባቢው ከ16ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ለረጅም ዘመን በነበረው ተዛማጅ የጂኦ-ፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የፀጥታና የማኅበራዊ ችግር ምክንያት በዘውዳዊ ምዕክልና ፖሊሲና ፕሮግራም በክፍለ አህጉሩ እስላማዊና አዋማዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ የክርስቲያን መንግሥት ለመገንባት የጀመሩትን ዘመቻ ከግቡ ሳያደርሱ በ1868 እና በ1889 በቅደም ተከተል በመቅደላና በመተማ ጦርነቶች ሞቱ።

በመሀል ሰሜኑ ደጋአምባ በሁለቱ ነገሥታት የተጀመረው የክርስቲያን መንግሥት ግምባታ ፖሊሲና ፕሮግራም ከፈረሰ በኋላ አፄ ምኒልክ (1889-1913) ከሸዋ እስትራቴጂያዊ ክልል በመነሳት በአንድ በኩል የደቡብ ኢትዮጵያን ታላቅ የሰውና የተፈጥሮ ሀብት በመቆጣጠር በሌላ በኩል ደግሞ ከአውሮፓውያን ከፍተኛ የጦር መሣሪያና የፖለቲካ ድጋፍ በማግኘት በክፍለ አህጉሩ አዋማዊና እስላማዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ ዘውዳዊ የክርስቲያን መንግሥት፣ ሃይማኖትና ጦር በጠንካራ የገባር ኢኮኖሚ መሠረት በሰፋሪ ነፍጠኞችና ቄሶች ኃይል በደቡብ ኢትዮጵያ ማዕከልነት መርተው ሞቱ።

ነገር ግን በኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብ በተጠቀሱ የጎንደር፣ የትግራይና የሸዋ ክርስቲያን ነገሥታትና የጦር ኃይሎች ፖሊሲና ተግባር በኅብረተሰቡ ላይ የተማከለው ዘውዳዊ መንግሥትና ሥርዓት በአገሪቱ ለተዛማጅና ሁለአቀፍ የመሬት፣ የብሔረሰብ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የባህል፣ የሥርዓት፣ የትምህርትና የመንግሥት ሥልጣን ችግሮች

ታሪካዊ መነሻና ምክንያት በመሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ በአንድ በኩል የራሱን የዘውዳዊ መንግሥትና የገዥ መደብ ውድቀት በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ነፃነትና እርነት እንዴት እንዳስከተለ ይህ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች የታሪክ ዕውነታ፣ እውቀትና እውነት ያስተምራል።

በመጽሐፉ አራተኛ ክፍል «የእስላም ሃይማኖትና መንግሥት መነሻና ዕድገት በኢትዮጵያ 615-1300» በሚል ርዕስ፣ በአምስተኛ እና በመጨረሻ ክፍል ደግሞ «የኢትዮጵያ የሕዝቦችና የመንግሥት ረጅም የስያሜ ታሪክ» በሚል ርዕስ በአገሪቱ ረጅም ታሪክ ተገቢ አገራዊና ሕዝባዊ ትኩረትና ግንዛቤ ያላገኙ ሁለት መሠረታዊ ርዕስ ጉዳዮች ለመነሻ ያህል በአጭርና በጥቅል መልኩ ተገልጸዋል።

*የሰሜን/ፈላሻና የሙስሊም ሕዝቦች ታሪክ ጥናትና ግንዛቤ*

በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት በዝርዝር እንደሚታየው፣ ባለፉት 700 (1270-1974) ዓመታት የግብፅና የአውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖት፣ የቋንቋና የሥነ ጽሑፍ ጸሐፊዎች፣ አስተማሪዎችና ተርጓሚዎች ከኢትዮጵያ ሰለሞናውያን ተከታዮቻቸውና ተማሪዎቻቸው ጋር ባሳደሩት የተረት፣ የሃይማኖትና የፖለቲካ ተጽዕኖ ምክንያቶች የአገሪቱ ኦሪታዊ የሰሜን/ፈላሻና ጥንታዊ የሙስሊም ሕዝቦችና ሃይማኖቶች ታሪክ በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብና መንግሥት ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ ከሞላ ጎደል ሳይታወቅ ኖሯል። በመሆኑም አሁን የሁለቱም ሕዝቦችና ሃይማኖቶች ረጅም የመነሻ፣ የማንነትና የጭቆና ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች ታሪክ ከተቀረው የአገሪቱ አጠቃላይ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ጋር በሕዝባዊ የአገር ቋንቋና ባህል ከብዙ ጥንታዊና ዘመናዊ የሰነድ መረጃዎች ተጠንቶ ለኅብረተሰቡ ትምህርታዊ ግምገማ፣ ግንዛቤና አገልግሎት ከሥር ከመሠረቱ ቀርቧል።

ከእውነትና ከእውቀት አኳያ፣ የሁለቱ ሕዝቦችና ሃይማኖቶች ታሪክ በዚህ ጥናት እንደቀረበው ለአንባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ እውነተኛ ታሪክ መስሎ ባይታይ አያስገርምም። ታሪኩ ግን እውነተኛ ነገር ብቻ ሳይሆን ባለፉት 700 ዓመታት በቀድሞ ዘውዳዊ ሥርዓት የተቀሩ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦችና ሃይማኖቶች ታሪክ ዓይነተኛ ምሳሌ፣ ማስረጃና መግለጫ እንደሆነ ከዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ በስፋትና በዝርዝር ይታያል።





የታሪኩን ጥንትና ትምህርት በሚመለከት፣ ኦሪታዊ የሰሜን/ፈላሻ ረጅም (300-1990) የጦርነትና የስደት ታሪክ የተገኘው ከኢትዮጵያ ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፎችና ከሰለሞናዊ ነገሥታት ዜና መዋዕሎች ሲሆን፣ የሙስሊሞቹ ታሪክ ደግሞ ከአረብ ምንጮች፣ ከኢትዮጵያ ጥንታዊ የሐረር ከተማ መንግሥት ሰነዶችና ከሰለሞናዊያን ነገሥታት ዜና መዋዕሎች ነው።

የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግሥት በግምት ከ300 እስከ 1632 ድረስ ለ1300 ዓመታት በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በተከዜና በዓባይ ወንዞች መካከል ባለው ለምና እስትራቴጂያዊ አገር ላይ ከአካባቢው ተከታታይ የአክሱም፣ የአገውና የአማራ መንግሥታትና ነገሥታት ጋር እየተዋጋ በሉአላዊ ነፃነት እንደኖረ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል። ነገር ግን በመጨረሻ በ1580-1632 የሰሜን/ፈላሻ መንግሥት በጠላቶቹ እጅ በዘመናዊ የንፍጥና የመድፍ መሣሪያዎች ሊደመሰስ፣ ሕዝቡ ከመሬቱ ተነቅሎ በ1980ዎቹ ከአገሪቱ እስኪሰደድ ድረስ ለአራት ምዕተ ዓመታት እንዴት ለአጎራባች ሕዝቦች የዕደ ጥበብ አገልጋይ ማኅበረሰብ እንደሆነ በጥናቱ በዝርዝር ተገልጿል።

በዚህ ጥናት የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ታሪክ ከሥር ከመሠረቱ በስፋት እንዳጠና ብርቱ ግፊትና ንቃት የሰጠኝ፣ ባለፉት አሥርታት የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብ፣ መንግሥትና ታሪክ መነሻ ክስተትና ዕድገት በማስረዳት በልዩ ልዩ መንገዶች፣ መድረኮችና መሣሪያዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ያስተማርኩትን ትምህርት በሚመለከት ከአገሪቱ የሙስሊም ኅብረተሰብ በአጠቃላይ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ከጥንታዊ የሀዲያ፣ የስልጤ፣ የአላባ፣ የቀቤና፣ የሐረሪ፣ የአርጎባ፣ የወርጂ፣ የአፋርና የሱማሌ ሙስሊም ማኅበረሰቦችና ተወላጆች በተለይ የተገኘ ከፍተኛ የሞራል ድጋፍና ትብብር ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር ከ896 ማለትም ገና ከዘመነ አክሱም ጀምሮ እስከ 1600 ድረስ በደቡብ ኢትዮጵያ በአዋሽ፣ በከሰም፣ በሙገር፣ በዓባይ፣ በጊቤ፣ በብላቴ፣ በዋቤና በገናሌ ወንዞች ተፋሰስና ወይናደጋ ክልል በጥንታዊ አጎራባች የሐርላና የሀዲያ ሴማዊና ኩሻዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ምድር በአረቡ የሙስሊም ዓለም፣ የዜይላ ሕብረት መንግሥታት ተብለው የሚታወቁ እስላማዊ የሸዋ፣ የሀዲያ፣ የይፋት፣ የወርጂ፣ የገባል፣ የአዳል፣ የሞራ፣ የለበከላ፣ የሀገራ፣ የፈድሳ፣ የግዳድ፣ የነገብ፣ የዚባ፣ የሐርላ፣ የሁብት፣ የተርሳ፣ የእይም፣ የእልብሮ፣ የዜይላ፣ የእስቴ፣ የደዋሮ፣ የመንዝ፣ የዜጋ፣ የኩልጎራ፣ የገደያ፣ የቀድሴ፣ የሀርጋይ፣ የበቁልዘር፣ የፈጠጋር፣

የአርጎባ፥ የሸርካ፥ የአረባቢኒ፥ የባሌ፥ የደራ፥ የሐረር፥ የጉራጌ፥ የስልጤ፥ የአውሳ ... ሕዝቦች፥ አገሮች፥ መንግሥታትና ከተሞች እንደነበሩ ከታሪክ መረጃና ትምህርት በሥፍራና በጊዜ ቀመር በትክክል ታውቋል።

ከ896 እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ የሙስሊም መንግሥትና ሥልጣኔ ታሪክ ግንዛቤና ትምህርት በሚመለከት፥ በአካባቢው በተለይ በጥንታዊ የሐርላ ለም፥ ደጋማና ጤናማ ምድር ላይ፡-

1ኛ፥ በ896-1285 ከአረቢያ በዜይላ የወደብ በር በገባው መኽዙማዊ የቁረይሽ አረብ ሥርወ መንግሥት የተገነባው የሸዋ ሱልጣኔት፤

2ኛ፥ በ1285-1415 ከአረቢያ በዜይላ የወደብ በር በገባው የሃይሺማይት፥ ዋላስማ የቁረይሽ አረብ ሥርወ መንግሥት የተገነባው የይፋት ሱልጣኔት፤

3ኛ፥ በ1415-1577 የሃይሺማይት፥ ዋላስማ ሥርወ መንግሥት የተገነባው የአዳል ሱልጣኔት፥ በ1524-1543 በሐረርና በደምቢያ ማዕከላት የኢማም አሕመድ ክፍለ አህጉራዊ የአዳል ሱልጣኔት፥ በ1544-1567 የኤሚ፤ ኑር የሐረር ኤሚሬትና ጀጎል ግምብ፤

4ኛ፥ በ1577-1647 በኢማም አሕመድ ተወላጅና ወራሽ ኢማም መሐመድ ጃሳ የተገነባው የአውሳ ኢማሜት፤

5ኛ፥ በ1577-1887 በኢማም አሕመድ ተወላጅና ወራሽ ኢማም መሐመድ ጃሳ የተመሠረተው የሐረር ኤሚሬት፤

በ1647-1662 በሐረር ኤሚሬት የኤሚር ዓሊ ዳውድ አመፅ በአውሳ ኢማሜት ላይ ብሎም የነፃ ሐረር ኤሚሬት (ከተማ መንግሥት) ክስተትና ዕድገት (1647-1887)፤

6ኛ፥ በ1887-1994 የሐረር ኤሚሬት (ከተማ መንግሥት) ውድቀት በኢትዮጵያ ግዛተ አፄ፤

7ኛ፥ በ1994 በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ሥር የሐረሪ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ክስተት በቅደም ተከተል የሚቀርቡ ታላላቅ ታሪካዊ ምዕራፎች፥ ኃይሎች፥ እንቅስቃሴዎችና ዘመናት ናቸው።

ባጭሩ ከ896 ጀምሮ ለአራት ምዕተ ዓመታት በደቡብ ኢትዮጵያ በአጎራባች የሐርላና የህዲያ አገሮች የእስላም ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ሥርዓት ካደገና ከተስፋፋ በኋላ በ1270 በሰሜኑ ደጋአምባ ማለትም በላስታ የአገውን የክርስቲያን መንግሥት በአመፅ ገልብጦ የተነሳውና ራሱን በኢትዮጵያ ሰለሞናዊ ዘር ነኝ ብሎ የሰየመው ሥርወ መንግሥት ነገሥታት በተጠቀሱ የእስላም ሕዝቦችና





መንግሥታት ላይ እስከ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ የአመፅ ጦር ነት ድረስ ለሶስት ምዕተ ዓመታት የሚቆየውን ሁሉአቀፍ የመሬት፥ የግዛት፥ የንግድና የሃይማኖት ጦርነት ጀመሩ።

ነገር ግን በ16ኛው ምዕተ ዓመት የኢትዮጵያ ሁለቱም የክርስቲያንና የእስላም ተፋላሚ መንግሥታት፥ ነገሥታትና የጦር አበጋዞች በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ከአሬታዊው የሰሜን/ፈላሻ ጥንታዊ መንግሥት ጋር በሁለቱ ተዛማጅና ተከታታይ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ የአመፅ ጦርነትና የ1520-1620 ታላቁ የሕዝቦች የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴ ግፊት በየአካባቢያቸው ተሸንፈው እንዴት እንደወደቁ ብሎም በሂደቱ የእስልምና ሃይማኖት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ደረጃ እንዴት የበለጠ እንደተስፋፋ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መገለጫዎች ይዘት፥ ሂደትና ትምህርት በዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ በስፋትና በዝርዝር ያሳያል።

በመጨረሻም በዚህ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መገለጫዎች፥ የኢትዮጵያ የእስልምና ሃይማኖት ጥናትና ትምህርት በሚመለከት፥ ከአረቢያና ከሐረር ከተማ መንግሥት ከተገኙ የመረጃ ምንጮች ቀጥሎ ለጥናቱ ፍሬና ምርት የግንዛቤ፥ የትምህርት፥ የመረጃ፥ የሙያ፥ የቴክኒክ፥ የምክርና የሞራል እገዛና አስተዋጽኦ ያደረጉ የኢትዮጵያ ድርጅቶችና ዜጎች ብዙ ናቸው።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በተለይ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትና የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ?ዕርዳታና ልማት ማኅበር በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ህዝቦችና ሃይማኖቶች ኅብረተሰብና መንግሥት ታሪክ ውስጥ የሙስሊም ኅብረተሰብ ሃይማኖትና ታሪክ ጥናቴን ሰምተውና አይተው በየበኩላቸው ላሳዩኝ መልካም አመለካከትና ለሰጡኝ የትምህርትና የሞራል ድጋፍ ምስጋናዬ የላቀ ነው። ወዳጄ አቶ ወሂብ መሐመድ ቱሬ በኢትዮጵያ ረጅም የሙስሊም ሥልጣኔና ታሪክ ታላቅ ማዕከላዊ ሥፍራና ሚና ያለውን የሐረሪ ከተማ መንግሥትና ኅብረተሰብ ሕያው ታሪክ ከጀጎል ምንጩና መስኩ ለማጥናትና ለማወቅ ባደረግኩት ጥረት በመልካም አስተያየቱና ተግባሩ ታላቅ ትምህርታዊ ግፊትና ግንዛቤ እንደሰጠኝ ስገልፅ በታላቅ ደስታ ነው። እንዲሁም ይህን መጽሐፍ በታላቅ ትግሥትና ትጋት በኮምፒዩተር በማቀነባበር አቶ ሙክታር አሕመድ ዓላም ለጥናቱ መሳካትና አገልግሎት የራሱን ልዩ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ከታላቅ ምስጋና ጋር እገልፃለሁ። ከሁሉም በላይና በፊት በዚህ ረጅምና አስጨናቂ የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት የባለቤቴ ሽቶ ግርማና የልጆቼ ፀጋነሽ፥ ትዕግሥትና ዝናሽ የቤተሰብ

ተሳትፎና ወሳኝ አስተዋጽኦ ሳይገለጽና ሳይታወቅ የማይታለፍ ነው። ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፥ በዚህ መጽሐፍ የቀረበው የኢትዮጵያ ታሪክ የጥናት ሥልት ሆነ ትምህርትና ትርጉም የኔ የራሴ ብቻ ነው።

ላ. ጌ. ድ.
ሴፕቴምበር 1998
አዲስ አበባ





# ክፍል አንድ

## የኢትዮጵያ ታሪክ ግምገማና ትንተና

### 1. ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን

ከእንቅስቃሴና ከህልውና አኳያ፥ ሥፍራና ጊዜ የመኖርና የመሆን ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። በዚህ ረገድና ተግባር፥ በዓባይ ሸለቆ፥ በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ የሚዋሰነው እስትራቴጂያዊ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ተዛማጅ ኩሻዊ፥ ሴማዊ፥ ናይሎ-ቲካዊና ኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች የመኖሻ ምድር ነው። ይህ የክፍለ አህጉሩ ወሰን በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያ የሚለው የአገር ስያሜ ሰፋ ያለ አካባቢን የያዘ መሆኑን የሚገልጽ ታሪካዊ ማብራሪያ ነው።

የኢትዮጵያ በህውርታዊ (multinational) ሕዝብ ታሪካዊ መነሻና ማንነት በሚመለከት ደግሞ፥ ዘመናዊ ሥነልሳን (የሊንጉዊስ ቲክስ ሳይንስ) እንደሚያስተምረው፥ የሦስቱ ጥንታዊና አጎራባች የአፍሪካ፥ የእስያና የአውሮፓ አህጉራት ነባር ሕዝቦች ዛሬ የአፍሮ-እስያ እና የኢንዶ-አውሮፓ የቋንቋ ቤተሰቦች ተብለው በሁለት ታላላቅ የቋንቋ ግንዶችና ምንጮች ይከፈላሉ።[1]

ከሁለቱ የዓለም የቋንቋ ግንዶችና ምንጮች፥ የአፍሮ-እስያ የቋንቋ ቤተሰብ ራሱ የቻድ፥ የበርበር፥ የግብፅ፥ የኩሽ፥ የሴም፥ የኦሞና የናይሎሳሃራ በተሰኙ ንኡስ የቋንቋ ዘርፎች ይከፈላል። ከተጠቀሱት ቅርንጫፍ የቋንቋ ዘርፎች፥ ኩሻዊና ሴማዊ ቋንቋዎች በአመዛኙ፥ ኦሞአዊ ቋንቋዎች በሙሉ፥ ናይሎሰሃራዊ ቋንቋዎች በከፊል የሚገኙት በኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ ምድር ነው። በሊንጉዊስቲክስ ሳይንስ መሠረት፥ የተጠቀሰው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በህውርታዊ ብዛትና ግንኙነት ሁኔታ ለቋንቋዎቹ አካባቢያዊ መነሻና ጥንታዊነት ታሪካዊ ማስረጃና መግለጫ ነው።[2]

---

[1] Martin Bernal, Black Athena - The Afroasiatic Roots of Classical Civilization: Volume I: The Fabrication of Ancient Greece 1785-1985 (Rutgers, 1987), Maps and Charts, pp. XXIV-XXVII, 11-14; J. H. Greenberg, African Linguistic Classification, UNESCO, General African History, 8 Vols. (1981), I, pp. 92-308; M. L. Bender, The Ethiopian Nilo-Saharans, (1975).

[2] Martin Bernal, "ጉራጊኛ የግዕዝ እያት ነው"፥ እፎይታ፥ ቅ 5 ቁ 40 (1989)፥ ገፅ 11።

በተጨማሪም፥ በቅርቡ በአካባቢው በተገኙ የአርኪኦሎጂና የፖሌኦንቶሎጂ (archaeology and paleontology) መረጃዎች የኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች በሀውርታዊነትና ጥንታዊነት የበለጠ ተረጋግጧል። ከዚህ አኳያ ባለፉት 200 ዓመታት በኢትዮጵያ፥ በአረቢያ፥ በሱዳንና በግብፅ አጎራባች አገሮች፥ በአምሳ ከሚቆጠሩ ታሪካዊ ሥፍራዎች፥ በአራቱ ጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎች በ500 የሚቆጠሩና በድንጋይ ላይ የተጻፉ ጽሑፎች ከከርሰ ምድር በአርኪኦሎጂ ጥናትና ምርምር ተገኝተዋል። በነዚህ ጽሑፎች መሠረት፥ የግዕዝን ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት ጨምሮ፥ የኢትዮጵያን ጥንታዊ የደአማት-አክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ የፈጠሩት፥ በቅርቡ ዘመን የአውሮፓ ምሁራን እንደገመቱት ከእስያ ክፍለ አህጉር ወደ ኢትዮጵያ ገቡ የተባሉት የውጭ ኃይሎች ሳይሆኑ፥ የአገሪቱ ነባርና ጥንታዊ የአፍሪካ ሕዝቦች ናቸው።[3]

ይህም ብቻ አይደለም። በቅርቡም በ20ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ አሥርታት ውስጥ፥ በአርኪኦሎጂ ቁፋሮ በተገኙ የፖሌኦንቶሎጂ መረጃዎች (ጥንታዊ የቅድመ ታሪክ የአጥንትና የድንጋይ መሣሪያዎች) በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደተረጋገጠው፥ የሰው ልጅ ራሱ በሀልውናዊ አካሉና አእምሮው አድጎና ዳብሮ በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተው ከዛሬ ብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ በታላቁ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ በኢትዮጵያ የአዋሽ-ኦሞ ወንዞች ምድር ነው።[4] ከዚህ ከኢትዮጵያ የስምጥ ሸለቆ፥ የሰው ልጅ መነሻው ምድር፥ የዓለም የአፍሮ-እስያና የኢንዶ-አውሮፓ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች፥ በግምት ከዛሬ ዘጠኝና አሥር ሺህ ዓመታት በፊት በፍለሳና በሰፈራ እንቅስቃሴ በአፍሪካና በእስያ አጎራባች አህጉራት ላይ እንዴት እንደተሰራጩ የሊንጉዊስቲክ ሳይንስ ምሁራን እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፥ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) አሁን በይፋ ያስተምራሉ።[5]

---

3 A. J. Drewes, Inscriptions de L'Ethiopie Antique (1962); R. Schneider, "Les Debuts de L'Histoire Ethiopienne" Documents Histoire Civilisation Ehiopienne, RCP. 230, CNRS, FASC. 7 (1976); E. Bernand; J. A. Drewes, R. Schneider et F. Anfray, trs. and eds., Recueil des Inscriptions de L'Ethiopie des Periodes Pre-Axoumite et Axoumite (Forthcoming).


4 Bernal, Black Athena, pp. 11; UNESCO, History of Africa, I. pp. 300-301.

5 Ibid., Black Athena, pp. 11-14; G. Hudson, "Language Classification and the Semitic Pre-History of Ethiopia", Folia Orientalia, Vol. 18 (1977), pp. 119-166; Ibid., "Geolinguistic Evidence for Ethiopian Semitic Pre-History", Abbay, No. 9 (1978), pp. 71-85.





## የዓለም ቋንቋዎች መነሻና ስርጭት




Source: M. Bernal, Black Athena (1987) Vol. 1, p. XXVI.

በዘመነ-ታሪክ፣ ባለፉት ዘጠኝና አሥር ሺህ ዓመታት ውስጥ፣ በዓባይ ሸለቆ፣ በሜዲትራኒያን ባሕር፣ በመካከለኛው ምስራቅና በአረቢያ ጥንታዊና አጎራባች አካባቢዎች፣ በየዘመናቸውና በየአካባቢያቸው የተነሱት ጥንታዊ የግብፅ፣ የይሁዲ፣ የግሪክ፣ የሮም፣ የፋርስና የአረብ ተከታታይ ሕዝቦችና መንግሥታት በተለይ በንግድ፣ በሃይማኖትና በባህል መንገዶችና መስኮች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ታሪካዊና እስትራቴጂያዊ ክፍለ አህጉር ከኢትዮጵያ ነባር ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር የመስተጋብርና የመወራረስ ሁኔታዎች፣ እንቅስቃሴዎችና ሂደቶች እንደነበሩዋቸው በየወቅቱ በጥንታዊ የግብፅ ሃይሮግላፊክስ፣ የዕብራይስጥ፣ የደአማት፣ የሳባ፣ የግዕዝ፣ የግሪክ፣ የላቲን፣ የኮፕቲክ እና የአረብ ቋንቋዎች ተጽፈው የተገኙ የታሪክ መረጃዎች ያሳያሉ።

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ታሪካዊ መነሻና ስያሜ በሚመለከት፣ ከተጠቀሱት ጥንታዊ የአካባቢው ሕዝቦች በተለይም ሁለቱ ግብፃውያንና ይሁዳውያን- «ፑንት»፣ ግሪኮች- «ኢትዮጵያ»፣ አጎራባች አረቦች ደግሞ «ሀበሻ» በተሰኙ የአገርና የሕዝብ ስሞች እንደሚጠሩ ከታሪክ መረጃና ትምህርት ታውቋል።

ከዚህ አኳያ ከ330 እስከ 615 ድረስ በ285 ዓመታት ውስጥ በግሪኮ-ሮማውያንና በአረብ አስተማሪዎች አማካይነት ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁርአን ጋር ወደ አክሱም አገርና ቤተ መንግሥት የገቡት ሦስቱ የዓለም መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስትና፣ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች በአንድ ላይ ባለፉት 1700 ዓመታት ውስጥ በየፊናቸውና በየአካባቢያቸው የእምነት፣ የድርጅትና የትምህርት መሠረቶች፣ መሣሪያዎችና ምክንያቶች በመሆን ለኢትዮጵያ ጥንታዊ እና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገር፣ ኅብረተሰብና መንግሥት ህልውናዊ ክስተትና ዕድገት ድምር አስተዋፅኦ እንዳደረጉ በዚህ ጥናት፣ ይዘትና ሂድት በስፋት ይታያል።





# 2. የኢትዮጵያ በህውርታዊ ታሪክ መነሻና ዕድገት

## የኢትዮጵያ ታሪክ የመነሻና የባለቤት ጥያቄ

እንግሊዛዊው ታዋቂ የታሪክ፣ የቋንቋና የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር ፕሮፌሰር ማርቲን ቤርናል፣ *Black Athena: The Afroasiatic Roots of Classical Civilization (1897)* በተሰኘው ጥናቱ እንዲሁም በቅርቡ በአዲስ አበባ ተገኝቶ «የአውሮፓ ሥልጣኔ ምንጭ አፍሪካ ናት» በሚል ርዕስ ከእፎይታ መጽሔት ጋር ባካሄደው ትምህርታዊ ቃለ ምልልስ፣ በ18-20ኛ ምዕተ ዓመታት የምዕራቡ ክርስቲያን ምሁራን፣ በጀርመኑ የቋንቋ፣ የታሪክና የሃይማኖት ፈላስፋዎች አመራር፣ በአፍሪካና በእስያ ጥንታዊ ሕዝቦች ላይ የነጭ አውሮፓውያንን የዘርና የባህል በላይነት ለመገንባት ባካሄዱት ትግል የዘረኝነት እምነትና ትምህርት ፈጥረው፣ በአውሮፓና በአሜሪካ እንዳስፋፉት፣ ብሎም በሂትለሩ ጀርመን በይሁዳውያን ላይ ለተካሄደው የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዴት የፖለቲካ መሠረት፣ መንገድና ምክንያት እንደፈጠሩ አሳይቷል።

ከፕሮፌሰሩ ጋር የተካሄደውን የቃለ ምልልስ ይዘትና ትምህርት አስመልክቶ የመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል እንደገለጸው፣

«በዚህ እትማችን ለየት ያለ ታሪክ ይዘን ቀርበናል። እውቁ እንግሊዛዊ ፕሮፌሰር ማርቲን ቤርናል ያልተለመደ የታሪክ ምልከታ አድርገዋል። አዲስ የታሪክ ሃሳብም አቅርበዋል። «የኢትዮጵያ የሴም ቋንቋዎች አባት ግዕዝ ነው» የሚለውን ሽረውታል። «ጉራግኛ የግዕዝ አያት ነው» ብለውታል። ያልተለመደ ነው። የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች ከደቡብ አረቢያ መጡ ሲባል ነበር። ይህ አስተሳሰብ እስካሁን ድረስ ተቀባይነት አግኝቶ ቢቆይም በፕሮፌሰሩ ዘንድ ግን ሥፍራ ያለውም። እስካሁን ሲታመንበት የቆየውን የሴም ቋንቋዎች ከደቡብ ኢትዮጵያ ካሉ ቋንቋዎች ቀደምትነት አላቸው የሚለውን ሙሉ በሙሉ ያናጋል። ለዘመናት በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች የሚሰጠውን የታሪክ ትምህርትም የሚገለባብጥ በመሆኑ የክርክር እሳት ለኩሰዋል ፕሮፌሰሩ - ጥልቅ ንባብን ይጠይቃል።»[6]

በመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል አስቀድሞ እንደተገመተውም የፕሮፌሰሩ ትምህርት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከፍተኛ ክርክር ማስነሳቱ አልቀረም። ይህንንም በሚመለከት እፎይታ መጽሔት በሐምሌ 1989

[6] እፎይታ፣ ቅ.5 ቁ.10 (ሐምሌ 1989) ገፅ 2።

እትሙ፣ «ፕሮፌሰር ማርቲን ቤርናል የተባሉ ምሁር ሁለት አከራካሪ ሐሳቦች አቅርበው ነበር። አንደኛው ሐሳብ የአውሮፓ ሥልጣኔ ምንጭ አፍሪካ ናት የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ሐሳብ ደግሞ የጉራግኛ ቋንቋ ከግዕዝ ቋንቋ ቀደምትነት አለው የሚል ነው። ሁለተኛው ሀሳብ በተለይ ከፍተኛ ክርክር አስነስቷል። ሀሳቡ ደጋፊዎችም ተቃሚዎችም አሉት። በሁለቱም ሀሳቦች ላይ ያላቸውን ሙያዊ አስተያየት እንዲሰጡን በታሪክ ምሁር የሆኑትን ዶክተር ላጵሶ ጌ. ድሌቦን ጋብዘናል»[7] በማለት የግንዛቤ ጥያቄ አቅርቧል።

ይህን የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ ታሪክ መነሻና ባለቤት በተመለከተ ከእፎይታ መጽሔት ዝግጅት ክፍል በቀረበው ጥያቄ መሠረት የሰጠሁት ማብራሪያ የዚህ ኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች ጥናት አካል ስለሆነ እንደሚከተለው ቀርቧል።

## የኢትዮጵያ ሕዝቦች መጤዎች አይደሉም

ጉዳዩ አንገብጋቢና ወቅታዊ ነው። ጥያቄውም የማንነት ጥያቄ ነው። አንድ ሕዝብ፣ አንድ ሀገር፣ አንድ ባህል የራሱ የሆነ ሕይወት አለው። መነሻ አለው። ከሁሉም በላይ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በሕዝብነታቸው፣ ዜጎችም በዜግነታቸው የማንነት ጥያቄ አንስተዋል። የሀገርን ምልክት፣ የሀገርን ማንነት፣ የሀገርን መሠረት ማንሳት የአንድ ሕዝብ የዕድገትና የማንነት መነሻ ነው። እስከዛሬ ድረስ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የተሳሰረ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጸው ሰው ሁሉ ከመካከለኛው ምስራቅ እንደ ተገኘ ነው። ምዕራቡ አለምም ያንን እምነት ተቀብሎ ያስተጋባል። ምዕራባውያን ምሁራን የሚያስተምሩት በክርስትና፣ በእስልምና እና በኦሪት እምነቶች ላይ የተመሰረተውን ታሪክ ነው።

ኢትዮጵያ ሶስቱን ታላላቅ መለኮታዊ እምነቶች ተቀብላ የኖረች ሀገር ነች። ከሃይማኖት፣ በተለይም ከዘፍጥረትና ከሴም ቋንቋዎች ጋር በማያያዝ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከደቡብ አረቢያ የመጣ ሕዝብ ነው የሚሉት። እንደመጽሐፍ ቅዱስ አባባል አዳምና ሔዋን የተፈጠሩት በመካከለኛው ምስራቅ ውስጥ ነው። በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ ያሉ ሕዝቦች ሴማውያን ስለሆኑ የሴም ቋንቋ ተናጋሪ የሆነ ሕዝብ ሁሉ ከመካከለኛው ምስራቅ የፈለሰ ነው ብለው ለ300 ዓመታት ነጭ ምሁራን ሲያስተምሩ ቆይተዋል። ይህ እምነት ነው፣ የሚያስፈልገው ግን እምነት ሳይሆን እውቀት ነው። እውቀት የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስ፣ ክርክር የማያስነሳ የመሬት፣ የሕዝብና የስፍራ ጥያቄ

[7] እፎይታ፣ ቅ.6 ቁ.2 (ኅዳር 1990)፣ ገፅ 16-22።





ስለሆነ ማስረጃ ያስፈልገዋል። ከዚህም የተነሳ ኢትዮጵያውያን ማን ናቸው? ተብሎ ይጠየቃል። ይህ ዘወትር የሚነሳ ጥያቄ ነው።

ከፍተኛ ጥንታዊ ስልጣኔ በኢትዮጵያ መገኘቱ ሐቅ ነው። ፊደልና ዘውድ ኢትዮጵያ ውስጥ ተገኝተዋል። ይህ የሥልጣኔ ምልክት ነው። ከዚህ አኳያ በ1681 ጀርመናዊው የቋንቋ ምሁር ኢዮብ ሉዶልፍ የኢትዮጵያ ታሪክን በሚመለከት አንድ መጽሐፍ ጽፏል። ይህ ምሁር የኢትዮጵያን ቋንቋዎች ሲመረምር ስምንት ሕያው የሆኑ የሴም ቋንቋዎችን ማለትም ግዕዝ፣ ትግረ፣ ትግርኛ፣ አርጎባ፣ አማርኛ፣ ጉራግኛ፣ ሐረሪኛና ጋፋትኛ አገኘ። ከዚህ ግኝት ተነስቶ ቋንቋዎቹ ከደቡብ አረቢያ የመጡ ናቸው ብሎ ደመደመ። በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያውያን ከደቡብ አረቢያ የመጡ ሕዝቦች ናቸው ብሎ አስተማረ ማለት ነው። ለምን? ከሁሉ አስቀድሞ፣ ኢዮብ ሉዶልፍ ክርስቲያን ነው። ስለዚህም ሥራውን የመሰረተው በክርስትና እምነት ላይ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በሉዶልፍ ዘመን የአዝጋሚ ለውጥ ጽንሰ ሀሳብ (evolution theory) አልነበረም። የአዝጋሚ ለውጥ ጽንሰ ሀሳብ የመጣው በ19ኛው ምዕተ ዓመት ነው። ስለዚህም የነሉዶልፍ ሥራ የተመሰረተው በክርስትና አስተምህሮ ላይ ነው። ከዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ የእስራኤልና የአረብ ወገን ነው ተብሎ ተፈረጀ።

ከሉዶልፍ ቀጥሎ የተነሱ ምዕራባውያንና የአይሁድ የቋንቋና የስነጽሑፍ ሊቃውንት በተለይም የጀርመን፣ የኢጣሊያና የይሁዲ ሊቃውንት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሴማዊ ሕዝብ ነው ብለው በስፋት አስተማሩ። እኛንም ጭምር ያስተማሩን ይህንኑ ታሪክ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ምርጥ የሆነ ሴማዊ ሕዝብ ከምድረ አረቢያ ተነስቶ ኋላቀር የነበረውን የአፍሪካን «ኩሻዊ ሕዝብ» አሰለጠነ እንደማለት ነው። ይህ ግን በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሠረተ እውቀት ሳይሆን ሃይማኖታዊ ቀኖና ነው። እኛ ከታሪክ አኳያ መመርመር ያለብን ደግሞ በቀኖና ላይ የተመሠረተ ሃይማኖትን ሳይሆን ተጨባጭ መረጃዎችን ነው። መረጃ ከሌለ ታሪክ የለም። ታሪክ የሚኖረውም መረጃ ሲኖር ነው። ታሪክ ማለትም ባለፉት ዘመናት የሰው ልጅ የሰራቸው ተግባሮች ናቸው። የሰዎች ሥራዎች የሚነገሩት ግን ከእውቀት እንጂ ከእምነት አይደለም።

በመሠረቱ የኢትዮጵያን ታሪክ ከሶስቱ መለኮታዊ ሃይማኖቶች ጋር እያያያዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመካከለኛው ምስራቅ የመጣ ነው ማለት ሚዛን አይደፋም። የኢትዮጵያ ታሪክ ከመካከለኛው ምስራቅ ታሪክ ቅድሚያ አለው። ምክንያቱም የአይሁድ ታሪክ «ከአብርሃም ኩተኑሳን» ያለው እድሜ 4000 ዓመት ነው። የአፍሪካ ቀንድ ታሪክ ግን

ከአይሁድ፥ ከሙሴና ከኖህ በፊት ነበር። ሕዝቡም እዚሁ ምስራቅ አፍሪካ ውስጥ ነበር። ሙሴ ራሱ ሲጽፍ በምስራቅ አፍሪካ ያለውን ሕዝብ ፑንት፥ በሱዳን ያለውን ሕዝብ ኩሽ፥ በግብፅ የነበረውን ሕዝብ ግብፃዊ ብሏል። ስለዚህም እነዚህ ወንድማማች የሆኑ ነበርና ጥንታዊያን ሕዝቦች በአካባቢው መኖራቸውን እንጂ ከአረቢያ መምጣታቸውን የሙሴ ዘገባ አያመለክትም።

ይህንን ሐቅ ከተቀበልን በሶስቱም አካባቢዎች ማለትም በግብፅ፥ በኑቢያና በኢትዮጵያ ታላላቅ ሥልጣኔዎች ነበሩ። ነገር ግን ምዕራባዊያን ምሁራን ይህንን እውነታ በመካድ አፍሪካዊ ሥልጣኔ አልነበረም አሉ። ጥቁር ሕዝብ አይሰራም፥ የግብፅ፥ የኑቢያና የኢትዮጵያ ሥልጣኔዎች መጤዎች ናቸው ብለው አስተማሩ። ሥልጣኔዎቹ የጥቁር ሥልጣኔዎች ሊሆኑ አይችሉም ብለው ደመደሙ። ሌላውንም ሕዝብ አሳመኑ። አሁን ግን ሳይንስና ቴክኖሎጂ ከማደጉ የተነሳ የእውቀት አብዮት ተካሄደ፥ ምርምር ተጠናከረ። አርኪዮሎጂ እንደገና ተመረመረ። በምድር ውስጥ ተቀብሮ የነበረው ጽሑፍ ተጠና። የአርኪዮሎጂው መረጃ አውሮፓውያን ታሪክ ብለው ያስተማሩትን ተረት የሚያፈርስ ሆኖ ተገኘ።

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሀገር በቀል ናቸው

ከ1955 ጀምሮ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የአርኪዮሎጂ ጥናት ተካሂዷል። በዚህም መሠረት በጥንታዊ የደአማት፥ የሳባ፥ የግእዝና የግሪክ ቋንቋዎች የተፃፉ ወደ 500 የሚጠጉ ሰነዶች በኢትዮጵያ ተገኝተዋል። ደአማት ለግእዝ መነሻ የሆነ ጥንታዊ ቋንቋ መሆኑ ተረጋግጧል። ሰነዶቹ የሚያስረዱት የሴም ቋንቋዎች የአፍሪካ ቋንቋዎች መሆናቸውን ነው። አውሮፓውያኑ ግን ሴማዊ ፊደልና ስምንት የሴም ቋንቋ ማኅበረሰቦች ስለተገኙ ሕዝቦቹ ከባሕር ማዶ ነው የመጡት ብለው አስተማሩ። እምነታዊ ተጽእኖም አሳደሩ።

ዳሩ ግን በኢትዮጵያ ከአክሱም ሥልጣኔ በፊት በነበረው የደአማት ሥልጣኔ ዘመን ሁለት ፊደሎች እንደነበሩ በአርኪዮሎጂ ጥናትና ምሁራን አሁን ተረጋግጧል። ከሁለቱ አንዱ የሳባ ጽሑፍ ሲሆን ይህም ጽሑፍ ሐውልታዊ የቁም ጽሑፍ ነው። ሆኖም ይህ ጽሑፍ አንድ መቶ ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ ጠፍቷል። በምን ምክንያት እንደጠፋ ግን አይታወቅም። ከሳባ ፊደል ሌላ ስድ (cursive) የሆነ ፊደልም ተገኝቷል። ጽሑፉ ተራ ጽሑፍ ሲሆን የዚህ ጽሑፍ ምስጢር የተገኘው ከ20 ዓመት በፊት ነው። የዚህን ጽሑፍ ምስጢር ታላላቅ ምሁራን የተባሉት ኤኖ ሊትማንና ኮንቲ ሮሲኒ እንኳ ሊያውቁት





አልቻሉም ነበር። እንዳውም ኢትዮጵያ ውስጥ ከመጣ በኋላ ኢትዮጵያውያን ያበላሹት የሳባ ፊደል ነው ብለው ደምድመዋል። አሁን ግን የጥንት ጽሑፍ ኤክስፐርቶች (epigraphists) ሲመረምሩት ራሱን የቻለ የደአማት ፊደል ሆኖ ተገኘ። ይህ ፊደል በኋላ ለመጣው ለግእዝ ፊደልና ጽሕፈት መሠረት እንደሆነ በአርኪዮሎጂ ጥናት ተረጋግጧል። ይህንንም ምስጢር የደረሰበት የደቹ ተወላጅ አብርሃም ጆሃን ድሬዌስና የሉክሰምበርግ ተወላጅ ሮዠር ሽናይደር ናቸው። እነዚህ ምሁራን በመጀመሪያ ሌሎች አውሮፓ ውያን የፃፉዋቸውን ድርሳናት በሙሉ ከመረመሩ በኋላ አያሌ ጥያቄዎችን ደረደሩ። ቀጥሎም የኢትዮጵያ ፊደል ከውጭ ለመምጣቱ ማስረጃው ምንድነው? ብለውም ጠየቁ። በኋላም ድሬዌስ በ1962 እኤአ እስካሁን በአውሮፓውያን የተፃፈው ታሪክ ስሕተት ያለበት መሆኑን በሚገባ አጋለጡ። በመጨረሻም ኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘው ደአማታዊ ፊደል ሀገር በቀል እንጂ ከውጭ የመጣ አለመሆኑን ፕሮፌሰር ሽናይደር ጨምረው አረጋገጡ።

ሁለቱ ምሁራን የደረሱበት ግኝት ትክክለኛ መሆኑንን አለምን አሳመኑ። እርግጥ የሳባ ፊደል ኢትዮጵያ ውስጥ ተገኝቷል። ነገር ግን ከርሱ በፊት ለዛሬ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥልጣኔ መሠረት የሆነው የደአማት ፊደል የተገኘው በኢትዮጵያ ምድር ነው። ፊደሉ ከኢትዮጵያ ውጭ በሌላ አለም አልተገኘም። አለመገኘቱንም የቋንቋ ሳይንስና የአርኪዮሎጂ መረጃዎች አረጋግጠዋል።

በቋንቋ ሳይንስ ማስረጃዎች እውነታ መሠረት ፊደሉ በታዳጊነት ደረጃ ላይ የነበረ ቢሆንም የግዕዝ ቋንቋ ፊደልና ጽሕፈት የተገኘው ከዚሁ ከደአማት ቋንቋ ፊደልና ጽሕፈት መሆኑ ተረጋግጧል። በኋላ ግን እያደገ በመሄድና አናባቢዎችን በመጨመር የግእዝ ፊደል ሆኗል። በዚህም መሠረት እስከ አሁን ቀኖናዊ ምሁራን እንደሚነግሩን ሳይሆን የኢትዮጵያ የአክሱም ሥልጣኔ የሚጀምረው ከአክሱም ሥልጣኔ 500 አመታት በፊት ከነበረው የደአማት መንግሥት ነው።

## የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ጥንታዊ ነው

የደአማት ሥልጣኔ ከመጀመሩ በፊትም በአፍሪካ ቀንድ የፑንት ሥልጣኔ ነበር። የፑንት መንግሥት ከግብፆች ጋር ከ2800-1000 ዓመተ ዓለም ድረስ ለ1800 ዓመታት ያህል የጠበቀ የንግድ ግንኙነት ነበረው። በዚያን ወቅት ተስሎ የተገኘው ስዕል የዛሬ ሱማሌዎችን፥ ትግሬዎችን፥ ኦሮሞችን፥ አፋሮችን ወዘተ የሚመስል ገፅታ አለው። ሥዕሉ እነዚህ ሕዝቦች በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የሚኖሩ ጥንታውያን ሕዝቦች መሆናቸውን ያሳያል። ይህ ከዛሬ 7,000 ዓመታት በፊት የነበረ ሥዕል

ኢትዮጵያ ከጥንት ግብፃውያን ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደ ነበራት ያሳያል።

በሰሜን ኢትዮጵያ ያልተቋረጠ ዘመናዊ መንግሥት የጀመረው ከደአማት ዘመን ሲሆን ከዚያ በኋላ የአክሱም መንግሥት፥ ከአክሱም መንግሥት ቀጥሎ የአገው መንግሥት፥ ከአገው መንግሥት በኋላ የአማራ መንግሥት ይከተላል። በደቡብም እንደዚሁ ሐርላና ሀዲያ የሚባሉ ሕዝቦችና መንግሥታት ነበሩ። እስልምና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ደግሞ አያሌ መንግሥታት ተስፋፍተዋል። በዚህም መሠረት ለመንግሥታት መበራከት የኦሪት፥ የክርስትናና የእስልምና እምነቶች ምክንያት ሆነዋል። እነዚህም ሃይማኖቶች ከጥንት ጀምሮ ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደ ነበረን ያሳያሉ። ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምስራቅ ጋር የንግድ መስተጋብሮች የነበሩዋት ሲሆን በመካከለኛው ምስራቅ ውስጥ የነበሩ ሉአላዊ መንግሥታትና የኢትዮጵያ መንግሥት ግንኙነት ነበራቸው። የአርኪዮሎጂ መረጃም የሚመሰክረው ይህንን ሐቅ ነው። ሐቁ ይህ ከሆን ደግሞ ከ50 ዓመት በፊት ስለኢትዮጵያ የተፃፉት ታሪኮች ተረቶች ነበሩ ማለት ይቻላል። መነሻቸውም ቁጥር የሥልጣኔ ፈጣሪ ሊሆን አይችልም የሚል መላምት ነው። የሚገርመው ግን ያንን ተረት ተቀብለን ማስተጋባታችን ነው። ነገሩ ሞኝን አንድ ጊዜ ስደበው ራሱን ሲሰድብ ይኖራል እንደሚባለው መሆኑ ነው። ያም ሆነ ይህ እውቀት በሰፈነበት ዘመን ፈረንጆቹ ያሉትን ተቀብሎ ማስተ ጋባቱ የሚያዋጣ ነገር አይደለም። የአርኪዮሎጂ መረጃ የሚያሳየው የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ምንጭም፥ መነሻም፥ ባለቤትም ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ነው።

## አውሮፓውያን የማንነት ችግር አለባቸው

በቋንቋ ሳይንስ በኩል ያለውን ደግሞ እንመርምር። ይህ የቋንቋ ሳይንስ የአንድን ቋንቋ አገባብ፥ ግስ፥ እድሜና ዘርፉን የሚነግረን ነው። የቋንቋ ሳይንስ ሊንጉዊስቲክስ ይባላል። የሥነ ልሳን ሳይንስ የተስፋፋው ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ ሲሆን አዲስ ሳይንስ ነው። ከዚያ በፊት ግን ከዚህ ቀድም ስለኛ ሲነግሩን የነበሩ አውሮፓውያን ማንነትን በግልፅ እንመርምር። ከሁሉ አስቀደሞ አውሮፓ የማንነት (identity) ችግር ያለበት አህጉር ነው። በዚህም ረገድ ግብፆች የዓለም መንግሥት በነበሩበት ወቅት፥ ፊኒቃውያን የዓለም አስተማሪዎች በነበሩበት ወቅት፥ ባቢሎናውያን የዓለም ሕግ አስተማሪዎች በነበሩበት ወቅት የአውሮፓውያን ሥልጣኔ አልነበረም። ከዘመናት በኋላ ግን ግሪኮች ተነሱ።





ግሪኮችም ወደ ግብፅ ተጉዘው ሃይማኖትንና የሃይማኖት ሥርዓትን፥ ጂኦሜትሪንና ኪነጥበብን ከግብፅ ሊቃውንት ተማሩ።

ከፊኒቃውያንም እንደዚሁ የተለያዩ ጥበቦችን ተምረዋል። በዚያ ምክንያት ግሪካውያን ሰለጠኑ። ሮማውያንም ለጠቁ። እስልምና ሲነሳ ግን ታጠፉ። ከዚያ በኋላ ምዕራብ አውሮፓ ውስጥ ከማእከላዊ አውሮፓ የመጡ ባርቤሪያንስ የተባሉ ወራሪ ዘላኖች የግሪክንና የሮማውያን ሥልጣኔ አጥፍተው በኋላ አዲስ ክርስቲያናዊ ሥልጣኔ መሰረቱ። ከዚያም መስፋፋት ጀመሩ። ነገር ግን የእስልምናን እንቅስቃሴ መቋቋም አልቻሉም። የመስቀል ጦርነት የሚባል ዘመቻ አውጀው ለ300 ዓመታት ተዋግተው ተሸንፈዋል። ከዚህም የተነሳ የጥቁር ዘር እኩይ ነው፥ የአረብ ዘር እርጉም ነው፥ እስልምና ማለት ባርነት ነው ብለው ሰበኩ፥ አስተማሩ። በመሠረቱ ይህ ትምህርት ሚዳቋን አባሮ መያዝ ሲያቅት ስጋዋ መጥፎ ነው ከማለት የተለየ አይደለም።

ከዘመናት በኋላ ግን አውሮፓውያን ሳይንስና ቴክኖሎጂን አስፋፍተው በየብስ ያቃታቸውን በባሕር ተጉዘው ዓለምን በቅኝ ግዛትነት ያዙ። አፍሪካን የባሪያ ገበያ፥ የምዕራባዊ ንፍቀ ክበብ አህጉራትን፥ አውስትራሊያንና ኒውዚላንድንም መኖሪያቸው አደረጉ። ከዚህ በኋላ የማንነት ጥያቄ ተነሳ። ጀርመኖች፥ እንግሎ-ሳክሰኖችና ፍራንኮች ባርቤሪያንስ ስለነበሩ ከዚያ የተገኘ ሥልጣኔ ስላልነበር ፊታቸውን ወደ ግሪክ ሥልጣኔ አዞሩ። ይህንን ያደረጉት የማንነትን ጥያቄ ለመመለስ ነው። ከሮማውያን ሕግን፥ ከግሪኮች ዴሞክራሲን ወሰዱ፤ ያም ስላልበቃቸው ክርስትናን አጠናከሩ።

የግሪክን ሥልጣኔ ሲመረምሩ ከግብፅ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ሆኖ አገኙት ግን አምኖ ለመቀበል አልፈቀዱም። ምክንያቱም ባሪያ አድርገው የገዙትን አፍሪካዊ፥ የሰው ዘር አይደለም ብለው የካዱትን ሕዝብ የሥልጣኔ ምንጭ ነው ብለው መቀበል አዳገታቸው። ሆኖም ሶስት የጥቁር ሕዝብ ሥልጣኔዎችን አግኝተዋል። የግብፅ፥ የኑቢያና የአክሱም ሥልጣኔዎች ናቸው። እነዚህን ሥልጣኔዎች አፍሪካዊ ሥልጣኔዎች ናቸው ብለው ለመቀበል አልፈለጉም። ይህን ያልተቀበሉት የሚያካሄዱትን የባሪያ ንግድ የሚቃረን በመሆኑ ነው። ስለዚህም አውሮፓውያን ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ ገቡ። በመግባታቸውም ኢትዮጵያ የሚለውን ስም በመፋቅ አቢሲኒያ በሚል ስያሜ ተኩት። የአንድን ነገር ሕልውና ለማጥፋት መጀመሪያ መጠሪያውን መቀየር የተለመደ አካሄድ መሆኑን ካርል ማርክስ በአጽንኦት መግለጹን እዚህ ላይ ማስታወስ ይጠቅማል።

ይህንን ከአደረጉ በኋላ አውሮፓውያኑ የፈጠሩ ታሪካቸውን አስተማሩን፣ የነፃ ትምህርት እድል ሰጡን። እኛም ያስተማሩንን አጠናን። ያንን ለሌሎችም ማስተማር ጀመርን። የአርኪዮሎጂ ዕውቀት እየሰፋ ሲሄድ ግን የተማርነው ትምህርት ስህተት ሆኖ ተገኘ። ስነልሳን በበኩሉ የሴም ቋንቋዎች በአረቢያ፣ በባቢሎን ከመነገራቸው በፊት፣ ፊኒቃውያንና አይሁዳውያን ከመገኘታቸው በፊት ቢያንስ ከ10 ሺህ ዓመታት በፊት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ይነገሩ እንደነበር አረጋገጠ። ቋንቋዎቹ ወደ መካከለኛው ምስራቅ የሄዱት ከአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ተነስተው እንደሆነም አሳየ። በዚህም መሠረት ማስረጃዎች የሚያረጋግጡት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሀገር በቀል መሆናቸውን ነው። ስለሆነም ሴማዊ፣ ኩሻዊ፣ ናይሎቲካዊና ኦሞአዊ ቋንቋዎች በሙሉ ኢትዮጵያውያን ቋንቋዎች ናቸው። ከውጭ የመጣ አንድም የኢትዮጵያ ቋንቋ የለም። ሕዝቡም የዚሁ ሀገር ተወላጅ፣ ነባር ነው። መጤ የሚባል ሕዝብ የለም። የጠፋ ዘርም የለም። የሚያስገርመው ነገር በሌላው ዓለም ዘር ሲጠፋ፣ በባእዳን ሲገዛ፣ በአፍሪካ ቀንድ ግን የጥንቱ ጥንታውያን ደአማታውያን ሆኑ፣ ደአማ ታውያን ደግሞ አክሱማውያን ሆኑ እንጂ አልጠፉም። ፈረንጆቹ ያስተማሩት ግን የዚህን ተቃራኒ ነው። ለመሆኑ በመካከለኛው ምስ ራቅ ውስጥ ያልነበረ ቋንቋ እንዴት ወደዚህ ሊመጣ ይችላል?

## የሰው ዘር መገኛ የአፍሪካ አህጉር ነው

በፓሌኦንቶሎጂ መረጃና ትምህርት መሰረት፣ የሰው ዘር መገኛ ምንጭ ባቢሎንና መካከለኛው ምስራቅ ሳይሆኑ የአፍሪካ አህጉር ነው። ከዚህ አኳያ የድንቅነሽ ቅሪት አካል በኢትዮጵያ መገኘት የዓለምን ታሪክ ገለባብጦታል። የሰው ዘር መገኛ በአፍሪካ አህጉር የኢትዮጵያ ምድር መሆኑን ድንቅነሽ አስመስክራለች። እንደ ይሁዳው ያኑና እንደ አውሮፓውያኑ የሃይማኖት ትምህርት ከሆነ የዓለም ታሪክ ከ6000 ዓመታት አይበልጥም። ምክንያቱም ትምህርታቸው በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ የምድርን እድሜ ከ8000 ዓመታት በታች ያደርገዋል። የድንቅነሽ እድሜ ግን ከ3 ሚልዮን ዓመት በላይ ነው። የሰው ልጅ የተገኘው በአዋሽ አካባቢ ነው። አዋሽ ደግሞ የኢትዮጵያ ወንዝ ነው። አፍሪካ የሰው ዘር መገኛ መሆንዋን ዩኔስኮ ተቀብሎታል። ዩኔስኮ ስለአፍሪካ ታሪክ በስምንት ተከታታይ ቅፆች ባሳተማቸው ፅሁፎች የሰው ዘር መገኛ አፍሪካ እንደሆነች በሚገባ ገልጿል። ጀርመኖችና ኢጣሊያውያን ምሁራንም አሁን የአፍሪካን የሰው ዘር ምንጭነት ይቀበላሉ።





በእርግጥም በእምነት ግፊት ሳይሆን በተጨባጭ እውቀት የምናምን ከሆነ መቀበል ያለብን ሰው የተገኘው በአፍሪካ ቀንድ መሆኑን ነው። የአሁኑ ዘመን የምዕራብ ሊቃውንት የአፍሪካን የሰው ዘር ምንጭነት ተቀብለዋል። ይህንን ሐቅ ፖሌአንቶሎጂ አረጋግጧል። በተጨማሪም የሁለት ሚሊዮን ዓመት እድሜ ያለው ድንጋይ መሳሪያ ከአዲስ አበባ 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በመልካ ቁንጥሬ ተገኝቷል። በአፋር ምድር የተገኘውም የድንጋይ መሳሪያ ደግሞ የአራት ሚልዮን ዓመት እድሜ አለው። ይህም የቤት እንስሳትን፣ እፅዋትን አዝርዕትንና አራዊትን ያሰለጠነ ሕዝብ የተገኘው በዚህ ሀገር ነው። የተከዜ፣ የቀይ ባሕር፣ የአዋሽ፣ የዓባይ፣ የኦሞ፣ የዋቢሸበሌ፣ የዳቡስ ወንዞች ወዘተ የሚገኙትም በዚህ አካባቢ ነው። በዚህ አካባቢ የሚገኘው ሕዝብ በሚደረገው እንቅስቃሴ፣ በጦርነት፣ በጋብቻ እርስ በርስ የተወራረሰ ነው። ከሁሉምጤም ትልቁ ነገር የመንግሥት ምስረታ ነው። በዚህ ረገድ የአካባቢው የጥንት መንግሥት ከየትኛውም ሀገር በፊት መንግሥት ከመሰረተው ከጥንቱ የግብፅ መንግሥት ጋር ለ1800 ዓመታት ያህል የጠበቀ ግንኙነት ነበረው።

ነገር ግን ይህን የአገር ታሪክ እውነታና እውቀት ከማወቅና ከማስተማር አኳያ፣ ከሃይማኖት ተፅእኖ የተነሳ ኢትዮጵያዊው ምሁርና ባለሙያ ፈሪና ተጠራጣሪ ሆኗል። እምነቱ ስለተጫነው ወይም የውጭ አስተማሪ፣ ምሁር ስለተናገረ፣ እሱም የኔ መምህር ስለሆነ ያንን መቀበል አለብኝ የሚልም ይመስላል። ነገር ግን ያንን ተረት ዘመናዊና ሳይንሳዊ የታሪክ መረጃና ትምህርት ሽሮታል።

## የአፍሮ-እስያ ቋንቋዎች መነሻና ትምህርት

የአፍሮ-እስያ ቋንቋዎች መገኘት አብዮታዊ አስተሳሰብን አምጥቷል። የዚህ ግኝት ባለቤት አሜሪካዊው ፕሮፌሰር ጆሴፍ ግሪን በርግ ናቸው። አፍሮ-እስያዊ የቋንቋ ቤተሰብ የቅብጥን (ግብፅ)፣ የበርበር (የሰሜን አፍሪካ)፣ ቻዳዊ (ምዕራብ አፍሪካ)፣ ኩሻዊ፣ ናይሎቲካዊ፣ ኦሞአዊና ሴማዊ የተባሉ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ያጠቃልላል። እነዚህ ቋንቋዎች የአፍሪካና የእስያ ጥንታዊና ተዛማጅ ቋንቋዎች ናቸው። ከነዚህ ቋንቋዎች ውስጥ የሴም ቋንቋዎች በኢትዮጵያ፣ በደቡብ አረቢያና በመካከለኛው ምስራቅ ይገኛሉ። ሃያ አራት የሚሆኑ ኩሻዊ ቋንቋዎች የሚገኙት በኢትዮጵያ ሲሆን ሌሎች የኩሽ ቋንቋዎችም በጎረቤት ሀገሮች ይገኛሉ። የኦሞአዊ ቋንቋዎች የሚገኙት በኢትዮጵያ ብቻ ነው። ናይሎቲካዊ ቋንቋዎችም በኢትዮጵያና በጎረቤት ሀገሮች ይገኛሉ። እነዚህን ቋንቋዎች የሚናገሩ ሕዝቦች ጥንታውያንና

ተዛማጆች ናቸው። ሕዝቦቹ በዘር፣ በሥፍራና በጊዜ ተወራርሰዋል። ነባር የአካባቢው ነዋሪዎችም ናቸው። ኩሻዊ ቋንቋ የሚወክለው ሶስት ጥንታዊ ሕዝቦችን ሲሆን ይኸውም በአፍሪካ ቀንድ ፑንታውያንን፣ በላይኛው ዓባይ ሸለቆ ኑቢያውያንን፣ በታችኛው ዓባይ ሸለቆ ግብፃውያንን ነው። ከነዚህ ቋንቋዎች ውስጥ የኑቢያ ቋንቋ ጠፍቷል። ሀገሩም የአረቦች ሀገር ሆኗል። ግብፅም እንዲሁ የአረቦች ሀገር ሆኗል።

ዛሬ እነዚህን ሶስት ጥንታዊ የኩሽ ቋንቋዎችን የምትወክል ኢትዮጵያ ናት። የፑንትት፣ የግብፅና የኑቢያ ወራሽ የሆነ ያልጠፋ ሀገርና ሕዝብ የሚገኘው በአፍሪካ ቀንድ ነው። ቋንቋ በኢትዮጵያ የዘር መለያና የማንነት መግለጫ ነው። በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ እየተካሄደ ነው። አዲስ የፖለቲካ ስልት፣ አዲስ የኢኮኖሚ ሥርዓት እየተመሰረተ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ባሕር ነው። እስካሁን የተፃፈው ግን ዜና መዋእልና ገድል ነው። መፃፍ ያለበት ግን የኅብረተሰብ ታሪክ ነው። ያንን ለማድረግ የሚያስችሉ መረጃዎች ተገኝተዋል። አዲስ የታሪክ አጠናን ስነዘዴም (methedology) ተፈጥሯል። ቋንቋን ብንወስድ የሀገር፣ የብሔር፣ የብሔረሰብና የማኅበረሰብ መለያ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት 50 ዓመታት የብሔር ብሔረሰቦች አብዮት እየተካሄደ ነው። የብሔር ብሔረሰቦች አብዮት ማለት የቋንቋ፣ የታሪክ፣ የባህል፣ የሃይማኖት እንቅስቃሴ መግለጫ ማለት ነው። ይህ በሚደረግበት ዘመን የአርኪዮሎጂ፣ የሥነ ልሳንና የፖሌዮንቶሎጂ መረጃዎች ከእኛ ጋር ተሰልፈዋል። የአፍሮ-እስያዊ ቋንቋ ቤተሰብ መገኘት ከዚህ ቀደም የነበረውን ታሪክ ሽሮታል። ከዚህ ቀደም የነበረው ታሪክ ጥንታዊ የአይሁድ አስተማሪዎችና ጸሐፊዎች በፃፉት ድርሳናት ላይ የተመሰረተ ነው። ታሪኩም ከእምነት ጋር የተቆራኘ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ ነው። የአውሮፓ ታሪክ ጸሐፊዎች ያስተጋቡት የነበረው ያንን ታሪክ ነው። በዚህም የተነሳ ነው የሴም ቋንቋዎች መነሻ መካከለኛው ምስራቅ ነው የተባለው።

አውሮፓውያን በበኩላቸው የኢንዶ-አውሮፓ፣ ግሪክና ላቲን ቋንቋዎችን አቅፈው ተነሱ። በዚያም ምርጥ ዘር ነንና ዓለምን መግዛት አለብን አሉ። ከሰው ዘሮች ሁሉ ምርጥ የሆነው የአርያን ዘር ነው የሚል ፍልስፍና አመጡ። አፍሪካን ባሪያ አድርገው መግዛት ያዙ። የአፍሪካ ሕዝቦችን ሥልጣኔ ካዱ። ይህም ለባሪያ ንግድ እንዲ መቻቸው ነው። የግብፅን ሥልጣኔ መካድ ሲቸግራቸው ደግሞ ግብፅ ጥቁር አይደለም፣ ነጭ ነው አሉ። ኑቢያም ነጭ እንጂ ጥቁር ሕዝብ አይደለም አሉ። የኢትዮጵያን ሥልጣኔ አፍሪካዊነት ለመካድ የኢትዮጵያ ሕዝብ





ነጭ እንጂ ጥቁር አይደለም አሉ። አውሮፓውያን በመወናበድ ላይ ሳሉም ዘረኝነት መጣ። ይህም ሒትለርና ሙሶሊኒን አስነሳ። ሒትለር የሰውን ዘር ለማጥፋት ታጥቆ ተነሳ። አውሮፓ ነደደ። አውሮፓውያን ተርበደበዱ፤ አፈሩ። ይህን ሁሉ ጣጣ ያመጡት የሰው ዘር ጥላቻንና ንቀትን ሲሰብኩ የነበሩ ፈላስፋዎቻቸው ናቸው። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት መከራን ተጋቱ። ጥቁር ሕዝብ ሰብአዊ ፍጡር አይደለም ብለው ሲሰብኩ የነበሩት ጀርመኖች በተለይ ራቁታቸውን ቀሩ። የዘረኝነት ፍልስፍናቸው ራሳቸውን መልሶ ሲያቃጥላቸው ጊዜ ዛሬ የሰው ልጅ ሁሉ እኩልነትና ሰብአዊ መብት ይከበር እያሉ ማስተማር ጀመሩ። ከአውሮፓ ዘር ውጭ ያለው ሕዝብ ሰብአዊ ፍጡር አይደለም እንዳላሉ ሁሉ ዛሬ ለሰው ዘር ዴሞክራሲያዊ መብት ተሟጋች ሆኑ። ይህ ያለፈ በደላቸውን ለማካካስ ሲሉ የፈጠሩት ዘዴ ነው።

በቋንቋም ረገድ የነበረው መላምት ውድቅ ሆኖባቸዋል። የኢትዮጵያን ቋንቋዎች በኢንዶ-አውሮፓዊና በአይሁድ ቋንቋዎች ውስጥ ማስቀመጥ አልቻሉም። የአሜሪካ ፕሮፌሰሮች የደረሱበት ጭብጥ የእስያና የአፍሪካ ቋንቋዎች ተዛማጆች መሆናቸውን ነው። ከዚህም ሌላ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ቋንቋዎች ሀገር በቀል እንጂ ከውጭ ያልመጡ ቋንቋዎች መሆናቸው ታውቋል። ይህ ደግሞ አሁን ለተያያዝነው የሀገር ግምባታ በጣም ጠቃሚ ነው። ሴማዊ፣ ኩሻዊ፣ ናይሎቲካዊና ኦሞያዊ ሕዝቦች ነባር ኢትዮጵያውያን ሕዝቦች ናቸው። በእውቀት መንገድ የምንጓዝ ከሆነ ሐቁ ይህ ነው። በእምነት ዓለም የምንጓዝ ከሆነ ሌላ ጉዳይ ነው። ማስረጃዎች የሚያረጋግጡት ግን አንድም መጤ የሆነ ሕዝብ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሌለ ነው። እኛ መመራት ያለብን በሳይንስ መረጃ ነው እንጂ በእምነት ብቻ አይደለም። ታሪክን የምናውቀው በመዳሰስ ነው። ዘመኑን፣ ሕዝቡንና ስፍራውን ማወቅ ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ የሚያግዙን ደግሞ የፖሌኦንቶሎጂና የስነልሳን መረጃዎች ናቸው። በነዚህ መረጃዎች አማካይነት የኢትዮጵያውያን መነሻና ማንነት ማወቅ እንችላለን። ኢትዮጵያውያን ከጥንት ጀምሮ አሉ። ታላላቅ የነበሩትን፣ የሮማንና የፋርስ ሥልጣኔዎችን የደመሰሰው የአረብ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ጋር ተወዳጀ እንጂ ኢትዮጵያን አላጠፋም። ቱርኮችና ፖርቱጋሎች ኢትዮጵያን ለማጥቃት ሞክረው ነበር። ግን ተሸነፉ፤ ቅኝ ገዢዎችም ሞክረው ነበር ግን አድዋ ላይ ድል ተነሱ። ፋሽዝም ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ጦርነት ገጥሞ ተሸነፈ። ኢትዮጵያውያንም ያካሄዱት የ50 ዓመት አብዮት የሕዝብን አንድነት የበለጠ አጠናከረው እንጂ አላፈረሰውም። ይህ አካባቢ ሕልውናውን ጠብቆ የሚኖር ልዩ ችሎታ

ያለው ስፍራ ነው። ሕዝቡ ጥንታዊ ነው። ኋላቀር መሆኑም ታሪኩን የሚያዛባ ነገር አይደለም። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝቦች በፈጣን ዕድገት ጎዳና በመገስገስ ላይ ናቸው።

## የኢትዮጵያ ወንዞች የአፍሪካ ሥልጣኔ ምንጮች ናቸው

የኢትዮጵያ ጂኦ-ፖለቲካዊ ስፍራ እስትራቴጂካዊ ነው። ኢትዮጵያ የአፍሪካ የውሃ ጋን ናት። የኢትዮጵያ ውሃ የኑቢያንና የግብፅን ሥልጣኔ አፍርቷል። እኛንም አኑሮናል። ወንዞቹን በሚገባ አልተጠቀምንባቸው ይሆናል። ነገር ግን የወንዞቹ መኖር ራሱ ትልቅ ፀጋ ነው። የኢትዮጵያ ተራሮችም ትልቅ አስተዋፅኦ አላቸው። የታላላቅ ወንዞች መፍለቂያዎች ናቸው። ከዚህም ሌላ እስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ አላቸው። ለወራሪ ኃይሎች አይመቹም። ለሀገሬው ተወላጅ ግን ተስማሚ ናቸው።

ኢትዮጵያ በያይነቱ ሀብት አላት። የደጋ፣ የወይና ደጋ፣ የቆላና የበረሃ የአየር ንብረትዋ እጅግ ተስማሚ ነው። በያይነቱ እፅዋት፣ አዝርእት፣ አራዊትና እንስሳት ይገኛሉ። ደገኛው ወደ ቆላ ይወርዳል፣ ቆለኛው ወደ ደጋ ይወጣል። ሕዝቡ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደርጋል። ይህ ደግሞ ውስጣዊ ፍልሰትንና ውሕደትን ማለትም የሕዝቦችን መስተጋብርና መወራረስ ፈጥሯል።

## የተማከለ ቋንቋ ወጣት ነው

የኢትዮጵያ የሴም ቋንቋዎችን በተመለከተ ፕሮፌሰር ማርቲን ቤርናል ወዳነሳው ጥያቄ እንምጣ። ፕሮፌሰሩ የሚለው የተማከለ ቋንቋ ወጣትና ዘመናዊ እንደሆነ እንገንዘብ ነው። እንግሊዘኛን ብንወስድ በአሜሪካ፣ በአውስትራሊያ፣ በኒውዚላንድ የተማከለ ... ነው። ቋንቋው በተፈጠረበት በእንግሊዝ ግን በሀውርታዊ ነው። ይህም ብዙ ልዩነት ያሳያል ማለት ነው። በሀውርታዊ የሆነ ቋንቋ ጥንታዊነትን ማመልከቱ እርግጥ ነው። የተደራጀና የተማከለ ቋንቋ ደግሞ ዘመናዊ መሆኑ እርግጥ ነው የሚል አስተያየት ነው የሰነዘረው። ፕሮፌሰሩ የሰጠው የግንዛቤ ሐሳብ ነው። ውሳኔ አይደለም።

በጋዜጣና በመጽሔት ላይ የወጡትን አስተያየቶች ተመልክቻለሁ። አንዱ ሐሳብ የኢትዮጵያ ታሪክ በውጭ ሀገር ምሁራን መፃፍ የለበትም የሚል ነው። እውነቱ ግን ሌላ ነው። እስከዛሬ ድረስ ያለውን የኢትዮጵያ ታሪክ የፃፉት ፈረንጆችና አረቦች ናቸው። ኢትዮጵያዊ ታሪክ ፀሐፊ ነበር ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ያስቸግራል። ሁላችንም ባእዳን የፃፉትን ወስደን ነው የምናስተጋባው። በዛሬው ዘመን ታሪክ





ለመፃፍ አርኪዮሎጂ፣ ፖሌኦንቶኦሎጂ፣ ኢፒግራፊና የተለያዩ የትምህርት ዘዴዎችና ቋንቋዎች ማወቅ ያስፈልጋል። እስካሁን የነበረው «የኢትዮጵያ ታሪክ» ዜና መዋእል፣ ገድለ ቅዱሳንና ገድለ ሰማእታት ነው። የፃፉትም የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ባለሟሎች ናቸው። የተጻፈውም የመኳንንት፣ የመሳፍንትና የነገሥታት ታሪክ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ገና አልተፃፈም። የሕዝቦችን እውነተኛ ታሪክ ለመፃፍ ገና ሙከራ እየተደረገ ነው።

ፕሮፌሰር ቤርናል ጉራማኛ የግእዝ አያት ነው ያለው የሥነ ልሳንን ጥናት ስነዘዴ ተመርኩዞ ነው። ስለዚህም እኛ ማድረግ ያለብን የአጠናንን ስነዘዴ ማወቅ ነው። ፕሮፌሰሩ ኢንፎርሜሽን ሰጥቶናል። በአሁኑ ጊዜ እየታመነ የመጣ ነገርም አለ። ይህም የኢትዮጵያ የሴም ቋንቋዎች ከደቡብ አረቢያ የመጡ አይደሉም፣ ቋንቋዎቹ ነባርና ሀገር በቀል ናቸው የሚል ነው።

ፕሮፌሰር ቤርናል ታላቅ ምሁር ነው። የኢትዮጵያ ሴማውያን ቋንቋዎች ከደቡብ አረቢያ አልመጡም ብሎ እውነቱን ስለነገረን ማጉረምረም የለብንም። ፕሮፌሰሩ ያቀረበው ሐሳብ እንደግእዝና አማርኛ ያሉ ቋንቋዎች የተማከሉና ዘመናዊ ቋንቋዎች ናቸው። ይህም በእድሜ ወጣት መሆናቸውን ያመለክታል የሚል ነው። ይህንን ሐሳብ በጥልቀት መመርመር እንጂ «ሰውዬውን እወደዋለሁ ወይም እጠለዋለሁ» ማለት ብቻ ፋይዳ የለውም። እውቀት፣ ሙያ እንጂ ስሜት አይደለም።

በእፎይታ መጽሔት 5ኛ ዓመት ቁጥር 10/89 ላይ ትምህርታዊ ጽሑፍ ወጥቷል። እስከዛሬ ድረስ እንደዚህ ያለጽሑፍ በአማርኛ ቋንቋ ተጽፎ አያውቅም። እኔ ከ40 ዓመት በላይ ስለኢትዮጵያ አንብቤያለሁ። የኢትዮጵያ ታሪክና ማንነት በሚመለከት ያነበብኳቸው መፃሕፍት የሚያወሩት ሐቁን ሳይሆን መላምት ነው። በእፎይታ መጽሔት የቀረበው ጽሑፍ አንኳር ሀሳብ ግን አፍሪካ የአውሮፓ ሥልጣኔ ምንጭ ናት፣ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ምንጭም፣ ባለቤትም ኢትዮጵያ ናት የሚል ነው። ቋንቋም በተመለከተ የተነሳው ጥያቄ ለእኔ ያንን ያህል አንገብጋቢ መስሎ አይታየኝም። ማን አያት? ማን አባት? ማን ልጅ ነው የሚለው ጥያቄም ቢሆን ይህን ያህል የሚያስጨንቀን አይደለም። ዋናው ቁም ነገር ስምንቱም የሴም ቋንቋዎች ነባርና ሀገር-በቀል መሆናቸው መታወቁ ነው። ማን ከማን ይቀድማል የሚለውን ለመመለስ ያለን መረጃ አነስተኛ ነው። ያም ሆኖ ግን ፕሮፌሰር ቤርናል «የተማከለ ቋንቋ ዘመናዊና ወጣት ነው፣ በሀውርታዊ የሆነና ያልተማከለ ቋንቋ ደግሞ ጥንታዊ ነው» ያለው መንደርደሪያ ምሁራዊ አባባል

ነው። ለዚህ አባባል የሚረዳን አያሌ ሕዝብ የሚናገረውን ኦሮምኛን እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል። ኦሮምኛ ኩሻዊ ቋንቋ ነው። የተማከለና የተስፋፋም ቋንቋ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ 24 ገደማ የሚሆኑ ኩሻዊ ቋንቋዎች አሉ። ከነዚህ ውስጥ ስምንቱ በጣም ይቀራረባሉ። ከስምንቱ ቋንቋዎች አንዱ ኦሮምኛ ነው። የተቀሩት ሰባቱ ቋንቋዎች ያሉት በደቡብ ኢትዮጵያ ሲሆን በጣም ጥቂት ተናጋሪዎች አሏቸው። አንድ ምሁር ይህ ሁኔታ ሲያጋጥመው «የትኛው ነው ምንጭ፥ የትኛው ነው ቅርንጫፍ» ብሎ ይጠይቃል። ከዚህ በመነሳት ከስምንቱ ቋንቋዎች መካከል ኦሮምኛ ወጣት ነው ብሎ ግምት መስጠት ይቻላል። ፕሮፌሰር ቤርናልም ጉራግኛ የግእዝ እያት ይመስላል ያለው ከዚህ በመነሳት ነው። የጉራጌ ምድር ሜዳ ነው፥ ተራራማ አይደለም ያለውን አንድ ፀሐፊ በመቃወም የጉራጌ ምድር ተራራማ ነው ብሏል። ይህ ትክክለኛ አባባል አይደለም። ፕሮፌሰሩ ተራራ ሲል እንደራስ ዳሽን፥ ሒማሊያና ኤቨርስት ያሉ ተራሮች ማለቱ እንጂ ኮረብታ ማለቱ አይደለም። በጉራጌ ምድር ያሉ ኮረብታዎችን የተጫኑ በቅሎዎች፥ ፈረሶችና ሞኪናዎች የሚወጧቸው ናቸው። ቢያንስ ኮረብታና ተራራን መለየት መቻል አለብን። አንድን ሀሳብ ለመተቸትና ስሕተት ነው ለማለት ማስረጃ ያስፈልጋል። በተለይም የሰነድ፥ የሥነ ልሳንና የትውፊት መረጃዎች ያስፈልጋሉ። እነዚህ ሲሟሉ ነው አፍን ሞልቶ መናገር የሚቻለው። ባለሙያ መሆን ያስፈልጋል። የእውቀት ባለቤት መሆን ያሻል። አሁን ባለን መረጃ መሠረት ስምንቱ የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋ ዎች የአንድ ቋንቋ ቤተሰብ በመሆናቸው ይዛመዳሉ። ፕሮፌሰር ቤርናል ጉራግኛ ከግእዝ ቀደምትነት አለው የሚል ሀሳብ ሰንዝሯል። በቂ መረ ጃም ሰጥቷል። መቀበል የፈለገ ይቀበላል። መቀበል ያልፈለገ ደግሞ ያለመቀበል መብት አለው። የምሁር ድርሻ ማሳወቅ ነው። ምሁር የማስ ገደድ ሥልጣን የለውም። የምሁር ግዴታ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው። ፕሮፌሰር ቤርናል ያደረገውም ይህንኑ ነው። የሱን ሀሳብ ለማፍረስ የፈለገ ደግሞ በቂ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል። ስሜታዊ ተቃውሞ ማሳየት ምሁራዊ ባሕርይ አይደለም። በስሜት መነዳት የለብንም።

## የጉራጌ አመጣጥ ታሪክ

ስለጉራጌ ሕዝብ አመጣጥ ፕሮፌሰር ቤርናል አንድ ሀሳብ ሰንዝ ሯል። ጉራግኛና ሌሎቹ የሴም ቋንቋዎች እድሜአቸው በጣም ረጅም ነው። ከዚህ ቀደም ታሪክ ፀሐፊዎች የመሰላቸውን ፅፈዋል። ኮንቲ ሮሲኒ ግእዝ ከባሕር ማዶ መጥቶ ሌሎች ሴማዊ ቋንቋዎችን ወለደ ብሎ ጽፏል። ያ ሀሳቡ አሁን በትምህርትና በእውቀት ተሽሯል። ቀርቷል።





ተረት ሆኗል። የጉራጌን ቋንቋ ስንመለከት የ700 ዓመት እድሜ ያለው ቋንቋ ነው ለማለት የሚቻል አይመስለኝም። ጉራጌ የአምደ ፅዮን የጦር አበጋዝ ከሆነው አዝማች ስብሐት ጋር መጣ የሚል አፈታሪክ አለ። ይህንን የፃፉት አለቃ ታዬ ናቸው። አለቃ ታዬ የታሪክ ምሁር አይደሉም። ታሪክ ለመፃፍ የሞከሩ ሀገር ወዳድ ናቸው። አለቃ ታዬ ከሚሲዮኖች ጋር ጥቂት ቆዩ፥ ጀርመንን ጎበኙ፥ ከዚያም የኢትዮ ጵያን ታሪክ ጻፍኩ አሉ። አሁን እሳቸው የጻፉትን መፅሐፍ ስናነብ ጨዋታ ነው የሚመስለን።

የአለቃ ታዬ መጽሐፍ ጥሩ የተረት መጽሐፍ ነው። እኛ ስለ ሳይንስ ስለ ስነልሳን፥ ስለ ሰነድ መረጃና ስለ ስነዘዴ ነው የምንናገረው። እነዚህን መረጃዎች ለማሳጠርና ምርቱን ከግርዱ ለመለየት የሚችለው ደግሞ በመስኩ የተካነ ባለሙያ ነው። ዜና መዋዕል እኮ ጥሬ መረጃ ማለት ነው። ያንን ጥሬ መረጃ የሚተረጉም ባለሙያ ያስፈልጋል። እዚህ አገር ታሪክ ሲፃፍ የነበረው ሙያው ሳይኖር በድፍረት ነው። ታሪክ ለመፃፍ ግን የታሪክ ጥልቅ ሙያና እውቀት ያስፈልጋል።

የጉራጌን ሕዝብ በተመለከተ የአምደ ፅዮንን ጦር ከወጉት አያሌ የድቡብ ሕዝቦች መካከል አንዱ የጉራጌ ሕዝብ ነው። የጉራጌ ሕዝብ የአምደፅዮን ሰራዊት አካል ቢሆን ኖሮ አምደ ፅዮንን መልሶ አይወጋም ነበር። ጉራጌዎች ከአምደፅዮን ሰራዊት ጋር መዋጋታቸው በራሱ በአምደ ፅዮን ዜና መዋዕል ተገልጿል። የጉራጌ ሕዝብ በደቡብ እንዳሉት ሌሎች ሕዝቦች ሁሉ ነባርና ጥንታዊ ሕዝብ ነው። የጉራጌ ሕዝብ በአምደፅዮን ዘመን ከሰሜን ኢትዮጵያ መጣ የሚለው አፈታሪክ ጥሩ ተረት ነው። እኛ የምንፈልገው ግን እውነተኛ ታሪክና እውቀት ነው። የጉራጌ ሕዝብ በአካባቢው ለብዙ ሺህ ዓመታት መኖሩ የሚካድ ጉዳይ አይደለም። ፕሮፌሰር ቤርናል ለማረጋገጥ የፈለገው ይህንን እውነታ ነው። ሕዝቡ ነባርና ጥንታዊ ሕዝብ ነው። ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ በአኃዝ ለማስቀመጥ ቢያቅተንም ለብዙ ሺህ አመታት ሕዝቡ በአካባቢው ይኖር እንደነበር ማወቅ አያዳግትም። ሁኔታዎችን በሚገባ ሳይመረምሩ ይሆናል ግምት ሕዝብን ማሳሳት ግን ተገቢ አይደለም። ዛሬ ያልታወቀ ነገር ነገ ይታወቃል። ሽማግሌ ዎች የጉራጌ ሕዝብ ከቅርብ ዘመናት በፊት ከሰሜን ኢትዮጵያ ነው የመጣው ስላሉ ብቻ እንደበቂ የታሪክ መረጃ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። መመርመር አለበት። ያንን ለማጥናት ስነዘዴ ያስፈልጋል። ጊዜው በውል መታወቅ አለበት። ከዚያ በኋላ እውቀት ይሆናል። እውቀትን ሸሽተን በእምነት መንገድ እንጓዝ ከተባለ ሰው የፈለገውን ማመን ይችላል። ታሪክ ከሆነ ደግሞ በጠንካራ ማስረጃ ማስደገፍ

ያስፈልጋል። ከሰሜን የመጡ ወራሪ ነገሥታት ጉራጌዎችን ወግተው አስገብረዋቸዋል። ከአምደ ጽዮን ጀምሮ የሰሜን ኢትዮጵያ ነገሥታት የጉራጌን ሕዝብ በተከታታይ ወግተውታል። በዚያን ወቅት የጉራጌ ሕዝብ የራሱ ቋንቋ፥ የራሱ ባህል፥ የራሱ ሃይማኖት ነበረው። ከወረራ በኋላ ጉራጌዎች ክርስትናንና እስልምናን ተቀብለዋል። የጥንቱን እምነታቸውን የያዙም አሉ። እነዚህ ሕዝቦች አሁን በአሉበት ቦታ ለብዙ ዘመናት ኖረዋል። ከሰሜን ኢትዮጵያ የመጡት ከ700 ዓመታት በፊት ነው የሚለው ሀሳብ ሚዛን አይደፋም። የሚያዋጣው ፕሮፌሰር ቤርናል ያቀረበውን ፈተና ለማለፍ ጥልቅ የታሪክ ምርምር ማድረግ ነው። ለዚህም በርትቶ ታሪክን ማጥናት ነው። አንድ ሰው ከመሬት ተነስቶ ጥሩ ብሔራዊ ስሜት ስላለኝ ታሪክ እጽፋለሁ ወይም አስተምራለሁ ቢል አያዋጣም። ብሔራዊ ስሜቱን በኪነትና በመዝሙር መግለጽ ይችላል። ስሜት ግን እውቀት አይሆንም። የታሪክ ባለሙያም አያደርግም።

## ነጮች የአፍሪካን ሥልጣኔ ከደዋል

ፕሮፌሰር ማርቲን ቤርናል የአውሮፓ ሥልጣኔ ምንጭ አፍሪካ ናት በማለቱ ነጭ ምሁራን እንደሚጠምዱት የታወቀ ነው። ጀርመኖች ሲያቀነቅኑት የነበረውን ሀሳብ ሽሮባቸዋል። የነጭን የሥልጣኔ ምንጭነት በመስበካቸው ጀርመኖች ተሳስተዋል በማለቱ ፕሮፌሰሩ ላይ ጠላቶች መነሳታቸው ግልጽ ነው። ፕሮፌሰሩ ግን የሚለው ነጮቹ የአውሮፓን ሥልጣኔ ወጥ (የመጀመሪያ) ነው ለማለት የአፍሪካን የሥልጣኔ ምንጭነት ከደዋል ነው። ለምሳሌ፥ ታላቁ የጀርመን ፈላስፋ ሔግል አፍሪካዊ ሰው ሰብአዊ ገጽታ የለውም ብሏል። ይህንን ሀሳብ የሰነዘረው በባሪያ ንግድ ዘመን ነው። ነጮች የባሪያ ንግድ ተጠቃሚዎች ስለነበሩ ጥቁር ሰብአዊ ፍጡር ነው ብለው ለመቀበል አዳግቷቸዋል። ሆኖም የዘረኝነት ውጤት ፋሽዝም መሆኑን በሒትለርና በሙሶሊኒ እብሪት ተረድተውታል። ነገር ግን ጥቅማቸው የተነካባቸው ሽማግሌ የታሪክ ምሁራን አዲሱን ሀሳብ ይቃወማሉ። በኢትዮጵያ ዓለም አቀፋዊ የጥናት ጉባኤዎች ላይ በየጊዜው የሚቀርቡ አዳዲስ ሀሳቦችና ግኝቶች ናቸው። ፕሮፌሰሩም ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነባር ሕዝብ ነው። መጤ አይደለም ነው። ሽማግሌዎቹ ነጭ ምሁራን የአፍሪካ የሥልጣኔ ምንጭነት መካዱን ይቀጥሉበታል። አባቱ ባሪያ ነጋዴ ነበር፥ ሀሰት የሚያስተምር መምህር ነበር ብለው ለማመን አይፈልጉም። እነዚህ ሽማግሌ ምሁራን የዩኒቨርሲቲያቸውን ክብር ይጠብቃሉ።





ፕሮፌሰር ቤርናል ተራማጅና ስር-ነቀል የሆነ አስተሳሰብ ያለው ምሁር በመሆኑ እውነቱን ተናገረ። ዘረኛ የሆኑ ነጭ ምሁራን ደግሞ ተቃወሙት። በመሰረቱ አንድ አዲስ ሀሳብ የነባር ፕሮፌሰሮችን ጥቅም የሚፃረር ሆኖ ከተገኘ ትምህርቱ በዩኒቨርሲቲ እንዳይሰጥ ያደርጋሉ። ፕሮፌሰሩ የተከተለው የታሪክ አጠናን ስነዘዴ ግን የማያፈናፍን ጠንካራ ስለሆነ ሀሳቡን በቀላሉ ሚፍረስ ያዳግታል። በማወናበድ ሀሳቡን በማረሳሳትም ሆነ በዲፕሎማሲ ዘዴ በመጠቀም ፕሮፌሰሩ የደረሰበትን እውነታ ለመቅበር አይቻልም። የፕሮፌሰሩ ሀሳብ በመላው ዓለም ታውቋል። ከእንግዲህም የሀሳቡን መስፋፋት ለመገደብ መሞከሩ አያዋጣም።

አፍሪካውያን የሚያስፈልጋቸው ነገር ቢኖር ስነዘዴን መማርና እውቀትን መፈልፈል ነው። የታሪክ፥ የፍልስፍና፥ የሶሺዮሎጂና የአንትሮፖሎጂ ባለሙያ ለመሆን ደግሞ ጠንክሮ መማር ያስፈልጋል። ከዚህም ሌላ በተለይ በኢትዮጵያ አውሮፓውያን እንደሚያደርጉት የ«ሊበራል አርትስ» እሳቤን መቀበል ተገቢ ይመስለኛል። ይህም ማለት የታሪክ፥ የቋንቋ፥ የፍልስፍናና የስነጽሑፍ ጠቅላላ እውቀት ማስተማር ይገባል ማለት ነው። ይህን ጠቅላላ እውቀት ከገበየን በኋላ በፈለግነው ሙያ ለመካን እንችላለን። ባለሙያ ለመሆን መማር፥ እውቀት መስብ ሰብና መመራመር ያስፈልጋል። የባህርይ ለውጥ ማምጣትም ያሻል።

## ለኢትዮጵያ ታሪክ በቂ ስፍራ አልተሰጠም

ኢትዮጵያ ከግብፅ፥ ከግሪኮች፥ ከሮማውያንና ከአረቦች ጋር የረጅም ዘመን ግንኙነት እንደነበራት የተረጋገጠ ነው። የክርስትናን፥ የኦሪትንና የእስልምናን እምነት ተቀብለናል፥ አስተናግደናል። ለእነዚህም እምነቶች ከፍተኛ ቦታ ስንሰጥ ለኢትዮጵያ ታሪክ ግን ስፍራ አልሰ ጠንም። ስለሆነም የአምላክን ነገር ለቤተ ክርስቲያንና ለመስጊድ ትተን የታሪክን ጉዳይ ወደ ትምህርት ቤት፥ ወደ ግለሰብ፥ ወደ ኅብረተሰብ እንውሰድ። ንጉሥ እገሌ ከእገሌ ተወለደ። ከእገሌ ጋር ተዋጋ፥ በጦር ሜዳ ሞተ የሚል ዜና መዋዕል የሚፈይደው ነገር የለም። የተወለደ ሁሉ ይሞታል። ይህ ምን አዲስ ነገር አለው? እኛ ማስተማር ያለብን ስለነበረው ሥርዓት፥ ተቋም፥ ላዕላይ መዋቅር፥ ታሕታይ መዋቅር፥ የአስተዳደር ድርጅትና የኢኮኖሚ ሥርዓት ነው። ይህንን ግን ዛሬ ፈትፍቶ የሚያስተምር የለም። ምግባችን ለብለብ፥ ትምህርታችንም ለብ ለብ ስለሆነ ችግር አለብን። የሰከነ ሥራ ለመሥራት የጠበቀ እውቀት ያስፈልጋል። የታሪክ ትምህርትና እውቀት ያገርና የኅብረተሰብ ግንባታ መሰረትና መሳሪያ ነውና።

# 3. የኢትዮጵያ የጂኦ-ፖለቲካ ታሪክ ግንዛቤ

## የኢትዮጵያና የአረቦች ግንኙነት ታሪክ

### *የኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔ ዕድገትና ዓለማቀፋዊ ይዘት*

የዓይነት፥ የቅርፅ፥ የመጠንና የዕድገት ደረጃ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ፥ በእንግሊዝኛ ዘእስቴት በኢትዮጵያ ቋንቋዎች በዘልማድ መንግሥት ተብሎ የሚታወቀው ድርጅታዊ ሥርዓት፥ የአንድ በሥፍራና በጊዜ የተወሰነ ምድር፥ ሕዝብና የፖለቲካ የበላይ ሥልጣን ሕጋዊ ቅንጅትና ታሪካዊ ትስስር ነው። ይህ በአንድ በተወሰነ የምድር፥ የሕዝብና የፖለቲካ የበላይ ሥልጣን ድርጅታዊ ቅንጅትና ትስስር የሚፈጠረው የመንግሥት ሥርዓት ከባህል መስፈርት አኳያ ሲታይ የሰለጠነም ያልሰለጠነም ሊሆን ይችላል። በሌላ ቃል የመንግሥት ሥርዓት ማዕከላዊ ባህርይና መግለጫ የፖለቲካ ሥልጣን ነው። በመሆኑም ሥልጣኔ ማለትም የተወሰነ የባህል ዓይነትና የዕድገት ደረጃ የመንግሥት ሥርዓት ዓይነተኛው ሚዛንና መግለጫ አይደለም ማለት ነው።

ከትርጉም ሆነ ከተግባር አኳያ ሥልጣኔ ግን የከተማና የገጠር ተግባራት ክፍፍልና ዕድገት፥ የእርሻና የንግድ ሥራዎች፥ የግል መሬት ይዞታ፥ የጽሕፈትና የገንዘብ አገልግሎት የመታወቂያ ገፅታዎችና መግለጫዎች የሆኑበት አንድ ባህላዊ የኅብረተሰብ ሥርዓት ወይም አንድ ማኅበራዊ የዕድገት ደረጃ ነው። በዚህ አጭር ትርጉም መሠረት መንግሥት የሥልጣኔ ቅድመ ሁኔታ ነው፤ ሥልጣኔ ግን የመንግሥት ቅድመ ሁኔታም ገላጭ ባህርይም አይደለም። ሕዝብ ያለ መንግሥት ሊኖር ይችላል። መንግሥት ግን ያለ ሕዝብ አይኖርም።

በዚህ መሠረት፥ የኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ የአክሱም የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ሃይማኖቶች ኅብረተሰብ አንድ በተወሰነ ሥፍራና ታሪካዊ ወቅት የአንድ የተወሰነ መሬት ሕዝብና የፖለቲካ የበላይ ሥልጣን ሕጋዊ ቅንጅትና ድርጅት በመሆኑ አንድ ሉአላዊ መንግሥት ነው። እንዲሁም አንድ ባህላዊ የእርሻ፥ የከተማ፥ የንግድ፥ የዕደጥበብ፥ የግል ሀብት፥ የሕግ፥ የጽሕፈትና የገንዘብ ሥራዎች፥ ድርጅቶችና አገልግሎቶች ያሉት ማኅበረሰብ በመሆኑ አንድ ሥልጣኔ ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ የሚለው አባባል ትክክለኛ ግንዛቤና አባባል ነው።

የኢትዮጵያና የአረቦችን ታሪካዊ ግንኙነት በሚመለከት፥ በመቀሌ ከተማ ኅዳር 27 እና 28 ቀን 1990 (1998) በተካሄደው «እስሐማ ነጃሺ ሲምፖዚየም» ላይ ከደራሲው በተሰጠው የጂኦ-ፖለቲካና የታሪክ





ሌክቸር እንደተገለጸው፥ የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በአራቱ አጎራባች የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕርና የአረቢያ እስትራቴጂያዊ አካባቢዎች በሥፍራና በጊዜ አድጎና ተስፋፍቶ በሁለቱ ጥንታዊና አጎራባች የኢትዮጵያና የአረብ ሕዝቦች መካከል በሥፍራ፥ በጊዜ፥ በንግድ፥ በቋንቋ፥ በባህል፥ በፖለቲካ፥ በሃይማኖትና በታሪክ የጠበቀና የጠለቀ ግንኙነት እንዴት እንደፈጠረ ብሎም ከ610-661 ባሉት አምሳ ዓመታት በተፃራሪ የውስጥና የውጭ ኃይሎች ላይ ለአረቦቹ እስላማዊ ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ዓለም አቀፋዊ ትግልና ድል በኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት የተደረገው ታሪካዊ የድል አስተዋፅኦ እንደሚከተለው ቀርቧል።

### *የኢትዮጵያ የ550-1300 የታሪክ መረጃ ያልተገኘበት 'ጨለማ' ዘመን*

በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ በግምት ከ550 እስከ 1300 ድረስ፥ ለስምንት ምዕተ ዓመታት በቤተ መንግሥትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን የተጻፈ የታሪክ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም። በሌላ በኩል በዚህ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ፦ (1) የአክሱም ሥልጣኔ ፈርሷል። (2) የክርስትና ሃይማኖት በቀይ ባሕርና በዓባይ ወንዝ መካከል በኃይል ተስፋፍቷል። (3) የአገው (ዘአገው) የክርስቲያን መንግሥትና የገዥ መደብ (1100-1270) ተነስቶ ወድቋል። (4) በአክሱማውያኑ ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች በግምት በተከዜና በዓባይ ወንዞች መካከል፥ «ሰሜን» እና «ወልቃይት» ተብለው በሚታወቁ ጥንታዊና አዋማዊ ሕዝቦች አገር፥ በአንድ በኩል ሃይማኖተ ኦሪትን የሚከተል ብሎም ራሱን «ሰለሞናዊ አይሁድ» ነኝ እያለ የሚጠራ፥ በሌላ በኩል ደግሞ በአጎራባች ሕዝቦች «ፈላሻ» (መጤ፥ ባዕድ) ተብሎ የተሰየመ አንድ አዲስ አገርና መንግሥት ተከስቷል። (5) እንደ ሰሜን/ፈላሻም ራሱን «ሰለሞናዊ አይሁድ» ነኝ ብሎ የሚጠራ አዲሱ የአማራ መንግሥትና የገዥ መደብ ተከስቷል። (6) በተጨማሪም ከአገር ውጭ በአረቢያ የአክሱሙ መንግሥት የባሕር ማዶ ግዛትና ገበያ ተደምስሷል። (7) በአጎራባቹ የአረቢያ ምድር አዲሱ ዓለማቀፋዊ የእስላም ሃይማኖትና መንግሥት ተነስቶ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተስፋፍቷል። (8) በደቡብ ኢትዮጵያ እስላማዊ ሃይማኖትና መንግሥት በኃይል ተስፋፍቷል።

በተጠቀሰው ረጅም የታሪክ መረጃ ባልተገኘበት ዘመን እነዚህና ሌሎችም ታላላቅ አገርና ዓለማቀፋዊ ሁኔታዎች፥ ኃይሎች፥ ክስተቶችና እንቅስቃሴዎች በኢትዮጵያ ምድርና ቤተ መንግሥት

በሰነድ ተጽፈው አልተገኙም። ወይም ከጊዜ በኋላ ማለትም ከ14ኛው ምዕተ ዓመት ወዲህ በቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች በተረት መልክ ተቀርፀው ተገኝተዋል። በዚህ ረገድና ተግባር እንዲያውም ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖችና ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ ለመጀመሪያ ጊዜ በ14ኛው ምዕተ ዓመት በአጼ አምደጽዮን ዘመነ መንግሥት (1314-1344) በ1320 ገደማ በግዕዝ ትርጉም በክብረ ነገሥት መጽሐፍ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የገባው አዲሱ የታሪክ ትምህርት ጥንታዊ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ ጨምሮ የኢትዮጵያን ታሪክና ባህል በሙሉ ወደ ዝክረ ተረት ለውጦታል። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ራሳቸው «ሕዝብ» እና «አሕዛብ» ተብለው በሁለት ተፃራሪ ሠፈሮችና ፈርጆች ተከፍለዋል።

እጅግ በጣም የሚገርመው ነገር በዚህ «ኢትዮጵያውያን ዓለምን እረስተውና በዓለምም ተረስተው በረጅሙ ተኙ» ተብሎ በተገጠመለት ዘመን መጀመሪያ ላይ አጎራባች አረቦች፣ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ፣ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በራሳቸው ፈቃድ፣ ስንቅና ትጥቅ ከጎናቸው ተሰልፈው በነቢዩ ሙሐመድና በካሊፋዎቹ ማለትም በአቡበከር፣ በዑመር፣ በዑትማንና በዓሊ ተከታታይ አመራርና ዘመን ለአምሳ ዓመታት (610-661) ለታላቁ የእስልምና ሃይማኖት ምሥረታና ግምባታ በተፃራሪ ኃይሎች ላይ በተካሄደው ትግል ከፍተኛ ተሳትፎና የድል አስተዋጽኦ ያደረጉ ባለውለታ ሕዝብና መንግሥት ናቸው ብለው የምስክርነት ቃላቸውን ለዓለምና ለትውልድ በይፋ ሰጥተዋል።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፣ አሁን ከጊዜና ከታሪክ አኳያ ከአንድ ወገን ብቻ የተሰጠው የአረቦች የምስክርነት ቃል ታሪካዊ መነሻና ፋይዳ በምን ተጨባጭ መንገድና ሚዛን ማወቅና መግለጽ ይቻላል? የሚለው መሠረታዊ የይዘትና የግንዛቤ ጥያቄ ነው። ለዚህ ተገቢና ወቅታዊ ጥያቄ አጥጋኝ መልስ ለማግኘት ደግሞ የኢትዮጵያና የአረብ ሕዝቦችን ጥንታዊ የጂኦ-ፖለቲካ ታሪክ ማጥናትና ማወቅ አማራጭ የሌለው ቁልፍ ነገር ይሆናል።

በአጭርና በጥቅል አነጋገር የኢትዮጵያውያንና የአረቦች ረጅም ግንኙነት በዓባይ፣ በቀይ ባሕር፣ በአክሱም ሥልጣኔ፣ በጥንታዊ የሳባ የግዕዝና የአረብ ቋንቋዎች፣ በቅዱስ ቁርአን፣ በእስልምና ሃይማኖትና በጥንታዊ የአረብ ጸሓፊዎች ትምህርት መሠረቶችና መጣሪያዎች የተገነባ የሁለቱ አጎራባች ሕዝቦች ሕልውናዊ አንድነትና ትስስር እንደ ሆነ የሚከተለው ረጅም የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል።





*የኢትዮጵያና የአረቦች የጂኦ-ፖለቲካ ታሪክ*

ኢትዮጵያውያንና አረቦች፣ ከጥንት ከቅድመ ታሪክ ጀምሮ፣ ለብዙ ሺህ ዓመታት በቀይ ባሕር ጂኦ-ፖለቲካ ተሳስረው የሚኖሩ አጎራባች ሕዝቦች ናቸው። ጂኦ-ፖለቲካ በአንድ አገር፣ በአንድ አካባቢ ሕዝብ ጉዳዮች ላይ እንደአካባቢውና እንደዘመኑ ተጨባጭ ሁኔታ መሠረታዊ የዕድገት አስተዋፅኦ ሊያደርግ ወይም አፍራሽ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል የጂኦግራፊ፣ የእስትራቴጂ፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታዎች መግለጫና መስተጋብር ነው። በዚህ ረገድና ተግባር የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ ጂኦ-ፖለቲካ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በአካባቢው ሕዝቦች ሕይወትና ዓለማቀፋዊ ሁኔታና ሂደት ላይ መሠረታዊ የልማት አስተዋጽዖና የአፍራሽ ተጽዕኖ መፈራረቅ ሊያስከትል እንደኖረ ከታሪክ መረጃና ትምህርት ይታወቃል።

በጥንት ዘመን፣ በግምት ከ2800 ዓመተ ዓለም እስከ 615 ዓመተ ምህረት ድረስ ለ3430 ዓመታት በቀይ ባሕርና በዓባይ ሸለቆ ጠረፎችና የንግድ መስመሮች ጥንታዊ ግብፃውያን፣ ሳባውያን፣ ግሪኮች፣ ሮማውያንና አረቦች በየዘመናቸው በንግድ፣ በሃይማኖትና በባህል ከሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ጋር ለረጅም ዘመን የነበራቸው ጂኦ-ፖለቲካዊ ግንኙነት ለኢትዮጵያ ጥንታዊ የፑንታውያን፣ የደአማታውያንና የአክሱማውያን ሕዝቦችና መንግሥታት የዕድገት አስተዋፅኦ እንዳደረገ ከታሪክ መረጃና ጥናት ይታወቃል። በመሆኑም በ615-661 በአረብ ሙስሊሞችና በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች መካከል የተከሰተው ታሪካዊ ግንኙነት ራሱ በሁለቱ አጎራባች ሕዝቦች መካከል ለረጅም ዘመን የነበረው የጂኦ-ፖለቲካ ግንኙነት አንድ ማስረጃና ምሳሌ ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር፣ ከዛሬ 3500 ዓመታት በፊት የኖረው የአይሁድ አስተማሪና ጸሐፊ ነቢዩ ሙሴ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 10፣ ቁጥር 6-20 ላይ በታችኛው ዓባይ ሸለቆ፣ በላይኛው ዓባይ ሸለቆ፣ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካና በአረቢያ የነበሩ ሕዝቦችን በቅደም ተከተል ግብፅ፣ ኩሽ፣ ፑንትና ሳባ በተሰኙ ስሞች ገልጿል። ዛሬ በዘመናችን ማለትም ከ1800 ዓመተ ምህረት ጀምሮ በሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ ከከርሰ ምድር በአርኪኦሎጂ ጥናት የተገኙ ጥንታዊ የግብፅ የሃይሮግሊፊክስ ጽሑፎች የእነዚህ ሕዝቦችን ታሪክ በሚመለከት ብዙ ተጨማሪ መረጃዎችን ሰጥተዋል።

ከዚህ አኳያ፣ በጥንታዊ ግብፅና ፑንት መካከል በንግድ፣ በባህልና በሃይማኖት መስኮችና መንገዶች ከ2800 እስከ 1000 ዓመተ ዓለም ድረስ ለ1800 ዓመታት የቆየ የንግድ ግንኙነት እንደነበር

ከተጠቀሱት የሃይሮግላፊክስ መረጃዎች በትክክል ታውቋል።

በግምት ከ1000 ዓመተ ዓለም ገደማ ጀምሮ የተጠቀሰው የግብፅና የፑንት ጥንታዊ የዕጣን፥ የከርቤ፥ የሙጫና የቀረፋ ቅመማ ቅመም ንግድ በትክክል ባልታወቁ ምክንያቶች ከተቋረጠ በኋላ በ1000-500 ዓመተ ዓለም ባለው ዘመን ውስጥ በአንድ በኩል በሰሜን መሀል ደጋ በሚገኘውና «የሀ» ተብሎ በሚጠራው አገር የኢትዮጵያ አዲሱ የደአማት ዘውዳዊ መንግሥት፥ በሌላ በኩል ደግሞ በአጎራባቹ ደቡብ አረቢያ እንዲሁም በዕጣን፥ በሙጫ፥ በከርቤና በቀረፋ ምርትና ንግድ የተሰማሩ ሚና፥ ሳባ፥ ቀጣባንና ሃድራማዊ የተባሉ የአረብ አናሳ መንግሥታት ተከስተዋል።

በኢትዮጵያውያንና በተጠቀሱት አረቦች መካከል የመጀመሪያው ታሪካዊ ግንኙነት በደአማትና በሳባ ሉአላዊ መንግሥታት መካከል በዓመተ ዓለም በ4ኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ ለአጭር ዘመን ተጀምሮ እንደነበር የሚያሳዩ ሰነዳዊ መረጃዎች ተገኝተዋል።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በአንድ በኩል በኋላ ለአክሱማውያኑ የግዕዝ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት መነሻ በሆነው የደአማት ጥንታዊ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት ጎን የሳባ ሐውልታዊ የቁም ጽሕፈት ተገኝቶ ባልታወቀ ምክንያትና መንገድ በአንድ ምዕተ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጠፍቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከደአማት ነገሥታት አንዱ ማለትም «ድል አድራጊው ንጉሥ ለመነ» በዜና መዋዕሉ ራሱን «የደአማታውያን፥ የሳባውያን፥ የአበራውያን፥ የቀዮችና የጥቁሮች ንጉሥ»፥ አገሩን ደግሞ «ከምስራቅ እስከ ምዕራብ» በማለት እንዲሁም «አስቴር፥ ሀበስ፥ እለሙቀሀ፥ ደተሀመ፥ ደተበአደአነ» የተሰኙ አዋማዊ አማልክቱን ዘርዝሮ በማሳወቅ በዘመኑ የነበረ የኢትዮጵያ የዘውዳዊ መንግሥትን የሕዝቦች፥ የቋንቋዎች፥ የባህሎችና፥ የሃይማኖቶች ብዝትና አንድነት ባጭርና በጥልቅ አስረድቷል።

በኢትዮጵያ የደአማት መንግሥትና ሥልጣኔ፥ እንዲሁም በደቡብ አረቢያ በዕጣን፥ በሙጫ፥ በከርቤና በቀረፋ ምርትና ንግድ የተሰማሩ የአረብ አናሳ መንግሥታት በየአገራቸው በዕድገት እንቅስቃሴ ላይ እንዳሉ፥ በሌላ በኩል ደግሞ በዓመተ ዓለም ከ6ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በላይኛው የዓባይ ሸለቆ፥ በጥንቱ የኩሽ/ኑቢያ አገር አዲሱ የሚሮዌ መንግሥት ተከሰተ። ከ525-405 ዓመተ ዓለም በታችኛው የዓባይ ሸለቆ ግብፅ የፋርሳውያን ግዛት ሆነ። ቀጥሎም በ332-30 ዓመተ ዓለም ግብፅ የግሪኮች ግዛት ሆነ። በመጨረሻ ከ30 ዓመተ





ዓለም እስከ 642 ዓመተ ምህረት ድረስ ለሰባት ምዕተ ዓመታት የሮማውያን ግዛት ሆነ።

ባጭርና በጥቅል አነጋገር በግብፅ የግሪኮ-ሮማውያን ተከታታይ ግዛቶች በአንድ በኩል በላይኛው ዓባይ ሸለቆ በሚሮዌ ላይ እንዲሁም በደቡብ አረቢያ በአረብ መንግሥታት ላይ የውድቀት ተፅእኖ አስከተሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለኢትዮጵያ ተከታታይ የደአማት-አክሱም መንግሥታት የዕድገትና የመስፋፋት አስተዋፅኦ እንዳደረጉ የታሪክ መረጃና ጥናት ያሳያል።

ከዚህ አኳያ፥ በ332 ዓመተ ዓለም በታላቁ እስክንድር መሪነት የግሪክ ጦር ግብፅን ከፋርሶች ከያዘና በታላቁ እስክንድር ስም የእስክንድርያ መዲና ከተቆረቆረች በኋላ በሚቀጥሉት 300 ዓመታት ውስጥ በግብፅ ምድር ላይ ቶለማውያን የተባሉ የግሪክ ነገሥታት ተነሱ። በግብፅ ቶለማውያን ነገሥታት በዘመኑ በዕጣን ምርትና ንግድ በዓለም ታዋቂ የነበረውን ደቡብ አረቢያን ከጎን በመተው ለንግድና ለአደን ተግባራት ትኩረታቸውን በአፍሪካ ምድር በቀይ ባሕርና በኤደን ባሕረሰላጤ ጠረፎች ላይ አደረጉ።

በዚሁ ሁኔታና ወቅት፥ በቀይ ባሕር ዳርቻ፥ የኢትዮጵያ የአዱሊስ ወደብ በሜድትራኒያን ባሕርና በሕንድ መካከል የተስፋፋው ዓለማቀፋዊ የግሪክ ንግድ፥ ቋንቋ፥ ባህልና ሥልጣኔ ኬላ፥ ማዕከልና መናኸሪያ ሆኖ አደገ። ማለትም የአዱሊስ ወደብ ለአክሱም መንግሥት እና ሥልጣኔ የመካከለኛው ምስራቅና የሜዲትራኒያን ሥልጣኔዎች የመግቢያ በርና መንገድ ሆነ።

በመጨረሻ በ30 ዓመተ ዓለም ማለትም በዘመነ-ክርስትና መባቻ ሮማውያን ግብፅን ከግሪኮች ያዙ። በዚህ በግሪኮ-ሮማውያን ዓለማቀፋዊ ሽግግር ዘመን በላይኛው ዓባይ ሸለቆ ጥንታዊው የኑቢያ-ሚሮዌ መንግሥትና ሥልጣኔ እንዲሁም በአጎራባቹ አረቢያ የሚና፥ የሳባ፥ የቀጣባን፥ የሃድራማዊ፥ የሂሚያሪትና የሃምዳና አረብ መንግሥታት በየበኩላቸው በራሳቸው ውስጣዊና አካባቢያዊ ምክንያቶችና ግፊቶች ሁሉም ባፋጣኝ የውድቀት ሁኔታዎችና ሂደቶች ላይ ነበሩ።

*በዘመነ እስልምና ዋዜማ በአካባቢው የዓለም ኃያላን መንግሥታት አሰላለፍ*

ከላይ የተዘረዘሩት የዘመኑ ታላላቅ አካባቢያዊና ዓለማቀፋዊ ክስተቶች፥ ሁኔታዎችና ሂደቶች የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕር፥ የአረቢያና የመካከለኛው ምስራቅ እስትራቴጂያዊ አገሮችን ለሦስቱ የሮማውያን፥ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን አፄ መንግሥታት ቅርብና ክፍት የገበያ የግዛትና የተፅእኖ አካባቢዎችና መስኮች አደረጉዋቸው።

## የኢትዮጵያ ነገሥታትና ወታደሮች በአረቢያ

በግምት ከ175 እስከ 225 ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ በአረቢያ እርስ በርሳቸው የግዛትና የሥልጣን ጠላት በሆኑ የሃምዳን፥ የሳባ፥ የሂሚያሪት፥ የቀጣባንና የሃድራማዊ አረብ መንግሥታትና የጦር አበጋዞች መካከል በተካሄደው ረጅም ጦርነት አገሮቹ በኃይና በሥልጣን እንጃዎች ተለያይተው ሲዋጉ «የሀበሾችና የአክሱማውያን ነገሥታት» ከሚሉዋቸው ገደረት፥ ዋዜባና አድባ አንድ ጊዜ የፖለቲካና የመሣሪያ እርዳታ ሲፈልጉ በሌላ ጊዜ ደግሞ ጊዜያዊ የአረብ ኅብረት ፈጥረው ከኢትዮጵያኑ ጋር ሲዋጉ ይታያሉ።

በመጨረሻም በ220ዎቹ የሂሚያሪታውያኑ አናሳ መንግሥት የተቀሩ ባላንጣ መንግሥታትን በውልም በውጊያም ተቆጣጥሮ ከዛፋሩ መዲናው በኢትዮጵያውያኑ የግዛት ተፅዕኖ ሥር አንድ ጠንካራ የሂሚያሪት-ሳባ ጥምር የአረብ ኃይል መሠረተ።

በሌላ በኩል «የሀበሾችና የአክሱማውያን» መንግሥት በአረቢያ የቀይ ባሕርን ምሥራቃዊ የጠረፍ ክልል በሰሜን ምዕራብ ከሂጃዝ፥ ከአሲርና ከቲሃማት ክልል ጀምሮ በደቡብ ምስራቅ እስከ ኤደን ወደብ ድረስ ማለትም የሂጃዝ-የመን ጠረፎችን በሙሉ በመቆጣጠር በምድ ርም በባሕርም ላይ ለሚቀጥሉት ምዕተ ዓመታት የደቡብ አረቢያ የበላይ ኃይልና ሥርዓት ሆነ።

በተጠቀሰው ዘመን የአክሱሙ የአጼ መንግሥት የአራቱ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ የዓባይ ሸለቆ፥ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አጎራባች ሕዝቦችና አገሮች የበላይ ኃይል ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ታሪክ ላይ የታወቀው በታላቁ የአዱሊስ ሐውልት ጽሑፍ ነው። የዚህ የአዱሊስ ሐውልት ጽሑፍ የጸሐፊው ስም ሆነ ጽሑፉ የተጻፈበት ዘመን እስከ ዛሬ ድረስ በትክክል አልተረጋገጠም።

ይሁን እንጂ ጽሑፉ የተጻፈበት ዘመን በሁለተኛው ምዕተ ዓመት «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት» አረቢያን ከገዛበት ጊዜ በኋላና በ4ኛው ምዕተ ዓመት በ330 ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ዘመን በፊት እንደሚሆን በኢትዮጵያ የዘመኑ ታሪክ ታዋቂ ምሁራን ይገምታሉ።

የዚህ የአዱሊስ ጽሑፍ ግኝትና ቅጅ አስመልክቶ የግሪክ-ግብፅ ጸሐፊ ኮስማስ ከ525 የአዱሊስና የአክሱም ከተሞች ጉብኝቱ መልስ እንደጻፈው፥ በተጠቀሰው ዓመት አጼ ካሌብ የጽሑፉን ቅጅ አስገል ብጦ እንዲልክለት አባስ ለተባለ የአዱሊስ ገዥ ትእዛዝ ይሰጣል። በታሪክ አጋጣሚ በዚህ ጊዜ ጸሐፊው ኮስማስ ሚናስ ከተሰኘ ጓደኛው ጋር በንግድ ሥራ ምክንያት በአዱሊስ ከተማ ነበር። በመሆኑም አገረ





ገዢው አባስ ግሪክ-ግብፅ ጸሐፊዎቹን ከሐውልቱ ጽሑፍ ለአጼ ካሌብ የሚልከውን ቅጅ እንዲያዘጋጁለት ጠየቃቸው። ጸሐፊዎቹም የጽሑፉን ሶስት ቅጂዎች አዘጋጅተው አንዱን ለአገረገዥው ሰጡ። የተቀሩትን ለራሳቸው አንዳንድ ወሰዱ። ኮስማስ የራሱን ቅጅ *የኮስማስ የክርስቲያን ቶፖግራፊ* በተሰኘ መጽሐፉ ገልብጦ ለትውልድና ለታሪክ መረጃ አስተላለፈ። ነገር ግን ኮስማስ የጽሑፉን ደራሲ ስም ሆነ የተጻፈበትን ዘመን ባለመጻፉ መቼና በማን ተጻፈ የሚለው ቁልፍ የታሪክና የጊዜ ጥያቄ እስከ ዛሬ ድረስ አልተመለሰም።

ባጭሩ የታላቁ የአዱሊስ ጽሑፍ ርዕሰ ነገሮች በጽሑፉ ገፅ ሆነ ያዘዙት በማይታወቅ ዘመን በአንድ በስሙ በማይታወቅ የአክሱም ንጉሥ በአራቱ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፥ በዓባይ ሸለቆ፥ በቀይ ባሕርና በአረቢያ አካባቢዎች በ30 በሚቆጠሩ አገሮች ላይ በምድርና በመርከብ ያካሄዳቸው ጦርነቶች ናቸው። ከዚህ አኳያ፥ በመጀመሪያ ዘመቻ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በሰሜኑ ደጋአምባ ክልል በግምት በመረብ ወንዝና በጣና ሐይቅ መካከል በሚገኘው ምድር ንጉሡ ግዕዝ፥ አጋሜ፥ ስግዱ፥ አድዋ፥ ቲአሞ፥ ጋምቤላ፥ ዘንጋበነ፥ አንገበ፥ ትአማ፥ አገው (አታገው)፥ ከለና ሰሜን የሚላቸውን አሥራ ሁለት አዋሳኝ አገሮችንና መንግሥታትን አስገበራቸው።

በሁለተኛው ዘመቻ በግምት በቀይ ባሕር፥ በአትባራ ወንዝ፥ በኑቢያ-ሚሮዌና በግብፅ መካከል ለዘን፥ ዘአ፥ ገበለ፥ አታለሞ፥ ቤጃና ተንገናይቴ (ታካ) የሚላቸውን ስድስት የተለያዩ የቤጃ አገሮችንና ማኅበ ረሰቦችን በማስገበር የመንግሥቱን የሰሜን ምዕራብ ወሰን በላይኛው የዓባይ ሸለቆ እስከ የሚሮዌና የግብፅ ጠረፎች ድረስ አስፋፋ።

በሦስተኛው ዘመቻ ጠረኛው ንጉሥ በክፍለ አህጉሩ ከትግራይ ደጋአምባ በደቡብ ምስራቅ በግምት ከአዋሽ ሸለቆ እስከ ቀይ ባሕርና የኤደን ባሕረሰላጤ ድረስ ባለው ቆላማና በጥንቱ ዓለም በዕጣን ምርትና ንግድ በታወቀ የትሮጅሎዳውያንና የበርበራውያን ምድር አነን፥ ምጣን፥ ሰለአ፥ ሮሳይና ሶላቴ የተሰኙ አምስት የቆላ ሕዝቦ ችንና አገሮችን አስገበራቸው።

በአራተኛውና በመጨረሻው ዘመቻ የንጉሡ ጦር በእግርና በመርከብ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በአረቢያ ረጅም ምዕራባዊ ጠረፍ ዳርቻ ላይ በሰሜን ምዕራብ ክልል በሚገኘው በሂጃዝ-አሲር አገር በዘመኑ የሮማውያን ይዞታ ከነበረ ከለኡኮመ ወደብ ጀምሮ በመሀል፥ በምስራቅና በደቡብ አረቢያ እስከ ሳባ-ሂሚያሪት ጠረፎች እስከ ባቤልመንደብ ሰርጥ አካባቢ ድረስ ሙሉ ዘመቻ በማካሄድ በዘመኑ በሂጃዝ-አሲር ጠረፍ ኪናይዶኮልፕቴና በሂሚያሪት ጠረፍ አራብቴ

የተሰኙ ሁለት አስትራቴጂያዊ አገሮችን የመንግሥቱ የባሕር ማዶ ግዛቶች አድርጎ በቀጥታ ያዘ። በዚህ ረገድና ተግባር ከዚህ በፊት «በሀበሾችና በአክሱማውያን ነገሥታት» ገደረት፣ ዋዜባና አድባ ዘመን በደቡብ አረቢያ በየመን ጠረፍ ሀበሻ የተባለ የኢትዮጵያውያን ግዛት እንደነበር አይዘነጋም።

የአዱሊሱን ታሪካዊ ጽሑፍ ከጻፈው ንጉሥ ቀጥሎ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ በዓባይ ሸለቆ፣ በቀይ ባሕርና በአረቢያ አጎራባች አካባቢዎች የኢትዮጵያ መንግሥትን በቅደም ተክተል በ4ኛውና በ6ኛው ምዕተ ዓመታት በኢኮኖሚ፣ በድርጅት፣ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በዲፕሎማሲና በትጥቅ ከጥንቱ ኩሻዊ የግብፅና የኑቢያ መንግሥታት በኋላ የአፍሪካ ታላቁ ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት አድርገው የገነቡት ሁለት አጼ ነገሥታት ኢዛና (320-344) እና ካሌብ (493-534) ናቸው።

በዚህ ረገድና ተግባር የኢትዮጵያ የመጨረሻው አዋማዊና የመጀመሪያው ክርስቲያን ንጉሥ የሆነው አጼ ኢዛና በኢትዮጵያና በአረቢያ በግሪክ፣ በግዕዝና በሳባ ጥንታዊ ቋንቋዎች በተጻፉ ዜና መዋዕሎች (1) «ሰዎቼ» እያለ የሚጠራቸው መሀራ፣ ሀራ፣ ደመወ፣ ፈልሀ፣ ፅራእ፣ ህሌን፣ ምጤን፣ ዳጤን፣ ለኬንና ሰብራት የተባሉ የጦር ድርጅቶች፣ (2) «አባቶቼ» የሚላቸው አርስ፣ መሕርም፣ አስ ተር፣ ብሔር፣ ምድር፣ የሰማይ አምላክ፣ ክርስቶስ፣ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ተብለው በልዩ ልዩ ስሞችና ቋንቋዎች የሚታወቁ የውጭና የአገር ውስጥ አማልክት እንደነበሩት፣ (3) እንዲሁም «ግዕዝ»፣ «ካዕብ»፣ «ሣልስ»፣ «ራብዕ»፣ «ሐምስ»፣ «ሳድስ»፣ና «ሳብዕ»፣ የተሰኙ የኢትዮጵያ የቋንቋ ድምፅ፣ ንግግርና ንባብ ሥዕላዊ ምልክቶች ለመጀመሪያ ጊዜ በዘመነ መንግሥቱ እንደተገኙ የሰነዶች ጥናት ያሳያል።

በተጨማሪም በተጠቀሱት የድንጋይ ላይ ጽሑፎች «የአክሱም፣ የሂሚያር፣ የረይዳን፣ የኢትዮጵያ፣ የሀበሻ፣ የሰልሂን፣ የፅያሞ፣ የቤጃ፣ የካሱ፣ ንጉሠ ነገሥት የድል አድራጊው መሕርም ልጅ» የሚለው የአጼ ኢዛና የአገርና የመንግሥት ስም ንጉሡ በ4ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በ330ዎቹ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ከመግባቱ በፊት የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት የአራቱ አጎራባች የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ የዓባይ ሸለቆ፣ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አገሮች ሉአላዊ የበላይ ኃይልና ሥርዓት እንደሆነ ያመለክታል።

ከእነዚህ ከኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ግዛቶች ሂሚያር፣ ረይዳን፣ ሀበሻ፣ ሳባና ሰልሂን የመንግሥቱ አምስት የአረቢያ ግዛቶች፣ እንዲሁም ፅያሞ፣ ቤጃና ካሱ የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ





ግዛቶች፣ አክሱምና ኢትዮጵያ ደግሞ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በሰሜኑ ደጋአምባ ላይ የአጼው መንግሥት የማዕከላዊው ከተማና አገር ስሞች ናቸው።

ከአጼ ኢዛና ዘመን 200 ዓመታት በኋላ በ530ዎቹ «የአክሱም፣ የካሱ፣ የረይዳን፣ የሳባ፣ የሰልሂን፣ የትአሞ፣ የየመን፣ የቲሃማት፣ የራባም፣ የቤጃ፣ የኖባ፣ የአራባት፣ ንጉሥ» የሚለው የአጼ ካሌብ የአገርና የመንግሥት ስም በሁለቱም የአፍሪካና የእስያ አጎራባች አህጉራት የኢትዮጵያ መንግሥት ከአጼ ኢዛና ዘመን የበለጠ እንደተስፋፋ በግልጽ ያሳያል።

በአጼ ካሌብ ዜና መዋዕል ከተጠቀሱ ግዛቶች ረይዳን፣ ሳባ፣ ሰልሂን፣ የመን፣ ቲሃማት፣ ራባምና አራባት ስባት የኢትዮጵያ መንግሥት የአረብ ግዛቶች ናቸው። በዘመኑ ቲሃማት በሰሜን ምዕራብ ጠረፍ ከሂጃዝ በደቡብ ምስራቅ ጠረፍ እስከ የመንና ከዚያም ባሻገር ያለው ረጅም የደቡብ አረቢያ ምዕራባዊ ጠረፍ አጠቃላይ ስያሜ ነው። ካሱ፣ ትአሞ፣ ቤጃና ኖባ ደግሞ፣ ከሦስቱ ተከታታይ የአዱሊስ ሐውልት፣ የአጼ ኢዛናና የአጼ ካሌብ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች እንደሚታወቀው፣ በቤጃና በሚሮዌ ሕዝቦችና አገሮች ላይ እየሰፉ የመጡ የኢትዮጵያ መንግሥት የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ ግዛቶች ናቸው።

*የአይሁዶች ጠርነትና የኢትዮጵያ ግዛት በየመን አረቢያ*

የኢትዮጵያን ጥንታዊ የታሪክ መረጃ ዓይነትና ብዛት በሚመለከት፣ በግምት ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ ባለው በ1000 ዓመታት ዘመን ውስጥ በአራቱ ጥንታዊ የደአማት፣ የሳባ፣ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎች በድንጋይ ላይ የተጻፉና በ500 የሚቆጠሩ ጥንታዊ ጽሑፎች ከ1804 እስከ 1981 ድረስ በሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ፣ በአረቢያ፣ በሱዳንና በግብፅ በድምሩ ከ50 በሚበልጡ የተለያዩ ታሪካዊ ሥፍራዎች በ30 በሚቆጠሩ ምሁራን እና ተመራማሪዎች ተገኝተው ለጥናትና ምርምር አገልግሎት መዋላቸውን በ1982 በኢትዮጵያ ባህል ሚኒስቴር የጥንታዊ ጽሑፎች ተመራማሪ ምሁር ፕሮፌሰር ሮገ ሽናይደር ለዚህ ጸሐፊ በሰጡት ማስታወሻ አስታውቀዋል።

በእነዚህ ቁልፍና ወሳኝ የታሪክ መረጃዎች መሠረት፣ በ330 ዓመተ ምህረት በሁለት የሶሪያ ስደተኞች ፍሬምናጦስና አዴስዮስ አማካይነት የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ አዋማዊ ቤተ መንግሥት ከመግባቱ በፊት በአገሪቱ ምድርና ታሪክ የይሁዳውያኑ የእሪት ሃይማኖት አልተገኘም። ቀጥሎም በ5ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ

(470-550) ዘጠኙ ግሪክ-ሮማውያን ስደተኛ ቅዱሳን አረጋዊ፥ ጽንጠ ሌዎን፥ ገሪማ፥ ሊቃኖስ፥ ይምአታ፥ ዕሕማ፥ ጉባ፥ አፍጼና አሌፍ በአክሱም ከተማ በአንድ በኩል መጽሐፍ ቅዱስን ለመጀመሪያ ጊዜ ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተረጎሙ። በሌላ በኩል ደግሞ የገዳም ተቋምና ሥርዓት መሠረቱ። የጻድቃኑ የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስና ሥነ ጽሑፍ ከገዳም ሥርዓት ጋር በኢትዮጵያ ለሁለቱም የክርስትናና የእሬት ሥርዓቶች የመነሻ መሠረት ይሆኗሉ። ከሰባት አሥርታት በኋላ በ615 የአረብ ስደተኞች ደግሞ እስልምናውን ማለትም ሦስተኛውን መለኮታዊ ሃይማኖት ወደ አክሱም ያስገባሉ።

ከዚያ በፊት አክሱማውያንና ሮማውያን ክርስትናን በየበኩላቸው በየመን አረቢያ በማስተማር አስፋፉት። ይሁን እንጂ በ517 በየመን አረቢያ የነበሩት ተፃራሪ የአይሁድ ኃይሎች በማዝሩቅ ዙኑዋስ መሪነት በኢትዮጵያ፥ በአረብ፥ በሮማዊያንና በሌላም አገር ክርስትያኖች ላይ የማጥፋት ጦርነት ከፈቱ። በመሆኑም በ517 እና በ525 የአክሱሙ ንጉሥ አጼ ካሌብ በሁለት ተከታታይ ዘመቻዎች የአይሁዶችን አመጽ ደምስሶ በየመን የአክሱም መንግሥትን የባሕር ማዶ አስተዳደር (525-577) መሠረተ።

በ517-525 የአይሁዶች ጦርነት ጊዜ ከአረቢያ ብዙ ሕዝቦች ሱማፋ አሸዋን የተባለ አዋማዊ የሂሚያር መስፍን ጨምሮ በስደት ወደ አክሱም እንደሄዱ ታውቋል። በ525 አጼ ካሌብ የአይሁዶችን አመጽ ከደመሰሰ በኋላ ሱማፋ አሸዋንን የክርስትና ልጁና በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት ንጉሥ እንደራሴ (525-535) አድርጎ አነገ ሠው። በተጨማሪም ከንጉሥ ሱማፋ አሸዋን ጎን የአገሩን ጸጥታና ነፃነት እንዲጠብቅ በአንድ የጦር አበጋዞች ጉባኤና ትእዛዝ የሚመራ የጦር ሠራዊት በየመን አሰፈረ።

በ535 በየመን አንድ አብረሃ የተባለ የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት አዛዥ ንጉሥ ሱማፋ አሸዋንን በኩዴታ ገልብጦ ራሱን «የሳባ፥ የዴሁ ረይዳን፥ የሃድራማዊ፥ የየመን፥ የቲሃማት፥ የደጋና ቆላ አረቦች ንጉሥ አብርሃ የነገደ ግዕዝ ተወላጅና አዝማች» በማለት በ535-558 አነገሠ።

የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ የደቡብ አረቢያ መዲናን ከጥንቱ የሂሚያር-ሳባውያኑ የዛፋር ከተማ በስተሰሜን ከማሪብ የውሃ ግድብ ከተማ አጠገብ አዲሱን የሰንዓ ከተማ አሠርቶ ወደዚያ አዛወረ። በተጨማሪም የሰንዓ ካቴድራል ጨምሮ በየመን ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሠራ። እንዲሁም የማሪብን ጥንታዊ የውሃ ግድብ በከፍተኛ ወጪ አድሶ ገነባ። የሰሜንና የምዕራብ አረቢያ አካባቢዎችንና ነገዶችን ከየመን አረቢያ ጋር አዋህዶ አንድ ጠንካራ





የአረብ አገርና መንግሥት ለመገንባት በፋርስና በባይዘንታይም ተፃራሪ ኃይሎች ላይ ብዙ ያልተሳኩ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ትግሎችን እንዳካሄደ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያሳያል።

ይህም ሁሉ ከሆነ በኋላ፥ በ558 ንጉሥ አብርሃ ሞተ። በመሆኑም ከ558 እስከ 577 ድረስ በየመን አረቢያ በንጉሡ ልጆችና በተከታዮቹ መካከል ረጅም የሥልጣንና የእርስ በርስ ጦርነት ተካሄደ። በመጨረሻ በ577 የአረብ አማፅያን ከፋርሳውያን ባላንጣ ኃይሎች ወታደራዊና የፖለቲካ እርዳታ አግኝተው የኢትዮጵያ ሰፋሪ ኃይሎችን ከየመን አረቢያ አባረሩ። ነገር ግን ፋርሳውያን የኢትዮጵያ ጥገኛ የነበረውን የሂሚያር-ሳባውያኑን የአረብ መንግሥት ደምስሰው የመን አረቢያን በጦር በመያዝ በቀጥታ መግዛት ጀመሩ።

### *የኢትዮጵያውያኑ የ577-610 የሂጃዝ አረቢያ ሰፈራና የእስልምና ክስተት በመካ*

በ577 የኢትዮጵያውያኑ የየመን አረቢያ ግዛት ውድቀት በሚቀጥሉት ሦስት አሥርታት ውስጥ በአንድ በኩል በየመን አረቢያ ላይ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ሕይወት ፈጣን ውድቀትን በሌላ በኩል ደግሞ በሰሜን ምዕራብ አረቢያ በቲሃማት ጠረፍ ክልልና በመካ የመሀል ሀገር ከተማ ፈጣን ልማትና ዕድገትን አስከተለ።

በዚህ ወቅት ከየመን አረቢያ የተፈናቀሉ ብዙ የኢትዮጵያ ሰፋሪ ነጋዴዎች፥ ወታደሮች፥ የዕደጥበባት ባለሙያዎች፥ ሠራተኞች እና ባሮች በሰሜን ምዕራብ አረቢያ የጠረፍና የመሀል ሀገር ከተሞች በተለይም በመካው የንግድና የ360 ጣኦታት ከተማ በብዛት እንደሰፈሩ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያሳያል። በዚህ ረገድና ተግባር የመካን የንግድና የሃይማኖት ከተማ ክፍለ ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ እንደገነቡ ከሚነገርላቸው ከነቢዩ ሙሐመድ አብደላህ (470-632) አራቱ እውቅ ጎሳዎች የአብድሸምስ ልጆችና ተወላጆች በምዕራብ አቅጣጫ ቀይ ባሕርን ተሻግረው ከኢትዮጵያ ጋር፥ የአል-ሙጠሊብ ልጆችና ተወላጆች በደቡብ አቅጣጫ ከየመን ጋር፥ የሀሺም ልጆችና ተወላጆች በሰሜን የባይዘንታይም ግዛት ከነበረው ሶሪያ ጋር፥ የነውፈል ልጆችና ተወላጆች በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ከኢራቅ-ፋርስ ጋር ድንበር ዘለል ንግድ ያካሄዱ እንደነበር ታውቋል።

በእነዚህ አገር አቋራጭ የሲራራ ንግድ መስመሮችና ገበያዎች የተሰማሩ የመካ ቁረይሽ አረብ ከበርቴዎችና ባለሥልጣኖች በ610ዎቹ ሦስቱ ኃያላን የባይዘንታይም፥ የፋርስና የአክሱም ተፃራሪ መንግሥታት በየፊናቸው በሚቆጣጠሩት በአረቡ በርሃማ አገርና ዓለም አዲስ

የፖለቲካ ኃይልና የገዥው መደብ ሆነው ተከሰቱ። በ610ዎቹ ነቢዩ ሙሐመድ በዚህ አዲስ የአረብ የፖለቲካ ኃይል ላይ ታላቁን እስላማዊ አመፅ አወጁ።

### *የ615-631 የኢትዮ-አረብ ሙስሊም ስደተኞች በኢትዮጵያ*

በ615-616 የመካ ቁረይሽ ከበርቴዎችና ባለሥልጣኖች በነቢዩ ሙሐመድና በተከታዮቹ ላይ የቅጣት እርምጃ በወሰዱ ጊዜ ነቢዩ ተከታዮቹን በስደት ወደ አጎራባቹ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ አዘዛቸው። በመሆኑም ከ615 እስከ 661 ድረስ በአምስት አሥርታት የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥትና ዜጎች በራሳቸው ስንቅና ትጥቅ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በተፃራሪ ኃይሎች ላይ በነቢዩ ሙሐመድና በካሊፋዎቹ አቡበከር፥ ዑመር፥ ዑስማንና ዓሊ ጎን ተሰልፈው የአረቦቹን እስላማዊ የዓለም ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ከጥፋት ለማዳን በተካሄደው ትግል ብርቱ ተሳትፎና የድል አስተዋፅኦ እንዳደረጉ የታሪኩ ባለቤት የሆኑ የአረብ መሪዎች፥ ተከታዮችና ፀሐፊዎች ለዓለምና ለትውልድ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተው አልፈዋል።

በኢትዮጵያ የ615-631 የኢትዮ-አረብ ሙስሊም ስደተኞችን የዘር ጥንቅር፥ ቁጥር፥ ሕይወትና ሥራ በሚመለከት፥ በመጋቢት 1904 በአዲስ አበባ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የቱርክን የመጀመሪያ ልዑካን ቡድን መርቶ የመጣው ሌ/ጄ ሳድቅ አልሙሊያድ አልአዝም በዓመቱ Habash Siyahetnameshi በሚል ርዕስ በቱርክኛ ቋንቋ ጽፎ በ1908 Rihlate al Habasha (The Ethiopian Voyage) ጉዞ በሚል ስም ወደ አረብኛ ቋንቋ በተተረጎመው ተወዳጅ መጽሐፍ የጥንት አረብ ሙስሊም ጸሐፊዎችን ሰነዶችበስፋትና በጥልቀት መርምሮ ብዙ አዲስና ጠቃሚ መረጃዎችን በማቅረብ በ615-661 የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በአገር ውስጥና በውጭ አገር ከነቢዩና ከተከታይ ካሊፋዎቹ ጎን ተሰልፈው ለአረቦቹ እስላማዊ ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ድልና ዕድገት ያደረጉትን ታሪካዊ አስተዋጽኦ በዝርዝር አስቀምጧል።

የቱርኩ ጄኔራል በአዲስ አበባ ቆይታው ወቅት ከሁሉ በላይ የአገራቸውን ታሪክ በወግ ለማያውቁ ለኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች የአገራቸው የጥንቱ ክርስቲያን መንግሥትና ሕዝብ ነቢዩ ሙሐመድን በእስልምና ሃይማኖት ምሥረታና ግምባታ ተግባር እንዴት በልዩ ልዩ ሥራዎች፥ መንገዶችና መሣሪያዎች እንደረዱ ለመጀመሪያ ጊዜ በማሳወቅ በእጅጉ አስደነቃቸው።

ሁለተኛ የጄኔራል አልአዝም ጥናት በ615-631 በኢትዮጵያ ከነበሩና በድምሩ በ150 ከሚቆጠሩ ሙስሊም ስደተኞች ከበረካ ኡም አይማን የነቢዩ ኢትዮጵያዊት አሳዳጊ ሞግዚት ጋር አምስት ሴቶችን





ጨምሮ ሀያ አንድ በዘርና በትውልድ ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ ያሳያል። በተጨማሪም የተጠቀሱ ኢትዮ-አረብ ሙስሊም ስደተኞች በኢትዮጵያ በቆዩበት ረጅም ጊዜ ብዙ ኢትዮጵያውያንን ወደ እስልምና ሃይማኖት እንደአስገቡ የጄኔራሉ ጥናት ጨምሮ ያመለክታል።

ሦስተኛ፥ በዚህ ረገድና ተግባር በ631 በነቢዩ ሙሐመድ ቤተ ዘመድ በጃዕፈር ሙጠሊብ መሪነት ስደተኞቹ ወደ አረቢያ በተመለሱ ጊዜ ከተጠቀሱ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ነቢዩን በትጥቅ ለመርዳት 72 ወዶዘማቾች በንጉሥ አስሐማ ወንድም ልጅ በዙ ማህጃር አልሀበሻ፥ በአረቢያ የቀድሞው ኢትዮጵያዊ ንጉሥ አብርሃ (535-558) የልጅ ልጅ አብርሃ ቢን ሰባህ አልሀበሻና በአንድ ዕውቅ የታሪክና የቅኔ ባለሙያ በዙ ማህጀር አልሀበሻ ጥምር አዝማችነት ከስደት ተመላሾቹ ጋር አብረው እንደሄዱ ተገልጿል።


ከእነዚህ ከኢትዮጵያ ከፍተኛ የመንግሥትና የጦር ሹማምንቶች አንዱ ዙ ማህጃም አልሀበሽ ለነቢዩ ሙሐመድ የኢትዮጵያና የአረብ ጥንታዊ የግንኙነት ታሪክን ያስተምር ነበር ተብሏል።

### *ኢትዮጵያና እስልምና*

ከታሪክ መረጃና ትምህርት አኳያ ሲደመደም፥ በኢትዮጵያ ምድርና ቤተ መንግሥት በግምት ከ550 እስከ 1300 ድረስ የታሪክ ሰነዳዊ መረጃ ባልተገኘበት ዘመን ውስጥ ከአገር ውጭ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች የኢትዮጵያ የታሪክ መረጃ ብቸኛ ምንጭ እንደሆኑ ታውቋል። በዚህ ረገድና ተግባር በተጠቀሰው ዘመን በግምት ከ615 እስከ 661 ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥትና ዜጎች በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ከነቢዩ ሙሐመድና ከአራቱ ተከታይ ካሊፋዎች አቡበከር፥ ዑመር፥ ዑስማንና ዓሊ ጎን ተሰልፈው በውስጥና በውጭ ተፃራሪ ኃይሎች ላይ ለታላቁ የእስልምና ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ዕድገትና ዓለማቀፋዊ መስፋፋት የድል አስተዋጽኦ እንዳደረጉ፥ ብሎም ነቢዩ ለሙስሊም ተከታዮቹ ከኢትዮጵያውያን ጋር በሰላማዊ ጉርብትና አብረውና ተከባብረው እንዲኖሩ ቋሚ የእምነት፥ የትምህርትና የፖሊሲ መመሪያ እንደሰጣቸው የዘመኑ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች ለትውልድና ለዓለም የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል። ይህ አስገራሚ ታሪክ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ አምስትና ስድስት ምዕተ ዓመታት ውስጥ በቀይ ባሕርና በአረቢያ በኢትዮጵያና በአረብ ሕዝቦች መካከል የነበረው መልካም የጂኦ-ፖለቲካ ግንኙነት ዓይነተኛ መግለጫ እንደሆነ በዚህ ጥናት በቀረበው የታሪክ መረጃና ትምህርት

ተረጋግጧል። ስለሆነም ለኢትዮጵያውያን እስልምና መለኮ ታዊ ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የታሪክ ቅርስና ውርስም ነው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ የ5000 ዓመታት ታሪክ ካርታ




ምንጭ ላጊድ ፡ ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ (1990) ።





# 4. የጦርነት ተፅዕኖ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ

## የኃይለኛ መንግሥትና የደካማ ኅብረተሰብ ግንኙነት

በኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ ኅብረተሰብ በ20ኛው ምዕተ ዓመት በአንድ በኩል የሰው ልጅን አጠቃላይ የመነሻ ታሪክ በሚመለከት ዘመናዊ የኢቮሉሽን፥ የፖሌአንቶሎጂ፥ የሊንጉስቲክስና የአርኪኦ ሎጂ ሳይንስ የእውቀትና የትምህርት አብዮት አስገኝቷል። በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በአገሪቱ የሥርዓት ለውጥ አስከትሏል። እንዲሁም በዓለም ላይ የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መሠረተ ሀሳብና ትምህርት እየተስፋፉ መጥቷል። የዘረኝነት እምነትና ትምህርት በዓለም ላይ ከኃይል ሥርዓት ጋር ውግዝና ውድቅ ተደርጓል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ለአዲስ ኅብረተሰብና ሥርዓት ምሥረታና ግምባታ አመቺ ሁኔታና ዘመን ተፈጥረዋል ለማለት ይቻላል።

ስለሆነም በፖለቲካ ተረትና በዘረኝነት ትምህርት ለዘመናት የተቀመመውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ከስልተ ምርትና ከሥርዓተ ማኅበር አኳያ፥ ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ግንኙነት አኳያ በአዲስ ሜቶዶሎጂ (ስልተ ጥናት) ከመነሻ አንስቶ እንደገና ለማጥናትና ለመገምገም አስገዳጅ የእውቀትና የትምህርት ሁኔታዎች፥ መንገ ዶች፥ መሣሪያዎችና ምክንያቶች ተፈጥረዋል። የኢንፎርሜሽን እና የእውቀት አብዮት ተካሄዷል። በዚህ ታሪካዊ ሁኔታና ዘመንI


አንደኛ፥ ከላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ጥንታዊ የጭቆና ሥርዓት በሕዝባዊ አብዮት ተወግዷል። የመንግሥት ሥልጣን ምን ጭና ባለቤት አምራቹ ሕዝብ እንደሆነ አብዮታዊ ግንዛቤ እያገኘ መጥቷል።

ሁለተኛ፥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ የእውቀትና የቴክኖሎጂ አብዮት ተካሄዷል። የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች ጥያቄ የዘመኑ ትምህርትና ሥርዓት እየሆነ መጥቷል። በመንግሥትና በሥርዓት ላይ የግለሰብ የማኅበረሰብ የሕዝብና የኅብረተሰብ ሉአላዊ በላይነት ዓለማቀፋዊ እውቅና እያገኘ መጥቷል።

ሦስተኛ፥ ባለፉት ምዕተ ዓመታት በኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ ታሪክ ላይ ተፅዕኖ ያሳደረው የውጭ ምሁራን ትምህርት በዘመናዊ የኢቮሉሽን፥ የፖሌአንቶሎጂ፥ የሊንጉዊስቲክስና የአርኪኦ ሎጂ ሳይንስና እውቀት ውግዝና ውድቅ ተደርጓል። ባጭሩ ዛሬ በኢትዮጵያ ለአዲስ ኅብረተሰብና ሥርዓት ግምባታ የውስጥና የውጭ ሁኔታዎችና ሂደቶች አመቺ ሆነው ተገኝተዋል።

ተረጋግጧል። ስለሆነም ለኢትዮጵያውያን እስልምና መለኮታዊ ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የታሪክ ቅርስና ውርስም ነው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ የ5000 ዓመታት ታሪክ ካርታ



ምንጭ ላጊድ ፣ ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ (1990) ።





## 4. የጦርነት ተፅዕኖ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ

### የኃይለኛ መንግሥትና የደካማ ኅብረተሰብ ግንኙነት

በኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ ኅብረተሰብ በ20ኛው ምዕተ ዓመት በአንድ በኩል የሰው ልጅን አጠቃላይ የመነሻ ታሪክ በሚመለከት ዘመናዊ የኢቮሉሽን፥ የፖሌኦንቶሎጂ፥ የሊንጉስቲክስና የአርኪኦ ሎጂ ሳይንስ የእውቀትና የትምህርት አብዮት አስገኝቷል። በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በአገሪቱ የሥርዓት ለውጥ አስከትሏል። እንዲሁም በዓለም ላይ የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መሠረተ ሀሳብና ትምህርት እየተስፋፋ መጥቷል። የዘረኝነት እምነትና ትምህርት በዓለም ላይ ከኃይል ሥርዓት ጋር ውግዝና ውድቅ ተደርጓል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ለአዲስ ኅብረተሰብና ሥርዓት ምሥረታና ግምባታ አመቺ ሁኔታና ዘመን ተፈጥረዋል ለማለት ይቻላል።

ስለሆነም በፖለቲካ ተረትና በዘረኝነት ትምህርት ለዘመናት የተቀመመውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ከስልተ ምርትና ከሥርዓት ማኅበር አኳያ፥ ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ግንኙነት አኳያ በአዲስ ሜቶዶሎጂ (ስልተ ጥናት) ከመነሻ አንስቶ እንደገና ለማጥናትና ለመገምገም አስገዳጅ የእውቀትና የትምህርት ሁኔታዎች፥ መንገዶች፥ መሣሪያዎችና ምክንያቶች ተፈጥረዋል። የኢንፎርሜሽን እና የእውቀት አብዮት ተካሄዷል። በዚህ ታሪካዊ ሁኔታና ዘመን፤

አንደኛ፥ ከላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ጥንታዊ የጭቆና ሥርዓት በሕዝባዊ አብዮት ተወግዷል። የመንግሥት ሥልጣን ምንጭና ባለቤት አምራቹ ሕዝብ እንደሆነ አብዮታዊ ግንዛቤ እያገኘ መጥቷል።

ሁለተኛ፥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ የእውቀትና የቴክኖሎጂ አብዮት ተካሂዷል። የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች ጥያቄ የዘመኑ ትምህርትና ሥርዓት እየሆነ መጥቷል። በመንግሥትና በሥርዓት ላይ የግለሰብ የማኅበረሰብ የሕዝብና የኅብረተሰብ ሉአላዊ በላይነት ዓለማቀፋዊ እውቅና እያገኘ መጥቷል።

ሦስተኛ፥ ባለፉት ምዕተ ዓመታት በኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀውርታዊ ታሪክ ላይ ተፅዕኖ ያሳደረው የውጭ ምሁራን ትምህርት በዘመናዊ የኢቮሉሽን፥ የፖሌኦንቶሎጂ፥ የሊንጉዊስቲክስና የአርኪኦ ሎጂ ሳይንስና እውቀት ውግዝና ውድቅ ተደርጓል። ባጭሩ ዛሬ በኢትዮጵያ ለአዲስ ኅብረተሰብና ሥርዓት ግምባታ የውስጥና የውጭ ሁኔታዎችና ሂደቶች አመቺ ሆነው ተገኝተዋል።

ከዚህ አኳያ በማንኛውም ሥፍራና ጊዜ የማኅበራዊ ለውጥና ዕድገት መነሻ ነባር ማኅበራዊ ድርጅትና ሥርዓት ነው። ከላይ እንደ ተባለው፣ ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የኢትዮጵያ ጥንታዊና በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረ ተሰብና መንግሥት የመነሻ ምድር ነው። ይህ ጥንታዊ የፖለቲካ ሥርዓት በመጨረሻ በ19ኛው ምዕተ ዓመት ክፍለ አህጉሩን ከሞላ ጎደል ከሥሩ ያማከለውና ከጥንቱ አዋማዊ የደአማት-አክሱም ሥልጣኔና መንግሥት በረጅም ታሪካዊ ሂደት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የኢትዮጵያ ዘውዳዊ ሥርዓት ነው።

ከዚህ አንፃር በክፍለ አህጉሩ ከየሀ-ደአማት እስከ አዲስ አበባ ዘመን ድረስ ባለፉት 2500 ዓመታት በደአማት፣ በሳባ፣ በግሪክ፣ በግዕዝና በአማርኛ ቋንቋዎች ተጽፎ የተገኘው የኢትዮጵያ ታሪክ በጠባብ መልኩ ሲታይ የነገሥታትና የካህናት ጥምር የፖለቲካና የሃይማኖት ዘገባ ነው። ከሰፊው የኢትዮጵያ በህውርታዊ ኅብረተሰብ ክስተትና ዕድገት አኳያ ሲታይ ደግሞ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ ነው።•የብዙ ሕዝቦች የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴዎች ታሪክ ነው። በመሆኑም የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች የመስተጋብርና የመወራረስ መግለጫ ነው።

ከሥርዓትና ከትምህርት አኳያ፣ የተጠቀሰው የኢትዮጵያ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ብዙትና አንድነት በአንድ በኩል የኅብረተሰቡን ጥንታዊነት ያሳያል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለረጅም ዘመን ዕድገትና ለውጥ ያልተካሄደበት ኋላቀር ኅብረተሰብ፣ መንግሥትና ሥርዓት መሆኑን በግልፅ ያስተምራል።

በተጨማሪም ይህ የኢትዮጵያ ጥንታዊ፣ በህውርታዊና ኋላቀር የፖለቲካ ሥርዓት የኃይለኛ መንግሥትና የደካማ ኅብረተሰብ ጥንቅር እና ቅንጅት እንደሆነ አሁንም ከታሪክ መረጃና ጥናት በግልፅ ይታያል። በዚህ ኋላቀር የፖለቲካ ሥርዓት መንግሥት የኅብረተሰቡን የኢኮኖሚ ታሕታይና የፖለቲካ ላዕላይ ድርጅቶችንና መዋቅሮችን ከሃይማኖትና ከጦር ድርጅቶች ጋር በበላይነት የሚቆጣጠርና የሚገዛ ብቸኛው ኃይል ነው። በመሆኑም መንግሥት ወይም ንጉሥ በፍጹም ሥልጣኑ የሕዝቡን ሕይወትና ንብረት እንደፈለገ ይገዛል። ለወደደው ሹመት፣ መሬት፣ ማዕረግና ክብር ይሰጣል። ከጠላው ደግሞ ይወስዳል። ሕዝቡ ግን በንጉሡ ላይ የሕይወቱንና የንብረቱን መብት የሚያስከብርበት ሕጋዊ መንገድና መሣሪያ የለውም። ምክንያቱም ንጉሡ በሕዝቡና በኅብረተሰቡ ላይ የመንግሥት ሥልጣን ምንጭና ባለቤት





ነውና። ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊ በብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ (ዝክረ ነገር) ቃል፦

*የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በሚገዛው አገር ላይ ያለው ሥልጣን በጣም የተስፋፋ ወሰን የሌለው ነው። በሥጋዊም በመንፈሳዊም ሥራ ሁሉ ይገባል። ከፍ ባለው ሥልጣኑም ይሾማል፣ ይሽራል፣ ይሰጣል፣ ይነሳል፣ ያስራል፣ ይፈታል፣ ይቆርጣል፣ ይገድላል፣ ይምራል። ይህንንም የመሳሰለውን ሁሉ ይፈጽማል።*[8]

በአጼ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ጸሐፊ እንደተባለው ደግሞ፣ ራሱን የኢትዮጵያ ሥዩመ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ የሚጠራው፦

«ንጉሥ የወደደውን ያከብር ዘንድ የጠላውን ያዋርድ ዘንድ በሚገዛው ዓለም ላይ የእግዚአብሔር እንደራሴ ነው። ንጉሡ የወደደውን ይጠላል። የጠላውን መልሶ ይወዳል። በአመጻቸው የገደላቸው ሰዎችን ልጆች ወንድሞችና ዘመዶች እያመጣ ወዳጅ ያደርጋቸዋል»[9] ይላል።

ይህንን ጠንካራ የሆነ መንግሥታዊ የንጉሥ ኃይልና ሥልጣን የፈጠረው የኢትዮጵያ ጥንታዊ የፖለቲካ ሥርዓት ጠባዩ ምን እንደ ሆነ፣ ከምን ዓይነት የምርት ግንኙነት የወጣ እንደሆነ፣ መቼና በምን ሁኔታ እንደሚለወጥ ብሎም በኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ሕይወትና ዕድገት ላይ ምንዓይነት ተፅዕኖ እንዳስከተለና እንደሚያስከትል ለማወቅ የሥርዓቱን የኢኮኖሚ ታሕታይና የፖለቲካ ላዕላይ ድርጅቶችና መዋቅሮች ማጥናትና ማወቅ የግድ ይሆናል።

የተገለጸው ሥርዓት የጋርዮሽ ሥርዓት ነው እንዳይባል የተመለከተው ኅብረተሰብ በማኅበራዊ የሥራ ክፍፍልና የግል ሀብት መሠረት ለዘመናት በመደብ የተደራጀ የገዥና የተገዥ ኅብረተሰብ ነው። የባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ነው እንዳይባል ደግሞ የተጠቀሰው ኅብረተሰብ የምርት ግንኙነት የባሪያ ምርት ግንኙነት ሳይሆን የነፃ ዜጎች፣ አገርና ኅብረተሰብ ነው። የፊውዳሊዝም ሥርዓት ነው እንዳይባልም መሠረታዊ የፊውዳሊዝም ገጽታዎች ማለትም ከመሬት ጋር ተያይዘው የመንቀሳቀስና የምርጫ ነፃነት የሌላቸው ገባሮች መደብ፣ በግል መሬትና ጦር ተደራጅተው መደባዊና ሕጋዊ ጥቅማቸውን በገባሩና በመስፍኑ ላይ ማስከበር የሚችሉ የመሬት ከበርቴዎች መደብ፣ በገጠርና በከተማ መካከል ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍልና ሥርዓታዊ ቅራኔ፣ እንዲሁም በከተማ የተደራጁ የንግድና የዕደጥበብ ማኅበረሰቦች መደብ ከላይ በተመለከተው የኢትዮጵያ ንጉሣዊ ኅብረተሰብ ዘንድ ማኅበራዊና መደባዊ ህልውና የለውም።[10]

---

[8] ማህተም ሥላሴ፣ ዝክረ ነገር፣ (1962)፣ ገፅ 52።

[9] ተክለ ሥላሴ፣ የሱስንዮስ ታሪክ፣ ም 48፣ ቁ 223

[10] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፣ የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ (1982)፣ ገፅ 291-92።

ይህን በጋርዮሽ ሆነ በባሪያ አሳዳሪው ወይም በፊውዳል ሥርዓት ሥልተ ምርትና ሥርዓተማኅበር መልክና ደረጃ የማይመደ በውን ጥንታዊና ኋላቀር ኅብረተሰብ ካርል ማርክስ «እስያዊ» ወይም «ምሥራቃዊ»[11] ስልተ ምርትና ሥርዓተ ማኅበር ብሎ ይመድበዋል።

የዚህ የምሥራቃዊ ስልተ ምርትና ኅብረተሰብ ገላጭ ባህርያት ብዙና መሠረታዊ[12] ናቸው። ለትምህርታዊ ግንዛቤ ያህል የኅብረተሰቡ መሬት የመንደርና የቤተሰብ ይዞታ ነው። በሥርዓቱ መሠረት መሬትም፥ መንደርም፥ ቤተሰብም፥ ሁሉም የመንግሥት ማለትም የንጉሡ ይዞታ ነው። የግል መሬት ይዞታ እንዲሁም የግል ሀብት ሕግ የለም። ኅብረተሰቡ ጥንታዊ የገጠር ኅብረተሰብ ነው። የገጠር መንደሮች በኢኮኖሚና በፖለቲካ ራስገዝ አካባቢዎች ናቸው። በገጠርና በከተማ መካከል የሥራ ክፍፍልና ሥርዓታዊ ቅራኔ ገና አልዳበረም። የኅብረተሰቡ የኢኮኖሚ መሠረት የመንደር እርሻና ዕደጥበብ ቅንጅት ነው። ዘመናዊ ሳይንስና የምርት ቴክኖሎጂ የለም። በመንግሥትና በሃይማኖት መካከል ልዩነት የለም። ሙያዊና ማህበራዊ የሥራ ብዛት፥ ልዩነትና ክፍፍል ገና ያልዳበረ በመሆኑ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሸቀጥ ምርትና ልውውጥ የለም። በፖለቲካ፥ በሃይማኖት፥ በአስተዳደር፥ በኢኮኖሚ፥ በገንዘብ፥ በመከላከያና በኮንስትራ ክሽን ሥራዎችና መስኮች በንጉሥ የሚገዛ መንግሥት የኅብረተሰቡ የበላይ ተቆጣጣሪ ጌታ[13] ነው።

ነገሥታትና ካህናት የኅብረተሰቡ ገዢዎችና አስተማሪዎች ናቸው። በኅብረተሰቡ ዘንድ በግል ሀብትና በማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል የተመሠረተ መደባዊ ልዩነትና ሥርዓታዊ ቅራኔ ገና ያልዳበረ በመሆኑ በእስያዊ ወይም በምሥራቃዊ ኋላቀር ሥልተምርትና ሥርዓተማህበር በአንድ በኩል ኅብረተሰባዊ ዕድገትና ለውጥ ሰረጅም ዘመን አይታይም። ከፍተኛ የዕድገትና የለውጥ ቅራኔ የለበትም። በሌላ በኩል ግን የፖለቲካ፥ የመንግሥት፥ የነገሥታትና የሥርወ መንግሥት ዕድገት፥ ለውጥ፥ ውድቀት፥ ሽብር የዘወትር ክስተት ነው። በሌላ አባባል የፖለቲካና የመንግሥት ዕድገትና ለውጥ ማኅበራዊ የኅብረተሰብ ዕድገትና ለውጥ አይደለም ማለት ነው።

ካርል ማርክስ እንዳስቀመጠው፥ በእስያዊ ወይም በምሥራቃዊ ኅብረተሰብ ዘንድ ይህንን መንቲያ የሆነ ሥርዓታዊ ገፅታ የሚያስረዱ

[11] K. Marx, Capital, Vol. 1 Part 4, Chap. 15, Sec. 4; K. Marx, Pre-Capitalist Economic Formation, ed. E. J. Hobsbawm (1972), pp. 79-83.

[12] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፥ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፥ ገፅ 295-96።

[13] Marx, Capital, I, pp. 333-34.





ቁልፍ ነገሮች በተጠቀሰው ኅብረተሰብ በየመንደሩ ራስ ገዝ የሆኑና ሁልጊዜም ከጦርነትና ከሌላም አደጋ በኋላ በቶሎ ተመልሰው የሚያድጉ ትንንሽ የገጠር ማኅበረሰቦች ያላቸው፥ ነገር ግን በቅርፅ፥ በይዘትና በዕድገት ደረጃ የመሻሻል ለውጥ የማይታይባቸው፥ የምርት አደረጃጀት መንገዶችና መግለያዎች ናቸው። ባጭርና በጥቅል አነጋገር፥ በተጠቀሰው ጥንታዊ የምስራቅ ኅብረተሰብ ዘንድ ዘወትር የሚካሄደው የመንግሥት ለውጥ ሆነ የፖለቲካ ሽብር ወይም ጦርነት በኅብረተሰቡ የኢኮኖሚ መሠረትና አደረጃጀት ላይ የዕድገት ለውጥ አያስከትልም።[14] በሌላ ቃል፥ ፖለቲካም ሆነ ጦርነት ወይም ሃይማኖት በኅብረተሰቡ ዘንድ በትምህትና በምርት ቴክኖሎጂ ሥርዓት ላይ ለውጥ እና ዕድገት ለማምጣት እስካልቻለ ድረስ በመሠረታዊ የኢኮኖሚ፥ የባህልና የማኅበራዊ ሥርዓቶችና መስኮች ላይ ለውጥና ዕድገት እንደማያስከትል የተጠቀሰው ስልተ ምርትና ሥርዓተ ማህበር በግልፅ ያሳያል።

በአንድ ሌላ የጀርመን ምሁር በፕሮፌሰር ማርክስ ዊትፎጌል ዝርዝር ጥናትና ግኝት መሠረት፥ የተጠቀሰው ምሥራቃዊ ስልተ ምርትና ሥርዓተማኅበር የኃይለኛ መንግሥትና የደካማ ኅብረተሰብ ቅንብርና ቅንጅት ነው።[15] በሥርዓተ ማህበሩ መንግሥት የኅብረተሰቡ ፍጹም ገዥና ጌታ ነው። ሃይማኖትና ጦር የመንግሥቱ ማለትም የንጉሡ የግል መግለያዎች ናቸው። ሰዎች የመንግሥት ገባሮችና አሽከሮች ናቸው። የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶች ትምህርትና ጥያቄ ከሥርዓተ ማኅበሩ ጋር አብሮ አይሄድም። ሕዝብና ኅብረተሰብ የመንግሥትን ንጉሣዊ አስጨናቂና አፋኝ ኃይል የሚቆጣጠርበት ሕጋዊ መሠረት፥ መንገድ፥ መግለያ የለውም። በመሆኑም የፖለቲካ አመፅና ጦርነት የሥርዓቱ ዓይነተኛ ገፅታዎች ናቸው። ኅብረተሰቡ የሚገዛው በሕግና በሰላም ሳይሆን በኃይልና በአመፅ ግፊት ነው።

በካርል ማርክስ ጥናትና ግኝት መሠረት፥ በማኅበራዊ ዕድገት ገና ሙሉ በሙሉ ወደ ፊውዳላዊ ደረጃ ያልደረሰው የዚህ ኋላቀር ምሥራቃዊ ሥልተ ምርትና ሥርዓተ ማኅበር ሁለት ዓይነተኛ ምሳሌዎች ጥንታዊ የሕንድና የቻይና መንግሥታትና ኅብረተሰቦች ናቸው። በእነዚህ ጥንታዊ ኅብረተሰቦች ዘንድ የውጭ ወረራም ሆነ የውስጥ ጦርነት ወይም ዘወትር የሚከሰቱ የረሃብና የተፈጥሮ አደጋዎች በኅብረተሰቡ ጥንታዊ የኢኮኖሚ መሠረትና አደረጃጀት ላይ፥ በራስገዝ የመንደር እርሻና ዕደጥበብ ቅንጅት ላይ፥ በአሮጌ የምርት ኃይሎችና

[14] Ibid., p. 358.

[15] K. A. Witfogel, Oriental Despotism: A Comparative Study of Total Power, (1959), p. 271.

የምርት ግንኙነት ላይ የዕድገት ለውጥና መሻሻል አያስከትሉም። በመሆኑም በተጠቀሱ ጥንታዊ የሕንድና የቻይና ኅብረተሰቦች ዘንድ ለዘመናት በአሮጌ የምርት ኃይሎች ሆነ የምርት ግንኙነቶች ላይ የለውጥና የዕድገት ሁኔታዎች፣ እንቅስቃሴዎችና ሂደቶች አልተገኙም።[16]

ነገር ግን በ19ኛው ምዕተ ዓመት የምዕራቡ ኢንዱስትሪያዊ ኮሎኒያልዝምና ኢምፔሪያሊዝም በሸቀጥ ንግድና በትምህርት መሣሪያዎች የሕንድ-ቻይና መንግሥታትንና ኅብረተሰቦችን ጥንታዊ የኢኮኖሚ መሠረትና የአደረጃጀት ስልት በማናጋትና በማጥፋት ለዘመናዊ ሳይንስ፣ የምርት ቴክኖሎጂ፣ የጦርና የመገናኛ መሳሪያዎች፣ የገንዘብ እና የሸቀጥ ገበያ መንገድና በር በመክፈት ለመሠረታዊ የስልተ ምርትና የሥርዓተ ማኅበር ለውጥና ዕድገት እንዴት አመቺ ሁኔታ እንደፈጠሩ ካርል ማርክስ ጨምሮ አሳይቷል።[17]

የኢትዮጵያ ጥንታዊ የፖለቲካ ሥርዓትና ንጉሣዊ ሥልጣን በይዘትም ሆነ በአደረጃጀት ስልት ወይም በተግባር በጀርመን ምሁራን ማርክስና ዊትፎጌል ከተገለጸው ጥንታዊ የምስራቅ ስልተ ምርት እና ሥርዓተ ማህበር በዓይነት ልዩ አይደለም። በዚህ የኢትዮጵያ ምሥራቃዊ የዘውድ ሥርዓትና መንግሥት ሥር ነው ሦስቱ መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስትና፣ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁርአን ጋር በሰላማዊ መንገድ ወደ አገር ውስጥ በመግባትና መንግሥታዊ የእምነት፣ የትምህርትና የባህል ተቋማት፣ መሠረቶችና መሣሪያዎች በመሆን ባለፉት 1700 ዓመታት ውስጥ የተስፋፉት። የተጠቀሱ ሃይማኖቶች በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ የሥልተ-ምርትና የሥርዓተ-ማህበር ለውጥ አላስከተሉም። ነገር ግን በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በባህልና በዕድገት ደረጃ በተለያዩ የኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች መካከል ለአገራዊና ለባህላዊ መስተጋብርና መወራረስ ድርጅታዊ ኃይሎችና መሣሪያዎች በመሆን ታሪካዊ ሚና እንደ ተጫወቱ የማይካድ ሀቅ ነው።

## የመንግሥትና የሃይማኖት ግንኙነት

ከላይ እንደተባለው፣ በኢትዮጵያ ሦስቱ መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስትና፣ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች የተስፋፉትና የኖሩት በኅብረተሰቡ ዘንድ የመንግሥት የፖለቲካ መሣሪያዎችና አገልጋዮች ሆነው ነው። በዚህ ረገድና ተግባር፣ በጥንታዊ የደአማት፣ የሳባ፣

[16] K. Marx and F. Engels, On Colonialism, (1974), pp. 19-44, 81-8.

[17] Ibid., pp. 40-41, 81-87.





የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎች ተጽፈው ከክርስ ምድር በቅርቡ በአርኪኦሎጂ ጥናት በተገኙ ጽሑፎች መሠረት፣ በ330ዎቹ ዓመተ ምህረት መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስትና ሃይማኖት በግሪኮ-ሮማውያን አስተማሪዎች አማካይነት ወደ አገሪቱ እስኪገባ ድረስ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ምድር፣ ሕዝብ፣ መንግሥት፣ ሃይማኖትና ሥልጣኔ አዋማዊ እንደ ነበር ተረጋግጧል። በ5ኛው ምዕተ ዓመት መጽሐፍ ቅዱስ ከግሪክ ቋንቋ በዘጠኙ ግሪኮ-ሮማውያን ጻድቃን ወደ ግዕዝ ከተተረጎመ በኋላ ግን የአሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች በኢትዮጵያ አዋማዊ አገርና መንግሥት በአንድነት እንደተስፋፉ በአጠቃላይ መልክና መንገድ ይታወቃል። ነገር ግን ከዚህ አኳያ፣ በግምት ከ550 እስከ 1300 ድረስ በዘመኑ የተጻፈ የሰነድ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ በአገሪቱ ውስጥ ስላልተገኘ የሃይማኖቶቹ የዕድገትና የስርጭት ዝርዝር ታሪክ በትክክል አይታወቅም።

በሌላ በኩል በተጠቀሰው ዘመን ውስጥ ሦስተኛው መለኮታዊና አሀዳዊ የእስልምና ሃይማኖት ከአረቢያ በሙስሊም ስደተኞች አማካይነት በ615 በሰሜን ኢትዮጵያ በአክሱም ቤተ መንግሥትና አገር ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተሰበከ ቀጥሎም ከ896 እስከ 1270 ድረስ በአረብ አስተማሪዎችና ነጋዴዎች አማካይነት በሰላማዊ መንገድ ገብቶ በደቡብ ኢትዮጵያ በፍጥነት እንደተስፋፋ ከታሪክ መረጃ ተረጋግጧል።[18] ባጭሩ በኢትዮጵያ፣ እንደ ኅብረተሰቡም፣ የዓይነትና የደርጃ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ፣ ሁሉም ሃይማኖቶች የመንግሥት አገልጋይ መሣሪያዎች ናቸው።

በ14ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በአጼ አምደፅዮን (1314- 44) ዜና መዋዕል በዝርዝር እንደተጻፈው፣ ሦስቱም የክርስትና፣ የአሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች በቅድም ተከተል በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ሦስት የተለያዩ የመንግሥት ሃይማኖቶች ነበሩ። የዘመኑ የታሪክ መረጃና ትምህርት በስፋት እንደሚያመለክተው፣ ከትምህርትና ከተግባር አኳያ፣ ሃይማኖቶቹ በአንድ በኩል ስተጠቀሱት መንግሥታትና ነገሥታት ፍጹም የፖለቲካ መሣሪያዎች እና አገልጋዮች ነበሩ። በሌላ በኩል ደግሞ በሚያገለግሉዋቸው መንግሥታት ሥር ብዙ ተከታይ ምዕመናን ነበሩዋቸው። በተጨማሪም መንግሥታቱ በየበኩላቸው በመሬት፣ በግዛትና በንግድ ጥያቄ እርስ በርሳቸው በዘወትር ጦርነት ውስጥ ነበሩ። የመንግሥታቱ ጦርነት በሕዝቦች መካከል ጥፋትና መለያየት ሲፈጥር ሶስቱ መለኮታዊ ሃይማኖቶች ግን በየአካባቢያቸው በኢትዮጵያ በሀውርታዊ አገርና

[18] J. Couq, L'Islam in Ethiopia, (1981).

ቋንቋ ወደ ግዕዝ እንደተረጎሙና እንዲሁም የገዳምና የምንኩስና ሥርዓት በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደመሠረቱ አይረሳም።

ከዚያ በኋላ በ1337-1450 በተጠቀሱ ጻድቃን የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስና የገዳም ትምህርት መሠረት፣ የኢትዮጵያ እዎስጣጤዎሳውያን የተባሉ የገዳም መነኩሳትና መምህራን ለመጀመሪያ ጊዜ ከክርስትና ሃይማኖትና ትምህርት ጎን የአሪትን ሕግና ሃይማኖት በመላው የሰሜን ኢትዮጵያ ደጋአምባ ክልል በአራቱ የትግሬ፣ የአገው፣ የአማራና የሰሜን/ፈላሻ አጎራባችና ተዛማጅ ማኅበረሰቦች ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ እንደገነቡ ተረጋግጧል።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፣ በመሬት፣ በግዛትና በሥልጣን ጥያቄ ባላንጣ የሆኑ ሰሜን/ፈላሾችና የክርስቲያን ኃይሎች በተከዜ- ዓባይ እስትራቴጂያዊ ለምና ሰፊ ምድር ከ1316 እስከ 1632 ድረስ ለ316 ዓመታት ሲዋጉ እንደኖሩና በመጨረሻም ኦሪታዊ የሰሜን/ፈላሻ መንግ ሥት ሠርፀድንግልና ሱስንዮስ በተባሉ ክርስቲያን የአማራ ነገሥታት አመራር በዘመናዊ የነፍጥና የመድፍ መሣሪያዎች እንደተደመሰሰ፣ ሕዝቡም ከመሬቱ ተነቅሎ በተወሰኑ መንደሮች ብቻ በዕደጥበብ ሙያው እንዲኖር እንደተደረገ የዘመኑ ታሪክ መረጃና ትምህርት ያሳያል።

ከታሪክና ከጊዜ አኳያ፣ ከ1316 እስከ 1632 ድረስ በኦሪታዊ የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና በክርስቲያን የአማራ ነገሥታት አምደጽዮን፣ ዳዊት፣ ይስሐቅ፣ ዘርዓያዕቆብ፣ ባዕደማርያም፣ እስክንድር፣ ናኦድ፣ ልብነ ድንግል፣ ገላውዴዎስ፣ ሚናስ ሠርፀድንግልና ሱስንዮስ መካከል የተካሄዱ ጦርነቶች ከ1270 እስከ 1974 ድረስ ለ700 ዓመታት በክፍለ አህጉሩ በኢትዮጵያ አዋማዊ፣ እስላማዊና ኦሪታዊ ሕዝቦችና በክርስቲ ያን ነገሥታት መካከል ከተካሄዱ ጦርነቶች ለዓይነት ብቻ የሚጠቀሱ ናቸው። በዚህ ረገድና ተግባር፣ የተጠቀሱት ነገሥታትና የጦር አበጋዞቻቸው፦

(1) በግምት ከ1270-1577 ድረስ ለ300 ዓመታት በኢትዮጵያ እስላማዊና አዋማዊ የሸዋ፣ የሀዲያ፣ የወርጂ፣ የይፋት፣ የዳዋሮ፣ የአራባቢኒ፣ የሻርካ፣ የባሌ፣ የደራ፣ የአዳል፣ የሞራ፣ የለበከላ፣ የሀገራ፣ የፈድሴ፣ የግደድ፣ የነገብ፣ የዘባ፣ የሁብት፣ የተርሳ፣ የእይም፣ የሐርላ፣ የእልብሮ፣ የዜይላ፣ የእስቴ፣ የአርጎባ፣ የፈጠጋር፣ የሐረር፣ የስልጤ፣ የጉራጌ፣ የአውሳ፣ የዶባ፣ የዋጅ፣ የሶማሌ፣ የከምባታ፣ የጋሞ፣ የወላይታ፣ የጋፋት፣ የጀንጀሮ (የም)፣ የዳሞት፣ የቦሻ፣ የእናርያ፣ የቢዛሞ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ በሥፍራና በጊዜ ያልተቋረጡ ጦርነቶችን በማካሄድ የሕዝቦቹንና የመንግሥታቱን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የመከላከያ፣ የሃይማኖት፣ የባህል ሥርዓቶችንና ድርጅቶችን እንዳጠፉ በነገሥታቱ ዜና መዋዕሎች[25] በዝርዝር ተመልክቷል።

(2) በ1524-1543 ኢማም አሕመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚ (ግራኝ) ባካሄደው የአመፅ ጦርነት ኦሪታዊ ሰሜን/ፈላሻን ጨምሮ የመላ ክፍለ አህጉሩን እስላማዊና አዋማዊ ሕዝቦችን በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ አስተባብሮ፣ በ1543 ለክርስቲያኑ መንግሥት እርዳታ ከሕንድ በመጡ የፖርቱጋል ነፍጠኞች እስኪገደል ድረስ፣ በክርስቲያኑ መንግሥትና ጦር ላይ ታላቅ የአጸፋ ጉዳት እንዳደረሰ ታውቋል።[26]

(3) የኢማም አሕመድ ግራኝ የአመፅ ጦርነት በክርስቲያን ኃይሎች ላይ ካደረሰው ውድቀት ሌላ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለአዋማዊ የኦሮሞ ማኅበረሰቦች ፍልሰትና ሰፈራ ብሎም በክፍለ አህጉሩ ለታላቁ የ1520-1620 የሕዝቦች እንቅስቃሴ በርና መንገድ ከፈተ።[27]

በዚህ ረገድና ተግባር፣ በተለይ ከላይ የተጠቀሱ የ1270-1577 ጦርነቶች በደቡብ ኢትዮጵያ በሁለቱ ተፋላሚ የክርስቲያንና የእስላም ኃይሎች ላይ የጋራ ሽንፈትና ውድቀት ከደረሰባቸው በኋላ፣ ከክፍለ አህጉሩ የደቡብ ምስራቅ ቆላማ አካባቢ በታላቅ የፍልሰትና የሰፈራ እንቅስቃሴ የተነሱና ገዳ በተሰኘ ልዩ የጎሳ ሥርዓት የሚመሩ የኦሮሞ ዘላን ማኅበረሰቦች በረጅም ጦርነት የተዳከሙ የክርስቲያንና የእስላም ባላንጣ ኃይሎችን በቀላሉ ተቆጣጥረው[28] በክፍለ አህጉሩ የደቡብ፣ የምስራቅ፣ የመሀል፣ የምዕራብና የሰሜን ለምና ሰፋፊ አካባቢዎች በሃዋሪነት በመስፈር ጥቂት ጊዜ ውስጥ ለዛሬው የኢትዮጵያ ብሀውርታዊ ሕዝቦች ኅብረተሰብ፣ መንግሥትና ታሪክ ዕድገት የራሳቸውን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።[29]

(4) ሁለቱ ተከታታይና ተዛማጅ የ1524-1543 የኢማም አሕመድ ግራኝ የአመፅ ጦርነትና የ1520-1620 ታላቁ የሕዝቦች የፍልሰትና የሰፈራ እንቅስቃሴ በሰሜን ኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግሥትና ኅብረተሰብ

---

[25] Huntingford, Amda Seyon; J. Perruchon, tr. and ed., Les Chroniques de Zara Yaqob et de Baeda Maryam, (1893); Conti Rossini, Sarsa Dengil.

[26] Arab Faqih, Conquete.

[27] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፣ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ ገፅ 2159-17795-96

[28] Bahrey, History of the Gallas; Conti Rossini, Sarsa Dengil; ተክለ ሥላሴ የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ።

[29] ለምሳሌ በ1994 የኢትዮጵያ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መሠረት፣ በ9 ክልሎች ከተቆጠረው ከአገሪቱ 49,000,000 ሕዝብ፣ 17,000,000 የኦሮሞ ቋንቋ ማኅበረሰብ ሲሆን፣ በ2ኛ ደረጃ 16,000,000 ደግሞ የአማራ ቋንቋ ማኅበረሰብ ነው። በሃይማኖት በኩልም በ16ኛው ምዕተ ዓመት ሙሉ በሙሉ አዋማዊ ከነበረው የኦሮሞ ሕዝብ፣ በ1994፣ 9,000,000 ክርስቲያን፣ 8,000,000 እስላም፣ 800,000 ደግሞ አዋማዊ እንደሆነ ተመልክቷል።

የፖለቲካ ጉዳይ ሆነ።

በተጠቀሱ የክርስቲያን ኃይሎች የአሪታዊ፣ የእስላማዊና የአዋማዊ ሕዝቦች ፖሊሲና ፖለቲካ መሠረት፣ ከ1580 እስከ 1632 ድረስ የሰሜን/ፈላሻ መንግሥት በፖርቱጋልና በቱርክ ነፍጥና መድፍ በታጠቁ በአጼ ነገሥታት ሠርፀድንግልና ሱስንዮስ ሠራዊቶች ከ300 ዓመተ ምህረት ጀምሮ ለ1300 ዓመታት በስነድ ታውቆ በኖረባቸው በሰሜኑ አምባዎችና ሸለቆዎች «የአይሁድ» መንግሥት ነው ተብሎ በይፋ ተደመሰሰ። ሕዝቡም በሙሉ ከመሬቱ ተነቅሎ በአገሩ ለአሸና ፊው ኃይል ገባርና ባሪያ ተደረገ። ሃይማኖቱም በንጉሥ አዋጅ ተሰረዘ። እንዲሁም በጎንደር፣ በትግራይና በሸዋ የክርስቲያን አገሮች በዘልማድ «ጀበርቲ» ተብለው የሚታወቁ የአማራ፣ የአገውና የትግሬ ሙስሊሞች የመሬት ባለቤቶች እንዳይሆኑ፣ በመንግሥት ሥልጣንና ሥራ እንዳይሳተፉ የአምልኮ ቦታና ቤትም እንዳይኖራቸው ተደረጉ።

ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱ የኦሮሞ ማኅበረሰቦች በየአካባቢያቸው በቁጥርም፣ በህብትም በጦር ኃይልም በጎንደር፣ በትግራይና በሸዋ በተጠቃሽ የክርስቲያን ኃይሎች ላይ ለረጅም ዘመን ከፍተኛ የኃይል ሚዛን ስለነበራቸው፣ በ19ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ የአውሮፓ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ፣ የንግድና የትምህርት ወኪሎች ከዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ጋር ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በተጠቀሰው የኃይል ሚዛን ጉዳይ ላይ መሠረታዊ ለውጥ እስኪያስከትሉ ድረስ፣ የክርስቲያን ኃይሎች ከሦስቱ አጼ ነገሥታት ቴዎድሮስ፣ ዮሐንስና ምኒልክ በፊት፣ የመሬትና የሃይማኖት ፖሊሲያቸውን በፈረስ ጦር በታወቁ ኦሮሞዎች ላይ ለመተግበር በፍጹም አልቻሉም። በዚህ ረገድና ተግባር፣ አጼ ቴዎድሮስ በኅዳር 1862 ለእንግሊዝ ንግሥት በጻፉት ደብዳቤ፤

«እስከ ዛሬ ድረስ አባቶቼ ነገሥታቱ ፈጣሪአችንን ቢበድሉት መንግሥታቸውን ለጋላና ለቱርክ አሳልፎ ሰጥቶባቸው ነበር። ዛሬ ግን እኔ ከተወለድኩ ፈጣሪዬ ከአመድ አንስቶ ኃይል ሰጥቶ ባባቶቼ መንግሥት አቆመኝ። በእግዚአብሔር ኃይል ጋሎችን አስለቅቄአቸው ቱርኮች ግን ያባቴን መሬት ልቀቁ ብላቸው እምቢ ብለውኝ በእግዚአብሔር ኃይል ይኸው ልታገል ነኝ»[33] በማለት ባጭርና በግልፅ ያስቀመጡት ነገር የታሪኩን እውነታና ታላቅነት በትክክል ይገልጻል።

ባጭርና በጥቅል ለማስቀመጥ፣ ከጎንደር፣ ከትግራይና ከሸዋ ታሪካዊ የክርስቲያን ክልሎች ከላይ በተመለከተው የክርስቲያን ኃይሎች የፖለቲካ ትምህርት መሠረት፣ በተከታታይ በተነሱ በአጼ

[33] S. Rubenson, King Tewedros of Ethiopia (1966), p. 48.






ነገሥታት ቴዎድሮስ፣ ዮሐንስና ምኒልክ የዘውዳዊ ምዕክልና ፖሊሲና ፖለቲካ በተፈጠረው የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብና መንግሥት የተከሰቱ የሥርዓት፣ የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል፣ የትምህርት፣ የብሔረ ሰብና የመደብ ሁኔታዎችና ኃይሎች፣ ቅራኔዎችና ግፊቶች በአንድነት ተደምረው ባጭር የታሪክ ዘመን ውስጥ የ1974 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮትን አስከተሉ።

አብዮቱ በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ ከጥንት ጀምሮ የነበረውን የኃይለኛ መንግሥትና የደካማ ኅብረተሰብ ግንኙነት መሠረታዊ ችግር መሆኑን የበለጠ አስገነዘበ። በመሆኑም፣ መንግሥት የሕዝብና የኅብረ ተሰብ ተገዥና አገልጋይ የሚሆንበትን፣ ሕዝቡ የመንግሥት ሥልጣን ሉአላዊ ምንጭና ባለቤት የሚሆንበትን፣ እንዲሁም ሕዝቡ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና አሠራር የሕይወቱና የንብረቱ ሉአላዊ ባለቤትና ጌታ የሚሆንበትን አዲስ የፖለቲካ ኅብረተሰብና ሥርዓት በጉልበቱና በእውቀቱ የመገንባት ረጅምና መራራ ትግሉን ጀምሯል።

ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገር ግምባታ ትግል ግቡን የሚመታው ግን ሕዝቡ ራሱን በራሱ ታሪክና ልምድ መሠረት ለማደራጀትና ለመምራት ሲችል ብቻ ይሆናል። ምክንያቱም የአንድ ሕዝብ ታሪክ ኅብረተሰቡን የሚያንቀሳቅስ የመንፈስ ሞተርና ግፊት ነውና። በመሆኑም እስከ አብዮቱ የነበረውና የኃይለኛው መንግሥትና የደካማው ኅብረተሰብ ግንኙነት መሠረትና መግለጫ የሆነው የኢትዮጵያ ታሪክ ከስልተምርትና ከሥርዓተማኅበር አኳያ፣ ከኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች አኳያ ባዲስ ሳይንሳዊ ሜቶዶሎጂና ሚዛን እንደገና በትክክል ተጠንቶ መቅረብ አለበት። የዚህ ጥናት ዓላማና ተግባር በዚህ ረገድና አቅጣጫ ጅምር አስተዋጽኦ ማድረግ ብቻ ይሆናል።

## በ1855 ዘውዳዊ ምዕክልና በተጀመረ ጊዜ የኢትዮጵያ የነፃ ሕዝቦችና መንግሥታት ካርታ








### ሠንጠረዥ 1
### የኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማኅበረሰቦች ዝርዝር

| ኩሻዊ የቋንቋ ቤተሰብና ማኅበረሰቦች | አሞአዊ የቋንቋ ቤተሰብና ማኅበረሰቦች | ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰብና ማኅበረሰቦች | ናይሎዕቲካዊ የቋንቋ ቤተሰብና ማኅበረሰቦች |
|---|---|---|---|
| ቤጃ ቢለን አገው ወይጦ ፈላሻ ሶማሌ ረንዳል ጋቶ አርቦሬ ማኅጎዶ ባይላ ኮንሶ ኦሮሞ ዋራዚ ገዋዳ ፀማይ ደሳነች (ገለብ) አፋር ሳሆ ሲዳማ ከምባታ ሀዲያ ጥምባሮ አላባ ቀቤና ማሬቆ ጌዲኦ ቡርጂ ትግሬወርጅ | አሪ ሐመር በናማሌ ዘይሴ ቡላ አይዳ ዶርዜ ጎፋ ጋሞ ማሎ ወላይታ ዲማ ናኦ ጫራ ኮንታ ኩሎ (ዳወሮ) ቦሻ የም ዲዚ ባስኬቶ ሻኮ ማኦ ኩፋ ሸከቾ (ሞቻ) አንፊሎ ሺናሻ ኮራ ዘርጉላ ጋንዱላ ቃጫማ ጊዲቾ | ግዕዝ ትግረ ትግሬ አማራ አርጎባ ጋፋት ሐረሬና የጉራጌ ማኅበረሰቦች፥ ምሁር መስቃን ስልጤ እነሞር ቸሀ ጌቶ እዣ እንዳጋኝ ወለኔ ኤነር አዘርነትበርበሬ ዝዋይ ሰዶ | ማዠንገር ሙርሌ ሙርሲ ከዋንጉ ቦዲ ትሻና ሱሪ ባሌ ቡሩን ኑዌር አኙዋክ ያንጋቶም በርታ ኮማ ጃብላዊ ናራ ጉሙዝ ኩናማ ፋዳሺ |

ምንጭ ላጵሶ ጌ ድሌቦ፥ የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ(1985) ገጽ24

## ሠንጠረዥ 2
## በ1984 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከ20,000 በላይ የሰው ብዛት ያላቸው የኢትዮጵያ የ56 ብሔረሰቦች ዝርዝር

| ተቁ | ብሔረሰቦች | የሕዝብ ብዛት | | ተቁ | ብሔረሰቦች | የሕዝብ ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | ከመቶ | | | በቁጥር | ከመቶ |
| 1 | ኦሮሞ | 13027875 | 30.57 | 29 | ማሎ | 58039 | 0.14 |
| 2 | አማራ | 12055250 | 28.29 | 30 | ጥምባሮ | 57938 | 0.14 |
| 3 | ትግሬ | 4249697 | 9.74 | 31 | ሞቻ | 57505 | 0.14 |
| 4 | ጉራጌ | 1855905 | 4.36 | 32 | አርጎባ | 51877 | 0.12 |
| 5 | ሱማሌ | 1613394 | 3.79 | 33 | ሚኤን | 50405 | 10.12 |
| 6 | ሲዳማ | 1261721 | 2.96 | 34 | ናራ | 49229 | 0.12 |
| 7 | ወይታ | 1092958 | 2.57 | 35 | ባስኬቶ | 45471 | 0.11 |
| 8 | ትግረ | 683085 | 1.60 | 36 | ጃብላዊ | 44129 | 0.10 |
| 9 | ሀዲያ | 643512 | 1.51 | 37 | ዶርዜ | 43924 | 0.10 |
| 10 | አፋር | 583120 | 1.37 | 38 | ቡርጂ | 43259 | 0.10 |
| 11 | አገው | 489834 | 1.14 | 39 | ኮንታ | 39305 | 1.09 |
| 12 | ጋሞ | 463933 | 1.09 | 40 | ሻንቅላ | 38731 | 0.08 |
| 13 | ጌዴኦ | 455408 | 1.07 | 41 | ፈላሻ | 34056 | 0.08 |
| 14 | ከፋ | 443209 | 1.04 | 42 | ጉሙዝ | 33833 | 0.08 |
| 15 | ከምባታ | 432812 | 1.02 | 43 | ደሳች | 32629 | 0.08 |
| 16 | ደሙቴ (ደወሮ) | 275552 | 0.65 | 44 | ጊዶሌ | 31048 | 0.07 |
| 17 | ቅማንት | 169168 | 0.40 | 45 | ማሌ | 30887 | 0.07 |
| 18 | ጎፋ | 154041 | 0.36 | 46 | ሼኮ | 30763 | 0.07 |
| 19 | ሳሆ | 144485 | 0.34 | 47 | አኙዋክ | 30499 | 0.07 |
| 20 | ቤጃ | 124342 | 0.29 | 48 | አደሬ | 29518 | 0.07 |
| 21 | ቤንቾ | 123034 | 0.29 | 49 | ኑዌር | 27827 | 0.07 |
| 22 | የም | 115906 | 0.27 | 50 | ሐመር | 26759 | 0.06 |
| 23 | አሪ | 109124 | 0.26 | 51 | መሎ | 26087 | 0.05 |
| 24 | ኩናማ | 99999 | 0.24 | 52 | ዲዚ | 22329 | 0.05 |
| 25 | ኮንሶ | 94719 | 0.22 | 53 | ንዋዳ | 20122 | 0.05 |
| 26 | ቢለን | 88453 | 0.21 | 54 | ሺናሻ | 20002 | 0.05 |
| 27 | አላባ | 83839 | 0.19 | 55 | ሌሎች | 727310 | 1.70 |
| 28 | ኮይራ | 69852 | 0.16 | 56 | የውጭዜጎች | 9041 | 0.02 |
| | | | | | ድምር | 42616876 | 100% |

Source: The 1984 Population and Housing Census Commission of ethiopia (1991)





## ሠንጠረዥ 3
## በ1994-97 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች ዓይነትና ብዛት

| ክልል | የሕዝብ ብዛት | ሃይማኖት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ኦርቶዶክስ | ፕሮቴስታንት | ካቶሊክ | ሙስሊም | አዋማዊ |
| አዲስአበባ | 2,121,737 | 1,732,374 | 81,759 | 16,448 | 267,693 | 385 |
| ኦሮሚያ | 18,737,820 | 7,621,727 | 1,188,310 | 10,310 | 8,178,085 | 778,359 |
| አማራ | 13,834,297 | 11,264,297 | 11,392 | 937 | 2,541,834 | 2,734 |
| ደቡብ ብብሕ | 10,371,192 | 2,862,734 | 3,611,583 | 307,604 | 1,735,214 | 594,374 |
| ትግራይ | 3,136,267 | 2,992,305 | 1,136 | 12,489 | 727,657 | 53 |
| ሐረሪ | 131,139 | 49,554 | 1,231 | 603 | 78,952 | 34 |
| ድሬዳዋ | 151,864 | 86,777 | 2,668 | 1,818 | 158,871 | 11 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 460,459 | 160,079 | 26,917 | 2,532 | 202,970 | 60,346 |
| ጋምቤላ | 162,397 | 39,187 | 71,478 | 5,205 | 8,362 | 16,699 |
| ሶማሌ | 3,382,762 | 31,586 | 3,451 | 3,988 | 3,340,101 | 2,093 |
| አፋር | 1,097,064 | 42,448 | 4,765 | 944 | 1,048,710 | |
| ጠ/ ድምር | 53,382,958 | 26,783,468 | 6,305,690 | 459,918 | 16,588,539 | 2,467,088 |
| | 53,000,000 | 27,000,000 | 6,000,000 | 500,000 | 17,000,000 | 2,500,000 |

ምንጭ በ1994-97 የቤትና ሕዝብ ቆጠራ ከ11 ብሔራዊ ክልሎች ዘገባ በለቀማ የተገኘ